# የምሥራች!

## ቸሩ እግዚአብሔር፡
## እንኳን፡ እናንተንም÷ እኛንም፡
## ለታላቁ፡ ቋሚ እና ዘላለማዊ ምሥራቹ አበቃን!

እናንተ እና እኛ፡
እየራሳችንን፡ ለዚሁ ምሥራች በማብቃታችን፡
በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን!
ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!

በልዑል ፈጣሪያችንና በቅድስት እናቱ ፈቃድና ጥበብ÷ ጸጋና ረድኤት÷
እንዲሁም፡ በየግላችሁ በወሰናችሁት፡
የሃይማኖት ቈራጥነትና በፈጸማችሁት፡ የምግባር ጀግንነት፡

በአኹኑ ጊዜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡
ጸንታችሁ ለተገኛችሁ÷
ደግሞም፡ እየራሳችሁን በንስሓ አስተካክላችሁ፡
ማንነታችሁን፡ ለዚሁ የተቀደሰ ኢትዮጵያዊነት ሳበቃችሁ÷
ለማብቃትም፡ በገድል ጉዞ ላይ ላላችሁ÷

በምድረ ኢትዮጵያ ለምትኖሩና በመላው ዓለም ለተበትናችሁ÷
ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት፡ ለኹላችሁ÷
ይህ የምሥራች መልእክት ይድረሳችሁ!

በቅድሚያ፡ በቅድስቲቱ ሃይማኖታችንና አገራችን÷ እናታችንና ንግሥታችን ድንግል ማርያም እና በመለኮታዊው ልጇ፡ በፈጣሪያችንና አምላካችን÷ ካህን፡ ሊቀ ካህናታችን÷ ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን፡፡

ቀጥለንም፡ በእኛ በኩል፡ “የምሥራች! በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!” እንላችኋለን፡፡

እናንተም፡ “ምን አዲስ ነገር አገኛችሁና ነው? ምንስ እንግዳ ነገር መጣላችሁና ነው? 'የምሥራች!' የምትሉን?” ብላችሁ ትጠይቁን ይኾናል፡፡

ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ መልሱ፡ እንደሚከተለው፡ በስፋት ቀርቦላችኋልና፡ ተመልከቱት፡-

## መግቢያ

ባለፈው ሰሞን፡ በዚህ የጎዋ ስሌዳችን ዋና ገጽ ላይ በወጣው የበዓለ ትስብእት መልእክት መክፈቻ ላይ፡ የዛሬ ኹለት ሺህ አንድ ዓመት፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ ስለተነገረው፡ ስለመጀመሪያው፡ ታላቁ ምሥራች! አንሥተን፡ ዛሬ፡ ከኹለት ሽህ የምሕረት ዓመታት በኋላ፡ በዚህ፡ በ፪ሽህኛው የመጀመሪያ ዓመት ላይ፡ ይኸው ታላቁ ምሥራች! እንደገና፡ እንደአዲስ፡ ሊቀርብና ሊገለጽ፥ ሊነገርና ሊደመጥ፥ ሊጻፍና ሊነበብ፡ እጅግ አስፈላጊ እንደኾነ፡ ምክንያቱን ጭምር፡ ገልጸን እንደነበረ ይታወሳል፡፡

እርሱም፡ እንዲህ የሚል ነበር፡፡ ያ፡ ቅዱስ ገብርኤል የተናገረው፡ የመጀመሪያው፡ ታላቁ ምሥራች፡ “በአካሉና በባሕርዩ፥ በግብሩና በፍሬያማነቱ፡ የማይለወጥ፡ ያው አንዱና ራሱ፥ የጥንቱና የመሠረቱ ቢኾንም፡ ዛሬ፡ የሚቀርብበትና የሚገለጽበት መልክና ይዘት፡ በቀደመው ዓይነት ሊኾን አይችልም፡፡ እንደዚያ ሊኾን የማይችልበት ምክንያት፡ ያ፡ የቀደመው 'ምሥራች!'፡ የተነገረውና የተደመጠው፥ ኋላም፡ የተጻፈውና የተነበበው፡ የክፉቱ ኃይል፡ ዲያብሎስ፡ በእሥራት መጋዙ በተጀመረበት ዘመን ሲኾን፥ ይኸኛው፡ የዛሬው 'ምሥራች!' ግን፡ የሚነገረውና የሚደመጠው፥ ከዚያም፡ የሚጻፈውና የሚነበበው፡ ይኸው፡ የክፉቱ አበጋዝ፡ ዲያብሎስ፡ እንደመለኮታዊው ቃል፡ ከእሥራቱ፡ ለጥቂት ጊዜ፡ በተፈታበት የመጀመሪያ ዓመት በመኾኑ ነው፡፡

“ስለዚህ፡ የዚያ፡ የቀዳማዊው መለኮታዊ ምሥራች፡ ፍሬ የኾነው፡ ይህ፡ የዛሬው 'ምሥራች!' አቀራረብና አገላለጽ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ሰፍኖ ከሚታየው፡ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን፥ ከመላው የምድሪቱ ኅብረተሰብና ከፍጥረተ ዓለሙ ኹኔታና ይዞታ አንጻር፡ ያለውን ትክክለኛ አግባብነት በማሳየት ይኾናል፡፡”

እንግዴህ፡ በዚህና በሌሎቹ ተዛማጅ ምክንያቶች ላይ የተመሠረተው፡ የዛሬው **“የምሥራች! መልእክታችን”** እነሆ፡-

አስቀድመን ግን፡ የእኒህ ኹሉ ምክንያቶች፡ መነሻ የኾነው መሠረት፥ ምንጭና ግንድ፡ ምን እንደኾነ፡ ልንገልጽላችሁ ያስፈልገናል፤ እርሱም፡ መጀመሪያው፡ “አንትሙሰ፡ ኅሡ፡ መቅድመ፡ መንግሥቶ፥ ወጽድቆ፤ ወዝንቱሰ ኵሉ ይትዌሰከክሙ!” ማለትም፡ “እናንተ፡ አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ እውነቱንም ሹ! ሌላው ኹሉ ይጨመርላችኋል!” የሚለው፡ የኢትዮጵያዊው መሪያችንና መምህራችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ቃል ነው፤ መጨረሻው ደግሞ፡ ከዚያ ተከትሎ የተገኘው፡ የመሠረቱ ቋሚ አካል፥ የምንጩ ለምለም ውጤትና የግንዱ ጫፋጭ ፍሬ ነው፡፡ ያ፡ ቋሚ አካል፥ ያ፡ ለምለም ውጤትና ያ፡ ጣፋጭ ፍሬም፡ ይህን ሕያውና ዘለዓለማዊ መመሪያ ቃል፡ እናንተም፥ እኛም፡ በሃይማኖት ተቀብለን፡ በምግባር ለመፈጸም መቻላችን ነው፡፡ (ማቴ. ፮÷ ፴፫፡፡)

ይህ ረቂቅ ምሥጢር፡ ለእናንተ እና ለእኛ ተገልጾልንና አውቀነው፡ በየራሳችን እውን ልናደርገው፡ እንዴት ቻልን? አኹንም፡ የዚህ ጥያቄ መልስ፡ አጭርና ግልጽ ነው፡- ይኸው መሪያችንና መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሱው፡ ራሱ፡ ጥንቱኑ፡ ሲፈጥረን፡ ለእያንዳንዳችን፡ በቸርነቱና በለጋሥነቱ ካቀዳጀን፡ ከእግዚአብሔራዊው መልካችን የተነሣ፡ እግዚአብሔራዊ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን፥ እንዲሁም፡ ያን ምርጫችንንና ውሳኔያችንን ለመተግበር የሚያበቃን፡ ፍጹም ኃይል ያለን መኾናችንን፡ እግዚአብሔራዊቷ እውቀት፡ ከሠተችልና! በእርሷም ተመርተን፡ በእግዚአብሔር መልክ ከተፈጠርንበት፡ ከየራሳችን ባፈለቅነው፡ በእውነተኛው ፍላጎታችንና በበጎው ምርጫችን ተጠቅመን፥ ቆራጡን ውሳኔያችንን በሥራ ላይ አዋልነዋ! ይህ ነው፡ አጭሩና ግልጹ ምላሽ፡፡

ይህን እውነታ፡ እንዲህ በሚል አንድ ዐረፍተ ነገር፡ አጠቃልሎ ማብራራት ይቻላል፡- ጥንቱኑ፡ "የሰው ልጆች" የተባሉት የቃኤል ዘሮች፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ በተሰጣቸው፡ በዚሁ **የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን፥ እንዲሁም፡ ያን ምርጫቸውንና ውሳኔያቸውን ለመተግበር በሚያበቃቸው፡ ፍጹም ኃይል ተጠቅመው፡** ሰይጣናዊ የኾነውን፡ ክፉውን ወገን ለመምረጥና ለመወሰን፥ ያን፡ መርጠው የወሰኑትንም፡ በሥራ ላይ አውለው፡ ለመራራው ፍሬ በማብቃት፡ ፍጻሜው፡ የዘለዓለም ሞት በኾነው በሥጋዊው የጥፋት መንገድ፡ እርስ በርሳቸው እየተላለቁ፡ የሲያል ኑሮን፡ ሳያቋርጡ ለመኖር መቻላቸውን፡ እነሆ፡ እንመለከታለን።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ለእናንተ እና ለእኛም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በሚያሰኘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን፡ በዚያው፡ <u>ነጻነትና ሥልጣን፥ ኃይልም በመጠቀም፡ እግዚአብሔራዊ የኾነውን፡ መልካሙን ወገን መርጠን ለመወሰንና ያን ምርጫችንን፡ በተግባር ላይ አውለን፡ ለጣፋጩ ፍሬ በማብቃት፡</u> በፈተኛው የመንፈስ ትንሣኤ ለመኖር፡ እነሆ፡ ዕድሉን አግኝተን፡ በምድር ላይ፡ ዛሬ፡ በሥጋ እያለን፡ እንዲህ፡ የተድላ ገነት ሕይወትን ለመኖር ተቻለን ማለት ነው።

## ክፍል አንድ

ለመግቢያ ያህል፡ ይህን ካልን፡ "የምሥራች! በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሐሜትም እናድርግ!" የምንላችሁ፡ ለምን እንደኾነ፡ ከዚህ እያይዘን እናብራራላችኋለን። አዎን! "የምሥራች! በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሐሜትም እናድርግ!" የምንላችሁ እኮ፡ እንዲሁ በከንቱ፥ ያለምክንያትም አይደለም፤

- እግዚአብሔር፡ በአንድነቱ፡ እናንተንና እኛን፡ ወንዶቹንና ሴቶቹን፡ ኹላችንንም፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ በሥላሴነቱ፡ "የፈጠርነው ሰው፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ያሰኘውን የአምላክነት ማዕርግ፡ ለእያንዳንዳችንን በማቀዳጀቱ ብቻም አይደለም፤
- ፈጣሪያችን፡ እንዲህ አድርጎ ያከበረውንና ያላቀውን ሰብአዊ ተፈጥሮአችንን፡ "የሰው ልጆች" የተባሉት፡ የቀደሙትና የኋለኞቹ ወንዶችና ሴቶች፡ በገዛ ፍላጎታቸውና ፈቃዳቸው፥ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው፡ እየራሳቸውን፡ የእግዚአብሔር እውነት ተቃዋሚ ለኾነው፡ ለሓሰት አባትና ለክፋቱ አበጋዝ፡ ለዲያብሎስ፡ አሳልፈው ሰጥተው፡ ኹለንተናቸውን፡ ለእርሱ፡ በባርነት ባስገዙ ጊዜ ደግሞ፡-
    - እኒያን የጠፉትን ሰብአውያን ፍጡሮቹን ፍለጋ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፥
    - በኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን፡ ሰው ኾኖ፡ በ"በረት" ተወልዶ፥
    - በሕፃንነቱ፡ ተሰድዶ፥
    - በልጅነቱ፡ ቤተሰቡንና ኅብረተሰቡን አገልግሎ፥
    - በ፴ ዓመት ዕድሜው፡ ተጠምቆ፥
    - ወዲያው፡ ለትጋሃ ሱባኤ፡ ወደቆሮንቶስ በረሀ ኼዶ፡ በዚያ፡ ለ፵ ዕለታት ጾሞና በዲያብሎስ ተፈትኖ፥
    - በየገጠሩና በከተሞች እየተዘዋወረ፡ ስለእግዚአብሐር መንግሥት፡ በምድር ላይ መስፈን፡ ከምሥራቹ አዋጅ ጋር፡ ማንነቱን አረጋግጦ ለማሳመን፡ ተአምራትን እያደረገ፡ ካስተማረ በኋላ፡
    - በዓይነታቸውና በብዛታቸው፡ ወደር የማይገኝላቸውን፡ የመስቀል መከራዎችን፡ በጽኑ ትእግሥት ተቀብሎ፥

- ጥፋትንና በደልን፡ በንስሓ፡ ድል እያደረግን፡ ለሥጋዊውና ለነፍሳዊው ህልውናችንና ሕይወታችን፡ ምግብ፥ ለሥጋዊውና ለነፍሳዊው ኃጢኣትና ርኵሰት፡ ማስተስረያ፥ ለሥጋዊውና ለነፍሳዊው ደዌና ሞት፡ መድኃኒት ይኾነን ዘንድ፡ በመስቀል ላይ የተቆራረሰ፡ ቅዱስ ሥጋውን፡ "እንካችሁ ብሉት"፥ የፈሰሰ ክቡር ደሙንም፡ "እንካችሁ ጠጡት!" ብሎ ሰጥቶ፥
- ሞቶ፥ ተገንዞና ተቀብሮ፥
- ከ፫ ቀኖች በኋላ፡ በዘለዓለማዊው የትንሣኤ አካል ተነሥቶና ዓርጎ፥
- በመጨረሻ፡ በመንፈስ ቅዱስ ማንነቱ፡ ተመልሶ መጥቶ፡ እናንተንና እኛን፡ ክክፋት ኃይላትና ከኃጢኣት፥ ከሞትና ከሙስናም በማዳኑና በመጠበቁ ብቻም አይደለም፤

- ከቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንና ምግባራችን የተነሣ፡ እናንተና እኛ፡ ዛሬ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትና ሕይወት ውስጥ የምንኖር በመኾናችን ብቻም አይደለም፤

- ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለድ፡ ሰው ኾኖ፡ እንዲህ አድርጎ ያዳነን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ እናንተና እኛ፡ እርሱ ባስተማረንና በሚወድደው፡ በቅዱሱ ኪዳን የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችን ተቀብለን፡ ብፅዕናን በሚያድለው፡ በፊተኛው ትንሣኤ ለመኖር በመብቃችን ብቻም አይደለም፤

- እናንተና እኛ፡ ከዚሁ ብቅዓታችን የተነሣ፡ በዚህ ዓለም፡ በአካለ ሥጋ እያለን፡ መልካሚቱን የገነት ሕይወት ለመኖር በመቻላችንና በማንኛዪቱ የዳግም ምጽአቱ ቅጽበት፡ በትንሣኤ አካል እርሱን ለመቀበል የተዘጋጀን ኾነን በመገኘታችን ብቻም አይደለም፤

- ፈጣሪ፡ ጥንት፡ በአዳምና በሔዋን ሰውነት፥ በኢትዮጵያ ምድር፡ የመሠረታትን፥ ከዚያን ጊዜም ወዲህ፡ የእርሱ "የእግዚአብሔር ልጆች" መኾንን በመረጡት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወላጆቻችን፡ እስካኹን ተጠብቃ ያለችውን መንግሥቱን ለማፍረስ፡ ምድራዊ ገንዘብንና ንብረትን፥ ሥጋዊ እውቀትንና ጥበብን፥ ዓለማዊ ኃይልንና ጦር መሣሪያን መመኪያቸው አድርገው የሚዋጓትን፡ ይኼን ዲያብሎስንና ጭፍሮቹን፡ "የሰው ልጆች"፡ እናንተና እኛ፡ እንዲህ ተቋቁመን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ በእያንዳንዳችን የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሰውነታችን አማካይነት፡ በዘለዓለማዊ ህልውናዋ እንድትቀጥል በማድረጋችን ብቻም አይደለም፤

- "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው የዛሬው ትውልድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ እየፈጸመ ባለው፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትም ኃጢኣት ምክንያት፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ እንደኖኅ ዘመን በተቈጠረው፡ በዚህ፡ በአኹኑ ዓለም ላይ ከሚደርሰው ጥፋት፡ እናንተና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንን ጠብቀንና በምግባር ፈጽመን በመገኝታችን የምንድን በመኾናችንም ብቻ አይደለም፤

- በመጨረሻም፡ ይህችኑ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ ፈጽመው ለማጥፋት፡ ከቀድሞ ጀምረው፡ ዐቅደው፡ ሲጥሩበት የኖሩትን ዓላማቸውን፡ ዛሬ፡ ከግቡ ለማድረስ ቆርጠው በተነሡት፡ በዲያብሎስና በሠራዊቱ የሰዎች የክፋት ኃይላት፥ በኃጢኣትና በሞት ላይ፡ ዘለዓለማዊ የድል ዘውድን የተቀዳጀው፡ ኢትዮጵያዊው አንበሳ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከኢትዮጵያዊቷ እናቱና እናታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን፡ ድንግል ማርያም ጋር፡ በሊቀ ካህናትነቱ መለኮታዊ ሥልጣን፥ በንጉሠ ነገሥትነቱም ገናና ክብርና በእግዚአብሔራዊው ሉዓላዊ ምስጋና ሲገለጥ፡ እናንተና እኛ፡ በዚያ ትንሣኤ ዘጉባኤ ላይ፡ በታማኝ ባለሟልነት ማዕርግ የምንገኝ በመኾናችን ብቻም አይደለም፡ "የምሥራች! በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!" የምንላችሁ።

“የምሥራች! በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!” የምንላችሁ እኮ፡ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ሕያዋን ጥሪቶቻችንና ይዞታዎቻችን ጋር የሚነጻጸሩና የሚወዳደሩ፡ ሌሎች፡ አያሌ፡ መለኮታውያን ሀብቶችና ስጦታዎችም ስላሉን ነው:: እኒህንም፡ የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪና ባለቤት የኾነው እግዚአብሔር፡ ለእናንተ እና ለእኛ ብቻ ሳይኾን፡ ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በለጋሥነቱ ያደላቸው፡ ግልጽ ጸጋዎቹ ናቸው::

ይኹን እንጂ፡ እኒህን ግልጽ ጸጋዎች፡ ከሰው ልጆች መካከል፡ ሊያውቃቸውና ሊያስተውላቸው የሚፈልግ ወገን በመታጣቱ፡ እንደሌሉ ተቆጥረው ኖረዋል:: መላው፡ የሰው አእምሮና ጊዜ፥ ጕልበትና ገንዘብ የሚጠፋውና የሚባክነው፡ ለዓለሙ ሰዎች እንኳ፡ ሊረባቸውና ሊጠቅማቸው ላልቻለው፥ እንዲያውም፡ እነርሱኑ መልሶ ሲጎዳቸውና ሲያጠፋቸው ለሚኖረው፡ ለሥጋዊውና ለምድራዊው ኑሮና ዓላማ ብቻ መኾኑ፡ እነሆ፡ በእውን ሲካኼድ የሚታይ እውነታ ነው::

እንግዴህ፡ በዚህ እውነታ መሠረትነት፥ ምንጭነትና ግንድነት፡ እናንተንና እኛን፡ ለዚህ፡ ለቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቁንና በዚሁ ሕይወታችን ላይ የተከሠቱት፡ ዋና ዋናዎቹ መለኮታውያን ምክንያቶችና ስጦታዎች ምንድር ናቸው? እነዚህ ቍም ነገሮች ሲተነተኑ፡ እነሆ፡ እንዲህ በሚል ሓተታ ተብራርተው ቀርበውላችኋልና፡ በማስተዋል ተመልከቷቸው:-

## ፩ኛ፡ <u>በእግዚአብሔር እውቀት መመራታችን::</u>

እናንተ እና እኛ፡ ፈጣሪያችን፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በየልባችን ላይ የጻፈውንና በየልቦናችን ውስጥ ያሳደረውን፡ የእርሱን፡ የእግዚአብሔርን እውቀት <u>ብቻ</u> ተከትለን የምንኖርና የምንሠራ በመኾናችን ነው፤ የሰዎችን፥ ወይም፡ የባዕዳኑን፥ ወይም፡ የሰይጣኑን እውቀት ሳይኾን ማለት ነው::

ይህችም የእግዚአብሔር እውቀት፡ ለ፯ሺ፭፻፩ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ አንድ) ዓመታት፡ በመከራ እሳት ተፈትና፡ በወርቅነቷ ነጥራ ለወጣችው፡ ለእውነተኛዪቱ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን ያበቃችን ናት:: አዎን! የሰዎችን፥ ወይም፡ ሰይጣናዊዉን ሳይኾን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ብቻ ተከትለን እንድንኖር ያስተማረችን፥ የመራችንና ያስቻለችን፡ ይህችው፡ መለኮታዊት እውቀት ነች::

ራሱ፡ እውነት የኾነው እግዚአብሔር፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር፥ ከረቂቅነት ወደግዙፍነት አምጥቶ፡ በመልኩ የፈጠረንና በዚህ ዓለም የሚያኖረን፥ የሚወስደንም፡ በእርሱ እውነት እንደመኾኑ መጠን፡ እኛም፡ ልንኖር የሚገባን፡ በእግዚአብሔር እውነት፥ ለእግዚአብሔር እውነትና ስለእግዚአብሔር እውነት መኾን እንዳለበት ያስገነዘበችን፥ እንዲሁም፡ ከዚህ ቀጥለው በተከታታይ የቀረቡትን እግዚአብሔራውያን እውነታዎች ያስረዳችን፥ ባጠቃላይ፡ ስለእግዚአብሔር እውነት ያስተማረችን፡ ይህችው፡ የእግዚአብሔር እውቀት ናት::

በእርሷ፡ ኹሉን አወቅን:: እየራሳችንንና ራሱን እግዚአብሔርን፥ ሰብአዊ ፍጡሩንና መላውን ሥነ ፍጥረቱን፥ ሥጋዊዉን፥ ነፍሳዊዉንና መንፈሳዊዉን፡ ኹሉንም፡ ፈጽመን አወቅን:: የእናንተ እና የእኛ አስተማሪ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር፥ ትምህርታችንም፡ ከእርሱ ብቻ ያገኘነው መኾኑን ያሳወቀችንና ያሳመነችን፡ ይህችው፡ የእግዚአብሔር እውቀት ናት::

ከዚህ የተነሣ ነው፡ በየዕለቱ፡ በሠርክ ጊዜ፡ በዝማሬ በምናስሰማው፡ የኪዳን ጸሎታችን፡ “ለከ ለአብ፡ ዘኢይማስን፤ መድኃኔ ነፍስነ፤ ወመሠረተ ጥበባት፤ ዐቃቤ አልባቢነ፤ ዘእንተ ውስጥ ዓይነነ፡ አብራህከ፥ ወጽልመተ ኀሊናነ፤ <u>በዘዚአከ አእምሮ ከለልከነ አንተ::</u>”

ማለትም፡ “እግዚአብሔር አብ ሆይ! ከመለኮታዊው ባሕርይህ የማትለወጥ፥ የነፍሳት መድኃኒት የምትኾን፥ የጥበባት ኹሉ መሠረት፥ የልቡናችንም ጠባቂ ነህ፤ ውሳጣዊ ዓይናችንን፡ ብሩህ አደረግህልን፤ የኀሊናችንንም ጨለማ፡ አርቀህ፥ <u>የአንተንም እውቀት፡ ለእኛ ሰጥተህና የመጨረሻውን፡ የእውቀት አክሊል አቀዳጅተህ፡ አከበርኸን::”</u> እያልን ፈጣሪያችንን የምናመሰግነው::

ደግሞም፡ በዘወትሩ የቃል ኪዳን ጸሎታችን፡ "ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሐፈ ኢትዮጵያውናነ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፥ ወመሀረነ፥ ወረሰየነ፡ ንዕቀብ በሀልዎትነ በእንተ ቃለ ኪዳኑ።"

ማለትም፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን።" እያልን የምንደግመው።

እንዲሁም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ "መኑ የአምር፡ ኅሊናሁ ለእግዚአብሔር? ወመኑ መማክርቲሁ? ንሕነሰኬ፡ ኅሊናሁ ለክርስቶስ ብነ።"

ማለትም፡ "የእግዚአብሔርን፡ ኅሊናውን የሚያውቀው ማነው? አማካሪዎቹስ፡ እነማናቸው? እኛ ግን፡ የክርስቶስ፡ ኅሊናው አለን።" ሲል፡ በሐዋርያው አንደበት ያናገረውን፥ በእጁም ያስጻፈውን አምነን፡ እንዲህ በምግባር የምንፈጽመው። (፩ቆሮ. ፪፥ ፲፮።)

በዚህ ምክንያት፡ ዛሬ፡ መላው ዓለም፥ ከሃዲውንና ዓመፀኛውን፥ አመንዛሪውንም ኢትዮጵያዊ ትውልድ ጨምሮ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ወደቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ፥ ሥርዓቱና ህልውናው ካልተመለሰ በቀር፡ በኖኅ ዘመን ደርሶ በነበረው ዓይነት፡ ከሚጠብቀው የጥፋት ጽዋና ድንገተኛ የሞት ጥሪ ሠቀቀን፥ እንዲሁም፡ በምጥ ጣር ላይ ኾኖ ከሚሠቃይበት፡ የልቅሶና ጥርስ-ማፋጨት ኑሮም፡ እናንተና እኛ፡ ነጻ ወጥተናል።

በዚህ፡ በእናንተ እና በእኛ፡ የነጻነት ህልውናችን፡ "ስምዑ ቃለ እግዚአብሔር ደቂቀ እስራኤል! እስመ ይትዋቀሦሙ እግዚአብሔር፡ ለእለ ይነብሩ ውስተ ምድር። እስመ አልቦ ጽድቅ፤ ወአልቦ ምሕረት፤ ወአልቦ አእምሮ እግዚአብሔር ውስተ ምድር፡ ዘእንበለ ሓሰት ወቀትል፥ ወስርቅ፥ ወዝሙት መልአ ምድረ፤ ወዴምሩ ደም ምስለ ደም። ...ወይመስሉ ሕዝብየ፡ ከመ ዘአልቦ ልብ። እስመ ለከሂ፡ ኀደገከ ልብከ፤ ወአነሂ ኀደግሁከ።"

ማለትም፡ እናንት የእስራኤል ልጆች ሆይ! እግዚአብሔር፡ በምድር ላይ ከሚኖሩ ጋር ክርክር አለውና፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ! በዚህ ዓለም፡ ሓሰት ከመናገር፥ ነፍስ ከመግደል፥ የሰው ሀብትም ከመስረቅ በቀር፡ እውነት የለም፤ ርኅራኄ የለም፤ እግዚአብሔርንም ማወቅ የለም። ዝሙታቸው፡ ምድርን መላ፤ ደምን፡ ከደም ጋር ይደባልቃሉ።...ሕዝቤ፡ የእግዚአብሔርን እውቀት ከማጣቱ የተነሣ፡ ጠፍቷል። አንተም፡ ይህችን እውቀት ትተሃልና፡ እኔም፡ ተውሁህ።" ተብለው፡ በእግዚአብሔር ቃል ከተገሠፁትና ከተዘለፉት፡ ከእስራኤላውያን ይልቅ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የሃይማኖት ተክልና የምግባር ፍሬ፡ ጥንትም ኾነ፡ ዛሬ፡ ፈጽሞ የተለየንመኾኑ፡ ተረጋግጦ ታይቷል። (ሆሴ. ፬፥ ፩-፮።)

## ፪ኛ፡ በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራችን።

እናንተ እና እኛ፡ በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራችንን፡ ከእርሱው፡ ከፈጣሪያችን፡ ባገኘናት፡ ከላይ፡ ቀደም ብለን፡ በአንደኛነት በጠቀስናት፡ በእግዚአብሔርዋ እውቀታችን በመገንዘባችን ነው።

ይህ ግንዛቤያችን፡ እየራሳችንን፡ እንደእግዚአብሔር አድርገን እንገኝ ዘንድ አብቅቶናል። ይህም፡ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረንበት፡ በቀደመው የአዳምና ሔዋን ባሕርያችን፡ እንደሕፃናት የነበርንበት፡ ያ፡ ብቸኛው የደግ ጐናችን፥ ክፉውን ወገን ጭምር በማወቅ፡ በፍጹሙ የአምላክነት ባሕርይ የተሟላበትና በእግዚአብሔር መልክ የመፈጠር ብቅዓታችን የተረጋገጠበት ትንግርት ነው።

ያም ትንግርት፡ ፈጣሪ፡ በደግነት ባሕርዩ ብቻ ፈጥሮ፡ በተድላ ገነት ያኖራቸው፡ አዳምና ሔዋን፡ "አትብሉ!" ያላቸውን ዕፀ በለስ በመብላታቸው ምክንያት፡ በተነገረው፡ መለኮታዊ ቃል ተመስክሩዋል። መለኮታዊዉም ቃል፡ "ወይቤ እግዚአብሔር፤ 'ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ፡ ያእምር ሠናየ ወእኩየ!"

ማለትም፡ “እግዚአብሔርም አለ፤ 'አዳም፡ ደጉንና ክፉውን፡ ለይቶ በማወቅ፡ እነሆ፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!” የሚለው ነው። (ዘፍጥ. ፫፥ ፳፪።)

በእርሱም፡ ደጉን እና ክፉውን ለይተን ማወቅ ብቻ ሳይኾን፡ ደጉን፥ ወይም፡ ክፉውን መርጠን ለማድረግ የምንችልበትን ነጻነትና ሥልጣን አትርፈናል። ከዚህ፡ ከተሚላው፡ ከእግዚአብሔራዊው መልካችን የተነሣ፡ በተቀዳጀነው፡ የመምረጥ ነጻነታችንና የመወሰን ሥልጣናችን ተጠቅመን፡ ክፉውን በመተውና፡ ደጉን በመከተል፡ ይኸው፡ እናንተ እና እኛ፡ እንደእግዚአብሔር የማሰብ፥ እንደእግዚአብሔር የመናገርና እንደእግዚአብሔር የማድረግ መብትንና ችሎታን አገኘን።

## ፫ኛ፡ <u>የእግዚአብሔር በኾነው ኢትዮጵያዊነት መሠየማችን።</u>

በመጀመሪያውና በመካከለኛው፥ ይልቁንም፡ በመጨረሻው መልከ ጼዴቅ የቃል ኪዳን ጸጋ ምክንያት፡ <u>ከእግዚአብሔር ተሰጥቶን ያገኘነውን፡ የኢትዮጵያዊነትን የክብር ስምና የማዕርግ ጸጋ</u> በመሸማችን ነው።

እግዚአብሔር፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ለሰው ልጆች የሰጣቸውን፡ ሰባቱንም ቅዱሳት ኪዳናት፡ የቀደሙት ወላጆቻችንና ምዝላቶቻችን፡ ከዓለም ሕዝቦች ኹሉ ተለይተው በመቀበላቸውና ጠብቀው በመኖራቸው፡ እናንተ እና እኛ፡ በአምላክ መልክና ባሕርይ፡ የአንድነትንና የሦስትነትን ጸጋና በረከት፡ ያስገኘው፡ የኢትዮጵያዊነት ሹመት ተቀባዮችና ትክለኞች ኾነናል።

ይህም፡ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች፡ ማለትም፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት ዘሮች፡ በጋብቻ ውኅደት በተወለደው፡ በመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ ተመሥርቶ፡ በኋለኛውና በዘለዓለማዊው መልከ ጼዴቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተደመደመው ኢትዮጵያዊነት ነው።

በዚህ ኢትዮጵያዊነት፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ከኖኅና ከመልከ ጼዴቆቹ፡ ማለትም፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት፡ ከሦስቱም ዘሮች ውኅደት፡ የመወለድን ክብር፥ ከዚህም ጋር፡ እንደኖኅና እንደመልከ ጼዴቆቹ ሚመት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ባለሚሶዎች የኾኑትን፡ የቤተ ሕዝብነትን፥ የቤተ ክህነትንና የቤተ ምልክናን ሦስት ሹመቶች፡ የሚያጎናጽፈውን ጸጋ የታደሉ መኾናቸው ተረጋግጧል።

ከዚህ የተነሣ፡ እናንተ እና እኛ፡ የዚህ መለኮታዊ ጸጋና ዕድል ባለቤቶች ኾነን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ስለበቃን፡ ለዚህ ብቅዓታችን፡ ሓሤት ልናደርግ ይገባናል።

## ፬ኛ፡ <u>የእግዚአብሔር ልጆች መኾናችን።</u>

<u>የእግዚአብሔር ልጆች</u> የመኾንን የመጨረሻ ልዕልናን በመቀዳጀታችን ነው።

ይህ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾን የመጨረሻ ልዕልና፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ “የሰው ልጆች” ከመኾንና ከመባል ይልቅ፡ “የእግዚአብሔር ልጆች” መኾንንና መባልን መርጠው፡ ፈጣሪ፡ ለመላው ሰብአዊ ፍጡሩ መልካም ሕይወት በቀየሰው፡ በዚሁ ጎዳና ጸንተው ሲጓዙ በኖሩት፡ በቀደሙት የቅዱሱ ኪዳን ባለአደራዎች አባቶቻችንና እናቶቻችን አማካይነት ተጠብቆ የቆየው ነው።

እርሱም፡ ከብሉዩ ኪዳን በኋላ፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ተያይዞ በቀጠለው፡ በአዲሱ ኪዳን ሥርዓት፡ ለዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ልጅነት የበቃው፡ ኹለንተናችን ነው፤ በዚያ ኹለንተናችን ነው፡ የነፍስ ባሕርያችንና የሥጋ ተፈጥሮአችን፡ ለመልካሙ መንፈሳዊው ህላዌያችን፡ በመንፈስ ቅዱስ የተዋሓዱት። እናንተ እና እኛ፡ ለዚህ ህልውና የታደልነውም፡ በእግዚአብሔር እናት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ብቅዓትና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው ስርየትና ምሥጢረ ጥምቀት፡ እያንዳንዳችን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በቅዱሱ ቅብዓት ጸድቆ በታተመው ልደት፡ ከእግዚአብሔር በተወለድንበት ጊዜ ነው።

ከእግዚአብሔር የተወለድንበትን፡ ይህንኑ ልጅነታችንን፡ እንዲህ የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ለይቶና አብራርቶ፥ አረጋግጦም ገልጾልናል፡- “ወለእለሰ ተወክፍዎ፡ ወሀቦሙ ሥልጣነ፡ ውሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ፤ ለእለ አምኑ በስሙ፡፡ እለ ኢኮኑ፡ እምነ ዘሥጋ ወደም፤ ወኢእምሥምረተ ብእሲ ወብእሲት፡፡ አላ፡ እምእግዚአብሔር ተወልዱ፡፡”

ማለትም፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ “ለተቀበሉት ግን፥ በስሙ ላመኑት፡ ለእነርሱ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ሥልጣን ሰጣቸው፡፡ እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፡ ከሥጋና ከደም፥ ከወንድና ከሴትም ፈቃድ የተወለዱ አይደሉም፡፡” (ዮሐ. 1፥ ፲፪-03፡፡)

እግዚአብሔር፡ እንዲህ አድርጎ ወልዶ፡ የእርሱ ልጆች ለመኾን ያበቃን፡ በቅዱስ መንፈሱ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና በሥጋም የፈጠረን በመኾኑ፡ በነፍስና በሥጋ ጭምር ወልዶናል ማለት ነው፤ ይኸውም፡ በነፍስ፡ ማለትም፡ ባሕርዩ የኾነችውና “መልኩ” የተባለችው ረቂቅ አካል፥ በእናት ማሕፀን ውስጥ፡ እርሱው የፈጠረውን፡ ግዙፉን የሥጋ አካል እንድትለብስ ያደረገበት ድንቅ የሥነ ፍጥረት ጥበቡ ነው፡፡

ይኸው ፈጣሪያችን፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሣለ፡ “ስትፈልጉኝ፡ 'ፈጣሪያችን!' 'አምላካችን!' 'ጌታችን!' 'ንጉሣችን!' ወይም፡ 'ሊቀ ካህናታችን!' በሉኝ!” ያላለው፡ ነገር ግን፡ “'አባታችን!' ብላችሁ ጥሩኝ!” ያለው፥ ቅድስት እናቱን ድንግል ማርያምንም፡ በመስቀሉ ላይ ሣለ፡ ለደቀ መዝሙሩ ለዮሐንስ ወንጌላዊ በሰጠው የአደራ ቃሉ፡ “እናታችን!” በሏት ያለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ እናንተ እና እኛ አውቀናል፡፡ ማሰብና ማዘከር፥ መጸለይም ያለብን፡ በየግል፡ ለየራሳችን ብቻ ሳይኾን፡ ለኹላችንም መኾኑን፡ ፈጣሪያችን፡ በዚህ አምላካዊ ቃሉ አስተምሮናል፡፡

ለእናንተ እና ለእኛ፡ ይህን የመሰለውን ልጅነት ያስገኘልን፡ የእግዚአብሔር የአባትነቱ ፍቅር፡ ምን ዓይነት መኾኑን፡ እንዲህ፡ የሚለው የሐዋርያው ቃል ይገልጽልናል፡-

“ወርእዩ ከመ እፎ ፍቅሩ፡ ዘወሀበነ አብ፡ ከመ ውሉደ እግዚአብሔር ንኩን፤ ወኮንነሂ፡፡ ወበእንተዝ፡ ኢፈተወነ ዓለም፤ እስመ ሎቱኒ ኢያእመሮ፡፡”

ማለትም፡ “የእግዚአብሔር ልጆች እንኾን ዘንድ፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅሩን እንደሰጠን እዩ! ኾነናልም፡፡ ስለዚህም፡ ዓለም አልፈለገንም፤ እርሱን አላወቀውምና፡፡” (1ዮሐ. 3፥ ፩፡፡)

ይኸው ልጅነታችን፡ ማለትም፡ በዚህ ጸጋና ምሥጢር አማካይነት የተቀዳጀነው፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾናችን የክብር መብት፡ ለእናንተና ለእኛ፡ የፈጣሪያችንን ዘለዓለማዊ አባትነትና የቅድስት እናቱን ዘለዓለማዊ እናትነት ባስገኘው፡ በመለኮታዊው የትስብእት ደም ማኅተምና ቅብዓት ተረጋግጦልናል፡፡ የዚህ ልጅነታችን መታወቂያም፡ የእያንዳንዳችን የክርስትና ስማችን ስለኾነ፡ ይህንኑ፡ በቅዱሱ ቅብዓት ታትሞ፡ በዘለዓለማዊነት የጸደቀውን፡ የክብር ስማችንን፡ እነሆ፡ በዘወትር ጸሎታችን እያወሳን፡ እናዘክረዋለን፡፡

በዚህ ልጅነት ምክንያት፡ የተገኙት ጸጋዎችና በረከቶች ኹሉ፥ ማለትም፡ ሕዝባዊነቱ (ምእመንነቱ)፥ ካህንነቱና መለክነቱ፥ በእናንተ እና በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ለወንድ ብቻ ሳይኾን፡ ያለጾታ ልዩነት፡ ለሴትም ጭምር፡ በእኩልነት ደረጃ የተሰጡ መኾናቸውን በማረጋገጥ፡ ኹላችንም ተቀብለን ስንፈጽማቸው፥ ስንጠቀምባቸውና ስንሠራባቸው ኖረናል፤ ዛሬም፡ እየኖርን እንገኛለን፤ ወደፊትም፡ እንኖራለን፡፡

ይህም እውነታ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ፡ የቤተ ሕዝቧ፥ የቤተ ክህነቷና የቤተ ምልክናዋ፡ የበላይ ተጠሪዎች ኾነው ያገለገሉትን፡ በዘመነ ብሉይ፡ እነንግሥት ማክዳን፥ በዘመነ ሓዲስም፡ እነንግሥት ሕንደኬንና የቅርቧን፡ እነንግሥት ዘውዲቱን በመሰሉት ሴቶቻችን ህልውና ተረጋግጦ ታይቷል፡፡ በተለይም፡ ኢትዮጵያዊት እናታችንና አገራችን፥ ሃይማኖታችንና ንግሥታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ራሷን፡ ለእግዚአብሔር እናትነት ማብቃቷ፡ ለዚህ እውነታ ትክክለኛነት፡ የማያፈናፍን ጽኑ ማስረጃ ነው፡፡

እግዚአብሔር፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ በመልኩ ያበጀውን ሰውን ለማስገኘትና ሰብአዊዉን ዘር ለማብዛት ሲል፡ በመለኮታዊ ጥበቡ፡ ለመልካሙ ሕይወት የሠራውን፡ የሴትን የወር አበባና እርግዝናዋን፥ ልጅ መውለዷንና አራስነቷን፡ ከአምላካዊው ቃልና ሥርዓት ውጪ፡ እንደመርገምና እንደርኵሰት የሚቈጥረውን፥ ቀድሞ፡ "እስራኤላውያን ነን!" ከሚሉት ከአይሁድ የተወረሰውን፡ ኦሪታዊና ኋላም፡ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን የጸናውን ሰይጣናዊ ወግ፡ እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የማንቀበለው፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑ ሊታወቅ ያስፈልጋል፡፡

ይልቁንም፡ ሴቷ ብቻ ሳትኾን፡ ወንዱ ጭምር፡ ለአካለ መጠን፡ ማለትም፡ ወንዱ፡ ለዓቅመ አዳም፥ ሴቷም፡ ለዓቅመ ሔዋን ሲያደርሱ፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ያገኙት የሥጋ ሥርዓት ያስከተለው የኃብቻ ፍላጎታቸውና የሴቷ ለወር አበባነት መብቃት፡ እንደኃጢኣት ተቆጥሮባቸው፡ የመድኃኒታቸውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቍርባን ከመቀበል ታግደው፡ የሚከለከሉ መኾናቸው፡ በይፋ ይታወቃል፡፡ ይህ ጉዳይ፡ በወላጆች ዘንድና በቤተሰብ አካባቢ ብቻ ታውቆ የሚቀርና የሚፈጸም ሳይኾን፡ የአገሪቱ የኅብረተሰብ አካል አባላት የኾኑት፡ የቀደሙትም ኾኑ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ቤተ ሕዝብና ቤተ ምልክና፥ ቤተ ክህነቱም ጭምር የተባበሩበት ክፉ ድርጊት ኾኖ ኖሩዋል፡፡

ይህ ክፉ ድርጊት እየቀጠለ እንዲካኼድ ሲደረግ የሚታየው፡-

- እግዚአብሔር ወልድ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶና በመስቀል ላይ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፥ ክቡር ደሙንም አፍስሶ፥ ሞቶ፥ ተቀብሮና ተነሥቶ፡ ለዲያብሎስ የተዳረጉትን፥ በኃጢኣት የታሠሩትንና ሞት የተፈረደባቸውን፡ ሰብአውያን ፍጡሮች ኹሉ፥ እነዚህን ጎልማሶችና ቆነጃጅት ጭምር፡ ከዲያብሎስ፥ ከኃጢኣትና ከሞት ብቻ ሳይኾን፡ ከማናቸውም፡ የነፍስና የሥጋ መርገምና ርኵሰት ያዳናቸው መኾኑ እየታወቀ፥ ዘወትርም (በዘልማድ ኾነ እንጂ፡) እየተጸለየ እና እየተሰበከ ነው፤
- አዎን! የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች በኾኑት፡ በእነዚህ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወጣቶች ላይ፡ ይህ ኹሉ ታላቅ በደልና ከባድ ወንጀል እየተፈጸምባቸው የቀጠለው እኮ፡ እኒሁ ጎልማሶችና ቆነጃጅት፥ ሌላውም፡ ማነኛውም ምእመን፥ ወንድ ኾነ ሴት፡ በሥጋዊው ተፈጥሮአቸውና በዕድሚያቸው የፍትወት (የፍላጎት) አስገዳጅነት ምክንያት ተገፋፍተው፡ ከኃብቻ ውጪ የሚፈጽሙት የዝሙት ኃጢኣት ቢኖር እንኳ፡ በእውነተኛ ንስሓ ሊያስወግዱት የሚቻል መኾኑ እየታወቀና እየተሰበከም እኮ ነው፤
- ይልቁንም፡ በቅድስት ድንግል ማርያምና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የተገኘችው እውነተኛ ንስሓ፡ ኃጢኣተኛውን፡ ድንግል እንደምታደርግ እየታወቀና እየተሰበከም እኮ ነው፤

ይህን እውነታና ኹኔታ፡ በአንደበታችን፡ ዘወትር የምናሰማው፡ ከብዙው መካከል፡ እንዲህ የሚለው፡ የውዳሴ ማርያም ጸሎታችን ያረጋግጣል፡-

"ነበ ህለወት፡ ብዝኀት ኃጢኣት፥ በህየ ትበዝኅ፡ ጸጋ እግዚአብሔር፡፡ ...ትምክሕተ ኵልነ፡ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤ ዘበእንቲአሃ ተሰዕረ ዘቀዳሚ መርገም፥ እንተ ኀደረት ዲበ ዘመድነ፡፡ ...ወወለደት ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ፡ ዘይሰዕር መርገመ፡ እምዘመድነ፡፡ ..."ማርያም ድንግል፡ ሙዳየ ዕፍረት! ነቅዐ ፈልፈለ ማየ ሕይወት፤ ፍሬ ከርሣ አድኅነ ኵሎ ዓለመ፤ ወሰዐረ እምኔነ መርገመ፡፡"

ማለትም፡ "ብዙ ኃጢኣት ባለችበት፥ በዚያ፡ የእግዚአብሔር ጸጋ፡ በዝታ ትገኛለች፡፡ ...በተፈጥሮ ባሕርያችን ውስጥ፡ ጸንቶ የኖረው፡ የቀድሞው መርገመ ሥጋና መገመ ነፍስ፡ በእርሷ ምክንያት የጠፋልን፡ አምላክን የወለደች ድንግል ማርያም፡ የኹላችን መመኪያ ናት፡፡ ...ከአዳምና ሔዋን ተያይዞ፡ በባሕርያችን፡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣብንን፡ መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ ያጠፋልንን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደችልን፡፡"

ኢትዮጵያውያን ጐልማሶችንና ኢትዮጵያውያት ቈነጃጅትን፡ ከቅዱስ ቍርባን የሚያርቀው፡ ይህ ድርጊት፡ ከመንፈስ ቅዱስ ያልኾነ፡ የሰዎች ሰይጣናዊ አስተሳሰብ ያፈለቀው፡ ክፉ ልማድ ስለኾነ፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ዘንድ፡ በመለኮት ቃል የተወገዘ ኾኖ፡ እስከዛሬ ኖርዋል፡፡ ዛሬም፡ በንስሓ ታርሞ እስካልተስተካከለ ድረስ፡ ይኸው፡ የሰዎች ሰይጣናዊ ልማድ፡ እናንተ እና እኛ፡ ከእግዚአብሔር አግኝተን የኖርንበትን መለኮታዊ ሥርዓት የሚጻረር በመኾኑ፡ ከክፋቱ አበጋዝ፡ ከዲያብሎስና ከአገልጋዮቹ ሠራዊት ጋር፡ በዚሁ፡ በሚገኝበት መለኮታዊው የውግዘት እሥራቱ፡ አኹንና ወደፊትም፡ እንደቀጠለ ይገኛል፡፡

በዚህ፡ የሰዎች ወግና ሰይጣናዊ ልማድ ምክንያት፡ እግዚአብሔር፡ መጀመሪያ፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ በመልኩ በመፍጠር፡ "ልጆቼ" ያደረጋቸው፥ ኋላም፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ወደዚሁ "ልጅነታቸው" የዋጃቸው፡ ስንቶቹ እልፍ አእላፋትና ትእልፊተ አእላፋት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚሁ፡ ከእግዚአብሔር በተወለዱበት ልጅነታቸው፡ መለኮታዊቷን ያገራቸውን መንግሥት፡ በሕዝብነት፥ በክህነትና በምሉክነት ከማገልገል ውጪ ተደርገው፡ የሰይጣን ጭዳና ሰለባ፥ ባሮችና ተገዦች፥ መንጋና ሠራዊት በመኾን፡ ጠፍተው ቀሩ?!!! እስከዛሬ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬም፡ በዚሁ ቀንበርና እሥራት ተቀፍድደው፡ የጨለማና የሥቃይ ህልውናቸውንስ፡ እንዴት ዝም ብለው የሚቀጥሉ ኾኑ?!!!

በዚህ ጠንቀኛ መዘዝ ምክንያትስ፡ እግዚአብሔርና እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የኾነችው፡ አገራችን ኢትዮጵያ፡ እኒህን፡ ሥፍር ቍጥር የሌላቸውን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን፥ ምርጦቻቸውንና አገልጋዮቻቸውን፡ ለበርካታ ሺዎች ዘመናት አጥተው የኖሩ፥ ዛሬም፡ በዚሁ እጦት፡ የቀጠሉበት መኾናቸው ሲታይ፡ እጅግ የሚያሳዝን አይደለምን?

አዎን! በዚህ ምክንያት ብቻ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ አያሌ ሺህ ዓመታትን በሚያስቆጥሩት፡ ባለፉት የነጻነት ዘመናቷ ውስጥ፡ ለህልውናዋ፥ ለአገልግሎቷና ለጽናቷ፡ ከወጣቱ ክፍልና ከሴቱ ወገን፡ በአካል ጒልበት፥ በአእምሮ ኃይልና በመንፈስ ጸጋ ረገድ፡ ምን ያህሉን ብዛትና ዓይነት አጥታ እንደኖረች፡ በቀላሉ ለመገመት፡ ለማንም አስተዋይ ተመልካች፡ ከቶ አያዳግትም፡፡

ታዲያ! ይህ ኹሉ ሊኾንና ሊደርስ የቻለው፡ የእኒሁ፡ እየራሳቸውን "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" ብለው የሚጠሩት፡ ወንዶችና ሴቶች ወጣቶች፡ የየግል ፍላጎት፥ ፈቃደኛነትና ምርጫ ስላለበት አይደለምን? እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! አኹንስ ቢኾን፡ እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ይህን፡ የክፉው ወገን የኾነውን ጎጂ ፈቃደኝነታቸውን፡ እግዚአብሔራዊ ወደኾነው፡ ወደመልካሙ ወገን፡ በንስሓ ለምን አይመልሱትም? ይህን በጎ ምግባር ለመፈጸም፡ እስከመቼ መቆየት አለባቸው? እስከምጽአተ ክርስቶስ?

ከኹሉም ይልቅ፡ በበለጠ የሚያሳዝነው፡ በወጣቶቻችን ላይ፡ ይህን አሠቃቂ ኹኔታ ያስከተለው፡ ይኸው፡ "'መርገምና ርኵሰት' የሚባለው ጠንቅ፡ አኹንም፡ ጸንቶ መቀጠል አለበት!" ብለው የሚያምኑት፡ አሪታውያኑም ኾኑ፥ ለዚሁ፡ ለሰይጣናዊው ልማድ ተገዦች የኾኑት ወገኖች፥ ሰለባዎቹ ወጣቶች ጭምር፡ አጥብቀው ይዘው የቀጠሉበት፡ የግትርነት አቋማቸው ነው፡፡

ይህ ክፉ ድርጊታቸው፡ እየቀጠለ የኼደው፡ ይኸው ጠንቅ፡ ሌላውም፡ ማናቸውም ዓይነት መርገምና ርኵሰት፡ በአምላክ እናት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ብቅዓትና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ተደምስሶ የተወገደ መኾኑን የሚያረጋግጠው፡ የምሥራቹ (የወንጌሉ) ቃል እየተነገራቸውና እነርሱም፡ ይህን እውነታ፡ በግልጽ እያወቁት ነው፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፤ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ በዘወትር ጸሎታቸው፡ በግእዙ እያነበነቡት፥ ወደኢትዮጵያኛ ተተርጉሞና ተጽፎም፡ እያነበቡት መኾኑ፡ እነሆ፡ በገሃድ ይታያል። ይኹን እንጂ፡ ይህ ኹሉ ቀና መንገድ ተዘርግቶላቸው፥ የመዳኑም ደጃፍ ተከፍቶላቸው፡ በንስሓ አለመመለሳቸው፥ ለተዘጋጀላቸው ንጽሕናና ቅድስናም፡ እየራሳቸውን ለማብቃት፡ ዛሬም፡ ፈቃደኞች አለመኾናቸው ያስገርማል።

ታዲያ! ይህን የመሰለውን አድራጎት፡ እንኳንስ፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የሚሉት ይቅሩና፡ ክርስቲያናዊ ሕሊና ያለው፡ ማንም ሰብአዊ ፍጡር፡ "ያደርገዋል!" ተብሎ፡ ከቶ፡ እንዴት ሊታሰብና በግብር ላይ ሊውል ይቻላል? ጨርሶ፡ የሚቻል አልነበረም። እነርሱ ግን፡ አኹንም፡ እያደረጉት ነው። ይኸውም፡ በዲያብሎስ ገዢነት፥ በኃጢኣት ቀንበርና በሞት ፍዳ ተይዘውና ተቀፍድደው፥ በሥቃይ ከኖሩበት፡ ከነፍስ፥ ከሥጋና ከመንፈስ እሥራት፥ ተገዢነትና ባርነት፡ ነጻ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ፥ እነርሱም፡ በአዋጅ፡ "አዎን! ወጥተናል!" ካሉ በኋላ፡ እንደገና፡ ወደዚያው፡ ወደቀድሞው እሥራታቸው፥ ተገዢነታቸውና ባርነታቸው፡ መመለሳቸው ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ ይህ ድርጊታቸው፡ "እንዘ ተአምሩ፡ ከመ አኮ በዘይማስን፡ ብሩር ወወርቅ ዘተቤዘውክሙ እምውስተ ዘኢይበቍዕ ምግባሪክሙ ዘተመጠውክሙ እምአበዊክሙ። አላ፡ በክቡር ደሙ ለክርስቶስ፡ ከመ ዘበግዕ ቅድው ወንጹሕ፡ ዘተአምረ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ወአስተርአየ፡ በደኃሪ መዋዕል፡ በእንቲአነ።"

ማለትም፡ "ረብሓ ጥቅም ከሌለው፡ ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት፡ ከከንቱ ኑሮአችሁ፡ የተዋጃችሁት (ማለትም፡ ዋጋ ተከፍሎላችሁ፡ ከዲያብሎስ ተገዢነት፡ ወደእግዚአብሔር ልጅነት የተመለሳችሁት)፡ ነውርና ጒድፍ እንደሌለው፡ እንደበግ ደም፡ በቅዱሱ የክርስቶስ መለኮታዊ ደም እንጂ፡ በብርና በወርቅ፥ በሚበላሽና በሚጠፋም ነገር እንዳልኾነ ታውቃላችሁ። እርሱም፡ ዓለም ሳይፈጠር እንኳ፡ አስቀድሞ የታወቀው፥ በዘመኑ መጨረሻም፡ ስለእኛ የተገለጠው ነው።" የሚለውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚጻረር፡ አድራጊውን፡ ለዘለዓለማዊው ፍዳ፡ በእርግጥ የሚዳርግ ነው። (፩ጴጥ. ፩፥፲፰-፳።)

ዕጣ ክፍላቸውን፡ በገዛ ፈቃዳቸው፡ በዚህ ክፉ ወጥመድ ውስጥ አስገብተው ከተያዙት ወገኖች ጋር ላደረጉት ምስኪኖችም፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ አኹንም፡ እንዲህ እያለ ይመክራቸዋል፦

"'አሆ!' በልዎ ለእግዚአብሔር። ወ'እንብየ!' በልዎ ለጋኔን፤ ወይጐይይ እምኔክሙ። ቅረብዎ ለእግዚአብሔር፤ ወይቀርበክሙ። አንጽሑ እደዊክሙ ኃጥኣን፤ ወአንጽሑ ልበክሙ፡ እለ ትናፍቁ።"

ማለትም፡ "እንግዴህ፡ እግዚአብሔርን፡ 'እሺ!' በሉት። ዲያብሎስን ግን፡ 'እምቢ!' በሉት፤ ከእናንተም ይሸሻል። ወደእግዚአብሔር ቅረቡ፤ እርሱም፡ ወደእናንተ ይቀርባል። እናንት ኃጢኣተኞች! ከባዕድ አምልኳችሁና ከክፉ ሥራችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በንስሓ አጥሩ። እናንት ወላዋዮች! ልባችሁን፡ በአንዲቷ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት አንጹ።" (ያዕ. ፬፥ ፯-፲።)

## ፫ኛ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች መኾናችን።

እናንተ እና እኛ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች (ካህናትና ምሉካን) የመኾንን ታላቅ ሥልጣንና ተልእኮን በመቀበላችን ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ የእናንተ እና የእኛ፡ የየራሳችን የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሰውነትና ሕይወት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የመገለጫ ዓለም ኾኗል። ይህ ብቻ አይደለም። እያንዳንዳችን፡ በነፍስ ወከፍ፥ በጋራም፡ ኹላችን፡ ያለጾታ ልዩነት፡ በሦስቱም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ ማለትም፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ፡ በሕዝባዊው፥ በክህነታዊውና በምሉካዊው የእኩልነትና የኃላፊነት ደረጃ፡ የምናገለግል ኾነናል።

የምናገለግለውም፡ ፈጣሪያችንንና አምላካችንን፥ ካህን፡ ሊቀ ካህናታችንንና ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ ደግሞም፡ ሃይማኖታችንንና አገራችንን፥ እናታችንንና ንግሥታችንን ድንግል ማርያምን ነው።

እናንተ እና እኛ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የኾንበትን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በተቀበልንበት፡ በጥምቀታችን ጊዜ፡ የተቀባነው ቅብዓ ቅዱስ (ሜሮን)፡ የፈጸመው ታላቅ የተዋሕዶ ምሥጢር አለ። ይኸውም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለም፡ በአንድነት የቀረብልንና የተሰጠን፥ የታወቀልንና የጸደቀልን፥ የተቀደሰልንና የታተመልን፡ የማንነታችን መለያ፥ የተልእኳችን በረከትና የሹመታችን ሥልጣን ነው።

ያም፡ እያንዳንዳችን፡ ወኖቹም፥ ሴቶቹም፡ ከእግዚአብሔር፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የተወለድነው ልጅነታችን፡ በቤተ ሕዝብነት አባልነታችን ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ በመጀመሪያውና በመጨረሻው መልከ ጼዴቆች ቃል ኪዳን ምክንያት፡ አብረው ተዋሕደው ያገኘናቸው፡ የእያንዳንዳችን ካህንነት፡ ማለትም፡ የቤተ ክህነት አባልነታችንና እንዲሁም፡ ምሉክነታችን፡ ማለትም፡ እስከአጼነትና ንግሥትነት የሚያበቃን፡ የቤተ ምልክናው ሥልጣናችን ጭምር ናቸው እንጂ።

በሥጋዊው የተፈጥሮ አካላችን፡ ተባዕትና እንስት ኾነን፡ የተፈጠርንበት፡ የወንድና የሴት ጾታችን፡ ለሥጋ ልደትና ለዘር መባዛት ሲል፡ ፈጣሪያችን ያደረገው የሥነ ፍጥረቱ ድልድልና ድንቅ ሥራው ከመኾኑ በቀር፡ በነፍስና በመንፈስ አካሎቻችንና ባሕርዮቻችን፥ በሥጋዊው ጭምር፡ በማናቸውም ሚዛንና መሥፈርት፡ የወንድና የሴት፡ እኩልነትና ትክክለኛነት የተረጋገጠ ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ፡ አንዳችም ልዩነት እንደሌለ፡ በአጽንዖት ሊታወቅ የሚገባው ቊም ነገር ነው።

እንደዚሁም ኹሉ፡ እናንተ እና እኛ፡ እያንዳንዳችን፡ በየተሰጧችንና በየሙያችን፥ በየችሎታችንና በየትምህርታችን፡ እግዚአብሔርንና ቅድስት እናቱን፡ ደስ የሚያሰኛቸውን፥ ለወገናችንና ለአገራችን የሚጠቅመውንም አገልግሎት ለማበርከት ከመኾኑም በቀር፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ወንድ፡ ሴት፥ ካህን፡ ምእመን፥ ምሉክ፡ ሕዝባዊ፥ ባለሕግ፡ መነኰስ፥ ባለትዳር፡ ባሕታዊ፥ ድንግል፡ መዐስብ በመባባል፡ መለያየትና መበላለጥ ከቶ የለም።

ይህም እውነታ፡ እንዲህ፡ በሚለው፡ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ይረጋገጣል፡-

"እስመ ኵልነ ውሉደ እግዚአብሔር ንሕነ፡ በአሚን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ። ወአንትሙሰ፡ እለ ተጠመቅህክሙ በክርስቶስ፡ ክርስቶስሃ ለበስክሙ። አልቦ፡ በዝንቱ፡ አይሁዳዊ፥ ወአልቦ አረማዊ፤ አልቦ ነባሪ፥ ወአልቦ አግዓዚ፥ <u>አልቦ ተባዕት፥ ወአልቦ አንስት። ዳእሙ፡ ኵልክሙ አሓዱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ።</u>"

ማለትም፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ በአመንበት ሃይማኖት፡ እኛ፡ ኹላችን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ነን። እናንተም፡ በክርስቶስ ስም የተጠመቃችሁ፡ ክርስቶስን ለብሳችሁታል። ከዚህ የተነሣ፡ በመካከላችሁ፡ 'አይሁዳዊ'፥ 'አረማዊ' መባባል የለም፤ 'ገዢ'፥ 'ተገዢ' መባባል የለም፤ <u>'ወንድ'፥ 'ሴት' መባባል የለም። ኹላችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንድ ናችሁ እንጂ።</u>" (ገላ. ፫፥ ፳፮-፳፰።)

እናንተ እና እኛም፡ በዘወትሩ የቃል ኪዳን ጸሎታችን ላይ፡ "በእንተዝ፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት <u>በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡</u> እንዘ በኀቤሁ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሥረ ተዋሕዶ።"

ማለትም፡ "ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ <u>በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡</u> ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።" እያልን፡ በየዕለቱ በምንሰጠው የምስክርነት ቃላችን፡ ይህንኑ እውነታ፡ ማለትም፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሰውነት"፡ ወንዶችንና ሴቶችን የሚያጠቃልለው ሰብእና መኾኑን ማረጋገጣችን እኮ ነው።

## ፮ኛ፡ <u>የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መኾናችን፡፡</u>

የእናንተ እና የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነታችን፡ <u>የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ</u> መኾኑን፡ በሃይማኖት ተረድተን፡ እየራሳችንን፡ ለዚህ ቅድስና ማብቃታችን ነው፡፡

ይህም እውነታ፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ ሰውን፡ በነፍስና በሥጋ፡ ራሱን አስመስሎ፡ በመልኩ ከመፍጠሩ ጀምሮ፡ ኋላ፡ ይኸው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ በክፋትና በአምልኮ አመንዝራነት፥ በክህደትና በዓመፅ ኃጢኣት፡ ራሱን ከፈጣሪው ቢለይም እንኳ፥ ፈጣሪ ደግሞ፡ ፍጹም አምላክነቱን፡ ከዚያው በዳዩ፡ ፍጹም ሰውነት ጋር አዋሕዶና በዚያ፡ በራሱ ትስብእት (ሰውነት)፡ የመሥዋዕትነት ካሣን ከፍሎ፡ ሰውን፡ ወደእርሱ መልሶት፡ እርሱኑ፡ ሰውን፡ እንደገና፡ በቅዱስ መንፈሱ እስከመውለድ ባደረገለት የቸርነት ሥራው፡ ገሃድ ኾኗል፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ የቀደሙት የኢትዮጵያ ልጆችና የእናንተ፥ የእኛም ሰውነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ምክንያት፡ በእውን፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ብቻ ሳይኾን፡ ጽላትና ታቦት፥ መንበርም ጭምር ኾኖ መኖሩ፡ ከፍጥረት ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬ፡ በኪዳኑ ልቦና፥ በኪዳኑ ኦሪትና በኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ እየተፈጸመ ባለው፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ሕይወትና ህልውና ተረጋግጧል፡፡

ይህንም እውነታ፡ የመንፈስ ቅዱስን ቃላት የያዙት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ እንዲህ እያሉ በሚሰጡት፡ የምስክርነት ቃላቸው አጽንተውታል፡-

"'ናሁ ይመጽእ መዋዕል፤' ይቤ እግዚአብሔር፤ ወእሠርዕ ለቤተ እስራኤል፥ ወለቤተ ይሁዳ፡ ሕገ ሓዲሰ፡፡ ወአኮ ከመ ዝንቱ ሕግ፡ ዘሠራዕኩ ለአበዊሆሙ፡፡ ...እወዲ ሕግየ፡ ውስተ ሕሊናሆሙ፤ ወእጽሕፎ፡ ውስተ ልቦሙ፡፡ ...ወኢይምህር እንከ፡ እኁ፡ እኅዋሁ፡ እንዘ ይብል፡ 'አእምርዎ ለእግዚአብሔር!' እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፤ ንኡሶሙ፤ ወዐቢዮሙ፡፡"

ማለትም፡ "'እነሆ፡ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር፡ አዲስ ከዳን የምገባበት ዘመን ይመጣል፤' ይላል እግዚአብሔር፡፡ 'ያም፡ ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ኪዳን አይደለም፡፡ ...[በአዲሱ ኪዳን]፡ ሕጌን፡ በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፡፡ ...እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ ፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና፡፡"

እንዲሁም፡ "ወአንትሙሰ፡ ሕንፃ እግዚአብሔር አንትሙ፡፡ ...ኢተአምሩኑ ከመ ታቦቱ አንትሙ ለእግዚአብሔር? ወመንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ? ወዘሰ፡ አማሰነ ቤተ እግዚአብሔር፡ ሎቱኒ፡ ያማስኖ እግዚአብሔር፡፡ ወቤቱሰ ለእግዚአብሔር አንትሙ ውእቱ፡፡ ወቅዱሳን አንትሙ፤ ወኢታርኵሱ ቤቶ ለእግዚአብሔር፡፡"

ማለትም፡ "እናንተ፡ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ! ...እናንተ፡ የእግዚአብሔር ታቦቱ እንደኾናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም፡ በእናንተ አድሮ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም፡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያበላሽ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ያበላሸዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ እናንተ ናችሁ! የእግዚአብሔር ቤቱ፡ ቅዱስ ነውና፡ እንግዲያ፡ የእግዚአብሔር ቤት የኾነውን፡ ራሳችሁን አታርክሱ!"

ደግሞም፡ "ኢተአምርኑ፡ ከመ ማኅደሩ ለመንፈስ ቅዱስ አንትሙ፥ ዘኅዱር ላዕሌክሙ፥ ዘነሣእክሙ፡ እምኀበ እግዚአብሔር? ወኢኮንክሙ ለርእስክሙ፤ በሤጥ ተሣየጠክሙ፡፡ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፡ በሥጋክሙ፡፡"

ማለትም፡ "ሥጋችሁ፡ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት፥ በእናንተ የሚኖረው፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደኾነ፡ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋል፡፡ ለራሳችሁ አይደላችሁም፡፡ ስለዚህ፡ በሥጋችሁ፡ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡"

በመጨረሻም፡ "<u>ወአኮሰ፡ ዘየኀድር ልዑል፡ ውስተ ግብረ እደ ሰብእ፤</u> እስመ ከመዝ ይቤ ነቢይ፡- 'ሰማይኒ፡ መንበርየ፤ ወምድርኒ፡ መከየደ እገርየ፤ አየኑ፥ ቤተ፡ ተሓንፁ ሊተ?' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወአየኑ መካን ውእቱ መካነ ምዕራፍየ? አኮኑ፡ እደውየ፡ ገብራ ዘኵሎ?'"

ማለትም፡ "ነቢዩ፡ እንዲህ ሲል እንደተናገረ፡- 'ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት፤ ከቶ፡ ለእኔ፡ ምን ዓይነት ቤትን ልትሠሩልኝ ትችላላችሁ?' ይላል እግዚአብሔር፤ 'የማርፍበት ስፍራስ፡ ምንድር ነው? ይህን ኹሉ ሥነ ፍጥረት፡ እጄ የሠራችው አይደለምን?' ስለዚህ፡ <u>ልዑል እግዚአብሔር፡</u> ራሱ በፈጠረው፡ በሰው አካል እንጂ፡ <u>የሰው እጅ በሠራው ሕንፃ አያድርም!"</u> (ኤር. #1÷ ፴፩-፴፬:: ዕብ. 8÷ ፰-02:: 1ኛ ቆሮ. 3÷ ፱– 07፤ 6÷ ፲፱– ":: የሓዋ. 8÷ ፵፰-%::)

## ፯ኛ፡ <u>ቤታችን፡ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ስለመኾኑ::</u>

እናንተ እና እኛ፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለኾነው ሰውነታችን፡ ማደሪያ የኾነውን ቤታችንን፡ <u>የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን</u> በማድረጋችን ነው::

አዎን! የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የኾነው ሰውነታችን የሚያድርበትና የሚኖርበት፡ የእያንዳንዳችን ቤት፡ በእርግጥ፡ "ቤተ ክርስቲያን" ነው፤ ማለትም፡ "የክርስቲያን ቤት" ነው:: ሊኾንም ይገባል:: ቀድሞውንም፡ ነበር፤ አኹንም ነው፤ ወደፊትም፡ እንዲህ ኾኖ ይኖራል::

ይህን መለኮታዊ ጸጋ፡ አኹንም እንደገና፡ በቸርነቱና በልግሥናው÷ በቤዛነቱም፡ እውን ያደረገው÷ በምሥራች ቃሉ አጽንቶና አረጋግጦም፡ ለእውነተኞቹና ታማኞቹ ምእመናኑ፡ በነፍስ ወከፍ የሰጠው÷ ራሱ፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህ እውነታ የተከሠተው፡ ዕርገቱን ተከትሎ፡ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ ከመውረዱ በፊት፡ በምድር ላይ፡ ገና እያስተማረ ሣለ ነበር::

ይኸውም፡ ሰዎች፡ እርሱን፡ ማን እንደሚሉት፡ ለማወቅ፡ ደቀ መዛሙርቱን ጠይቋቸው፡ ከቀደሙት ነቢያት፡ እንደአንዱ እንደሚቈጥሩት ከገለጹለት በኋላ፡-

"አንትሙሰኬ፡ መነ ትብሉኒ ከዊነ?" ማለትም፡ "ታዲያ! እናንተሳ፡ እኔን፡ 'ማ፡ ነው?' ትሉኛላችሁ?" ብሎ ላቀረበላቸው ጥያቄ÷

ሊቀ ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ፡- "አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር!" ማለትም፡ "አንተ፡ ቅቡዑ መሢሕ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!" ሲል ለሰጠው ምላሽ፡ ጌታችን፡ የተናገረው ቃሉ መኾኑን፡ እንዲህ የሚለው ጥቅስ ይመሰክራል፡-

"ብፁዕ አንተ ስምዖን ወልደ ዮና! እስመ ኢከሠተ ለከ፡ ዘሥጋ ወደም፤ አላ፡ አቡየ ዘበሰማያት:: ወአንሰ እብለከ፡- ከመ አንተ ኰኵሕ፤ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ፡ አሓንፃ ለቤተ ክርስቲያንየ:: ወአናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ:: ውእሁበከ መራኁተ መንግሥተ ሰማያት:: ወዘአሰርከ በምድር፡ ይከውን፡ እሱረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕከ በምድር፡ ይከውን፡ ፍቱሓ በሰማያት::"

ማለትም፡ "የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ! ይህን እውነት የገለጸልህ፡ የሰማዩ አባቴ እንጂ፡ ሥጋዊውና ደማዊው፡ ሰውነትህ አይደለም:: እኔም እልሃለሁ፡- <u>አንተ፡ ዓለት ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ::</u> የሲኦል ደጆችም አይችሏትም:: የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ:: በምድር ያሰርከው፡ በሰማያት የታሰረ ይኾናል፤ በምድር የፈታኸውም፡ በሰማያት የተፈታ ይኾናል::" (ማቴ. 06÷ ፵፰-%::)

ዘለዓለማዊው መምህራችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው፡ ይህ፡ የአዋጅ ቃል፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረበት፡ በልቡ ጽላት ላይ በመንፈስ ቅዱስ ጣቶች፡ የተጻፉትን፡ እኒህን ቅዱስ ጴጥሮስ የተናገራቸውን የሃይማኖት ማረጋገጫ ሕያዋን ቃላት፡ ከእውነተኛ መንፈሳዊ ልቦናው አፍልቆ፡ በአንደበቱ ሲያስሰማና በይፋ ሲመሰክር፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ለእርሱ÷ ለእርሷ ተነግሮ የሚሰጥ፡ መለኮታዊ የሹመት ሥልጣን ነው:: ይህ ብቻ ሳይኾን፡ ለዚህ ሰብአዊ ፍጡር፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ በእግዚአብሔር መልክ ከመፈጠሩ ታላቅ ክብር ጀምሮ፡ እናንተን እና እኛን፡ የእግዚአብሔር ልጆች÷ የመንግሥቱ ወራሾችና አገልጋዮች እስከመኾን ድረስ ያበቁን፡ ሌሎቹ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ኹሉ ጭምር፡ ያለጾታ÷ ያለዘርና ያለቀለም ልዩነትና አድልዎ ይሰጡታል::

እኒህ የአምላክ ስጦታዎች፡ <u>"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነው!"</u> ብሎ ለሚያምን ሰው ኹሉ የተለገሡ ናቸው። ይህ የሃይማኖትና የምግባር፥ የህልውናም ሥርዓት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከዛሬ፡ ለ7ሺ፭፻፩ ዓመታት ጸንቶ የኖረ አቋም ነው።

እንዲህ በመኾኑ ነው እኮ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊዉና ኢትዮጵያዊቷ፡ እንደዚያ፡ "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" እንደተባለው፡ እንደአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ ባኮስ ኹሉ፡ ይህን የሹመት ጸጋ ስለተቀዳጁ፡ ከየራሳቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነት አልፈው ተርፈው፡ ቤታቸውንም፡ ለቤተ ክርስቲያንነት ለማብቃት የቻሉት።

ይህን እውነታ፡ በትክክል ለመገንዘብ፡ በአንድ ወገን፡ በመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ዘንድ የነበረውን ተቀዳሚ የክፋት፥ የጥፋትና የሞት አካኼድ፥ በኹለተኛው ወገን ደግሞ፡ በመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን፡ ማለትም፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ፡ በመደምደሚያ የተፈጸመውን የደግነት፥ የልማትና የሕይወት ፍሬ አገናዝቦ ማነጻጸርና ማመዛዘን ያስፈልጋል።

ለመኾኑ፡ በእኒህ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በተናገራቸው ቃላት፡ በልቡ የማያምንና በቃሉ የማይመሰክር፥ በምግባርም የማይፈጽም፡ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ምእመን ሊኾን ይችላልን? ሊባልስ፡ ከቶ ይቻላልን? አይቻልም። ታዲያ፡ እንዲህ ከኾነ፡ በዚህ የልቡና ሃይማኖቱና የምስክርነት ምግባሩ፡ ቅዱስ ጴጥሮስን ኾኖ፥ ወይም፡ መስሎ የተገኘ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፥ ወንድ ኾነ ሴት፡ ለዚያ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ መልስ ኾኖ ለተሰጠው፡ ለመለኮታዊው የሹመት ሥልጣንና ማዕርግ የማይበቃበት፡ ምን ምክንያት አለ? ምንም የለም።

"ያ የጌታ ቃል፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ የተነገረ፥ ሹመቱም፡ ለእርሱ ብቻ የተሰጠ ነው!" ብሎ የሚያምን ካለ፡ እርሱ ኢትዮጵያዊ አይደለም። ይህ ግለሰብ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ከኦሪታውያንና ከሰዎች ሥርዓት ነጻ ወጥቶ፡ በእግዚአብሔር ሥርዓት መኖርን "እምቢ!" ብሎ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ያመፀ፥ ቅዱሱን ኪዳን የካደና በቅዱሱ ኪዳን የአምልኮ አመንዝራነትን የፈጸመ መኾን አለበት።

የዚህ፡ የሰዎች ወጥመድና የዚህ የክፉዎች ቀንበር ሰለባ የኾነ ሰብአዊ ፍጡር፥ ወይም፡ ኢትዮጵያዊ ካለ፡ ከዚህ በታች የተጠቀሰው፡ ያ፡ የመለኮታዊው መምህራችን ቃል የሚጸናበት መኾኑን ሊያውቀው ይገባል፤ ይኸውም፡ በዘመኑ የነበሩት የአይሁድ ቤተ ክህነትና ቤተ ሕዝብ፡ ትምህርቱንና ምክሩን ባለመቀበል፡ ከአረማዊው፡ የሮም ቤተ ምልክና ጋር በመመሣጠር፡ ለክብራቸውና ለሥልጣናቸው፥ ለጥቅማቸውና ለገንዘባቸው ሲሉ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት እያፈረሱ፡ የራሳቸውን ሰው-ሠራሽ ወግ፡ በሥራ ላይ ማዋልን ስለቀጠሉ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስለማቸው፡ እንዲህ የሚለው፡ የተግሣፅና የዘለፋ ቃል ነው።

"ወሰዓርክሙ ቃሎ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ሥርዓትክሙ። አ መደልዋን! ሡናየ ተነበየ ኢሳይያስ ላዕሌክሙ፤ እንዘ ይብል፡- 'ዝ ሕዝብ በከናፍሪሆሙ ያከብሩኒ፤ ወበልቦሙሰ ነዋኅ ይርኅቁ እምኔየ። ወከንቶ ያመልኩኒ፡ እንዘ ይሜህሩ ትምህርተ ሥርዓታተ ሰብእ።'"

ማለትም፡ "ለሰብአዊው ሥርዓታችሁ ስትሉ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ፤ እናንተ ግብዞች! ነቢዩ ኢሳይያስ፡ በእናንተ ላይ እውነተኛውን ትንቢት ተናገረ፤ እንዲህ ሲል፡- 'እኒህ ሕዝብ፡ በከንፈራቸው ያከብሩኛል፤ በልባቸው ግን፡ ከእኔ እጅግ የራቁ ናቸው። "የሰውን ሥርዓቶች ብቻ ተከተሉ!" የሚለውን ትምህርት እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል።" (ማቴ. 05፥ ፩-0።)

እንግዴህ፡ እናንተ እና እኛ፡ የዛሬዎቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚህ፡ በምንኖርበት የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን፡ እየራሳችንን፡ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ"፥ ቤታችንንም፡ "ቤተ ክርስቲያን" አድርገን፡ ፈጣሪያችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱና ከቅዱሳን ባለሚሎቹ ጋር የሚፈቅደውንና የሚወድደውን፥ ያዘዘውንም፡ የአምልኮ ሥርዓታችንን፡ "በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ" እያካኼድን መፈጸማችን ስለኾነ፡ ለየራሳችን፡ ደስ ሊለን፥ ለቸሩ አምላካችንም ምስጋናችንን ልናቀርብ ይገባናል።

ዕጣ ፈንታችን ኾኖ፡ ይህን ከመሰለው ዘመን በምንደርስበት ጊዜ፡ በምን ዓይነት ሥጋዊ መሰናዶና መንፈሳዊ ትጥቅ ተዘጋጅተን ልንገኝ እንደሚገባን፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በየአጋጣሚውና በየምክንያቱ፡ እንዲህ አድርጎ፡ አስቀድሞ ነግሮናል። የአምልኮ ሥርዓታችንን፡ በዚህ መልኩ እያካኼድን ለመፈጸም የምንችልበትን፡ ይህን መለኮታዊ ጸጋ፡ ፈጣሪያችን፡ ቀድሞውንም ባይሰጠን ኖሮ፥ ኋላም፡ እርሱው፡ በትስብእቱ፡ ማለትም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሰውነት ተወልዶ፡ በመስቀል ላይ በፈጸመው ቤዛነቱ አጽንቶት፡ እንዲቀጥል ባያደርግልን ኖሮ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ታማኞች ኾነን የቀጠልነው እናንተ እና እኛ፡ የዛሬዎቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከቶ፡ ምን ይበጀን ነበር?

"ኧረ ለመኾኑ፡ መፍትሔው፡ ይህ፡ ከላይ የተገለጸው ብቻ ኾኖ፡ ሌላ አማራጭ የሌለውን፡ ይህን፡ ጠንቀኛ ችግር ያመጣው፡ ከቶ ምንድር ነው?" የሚል ጥያቄ፡ እዚህ ላይ፡ ቢነሣና ቢቀርብ፡ አግባብ ይኾናል። የዚህ ጥያቄ መልስ፡ በመጠኑም ቢኾን፡ ሲብራራ፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል ይጠቃለላል፡-

"ዛሬ ያለው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፥ ባለፉት ዘመናት፡ አልፈው አልፈው እንደተነሡት ተመሳሳይ ትውልዶች ኹሉ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በይፋ በፈጸመው፡ የክህደት፥ የዓመፅና የምንዝርና ኃጢአት ምክንያት፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፡ በሰው በኩል የፈረሰበት፥ ከዚህ የተነሣም፡ ሰብአዊዉና ሰይጣናዊው ኃይል፡ የሰፈነበት ዘመን መኾኑ፡ እነሆ፡ በገሃድ ይታያል፤ ከዚህ የተነሣ፡ ጊዜው፡ ክህነትና ካህን የታጣበት፥ እውነተኛው አምልኮ ሊፈጸምበትና አማናዊው መሥዋዕት ሊቀርብበት የሚቻልበት፡ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን፥ ወይም፡ "መካነ አምልኮ" የሌለበት፥ እንዲሁም፡ በአገራችን ውስጥ ኾነ፡ በውጪው ዓለም፡ ግዞትና ውግዘት፥ እሥራትና ስደት፥ ሞትም የጸናበት ስለኾነ ነው።"

ስለዚህ፡ ከላይ ከተገለጸው በቀር፡ ሌላ ማማረጫ የሌለውን፡ ይህን፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚነካውን፥ የጊዜያችን፡ ከባድና አሳሳቢ የኾነውን፡ ጠንቀኛና መዘዘኛ ችግር ተቋቁሞ ለማስወገድ፡ የፈጣሪያችንን ጸጋና ሥርዓት በመከተል፡ የእያንዳንዳችንን፡ የእውነተኞቹንና የታማኞቹን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን ቤት፡ ለየቤተሰቡ፡ በቤተ ክርስቲያንነት እንዲያገለግል ላደረገው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ውሳኔያችን፡ መነሻ ምክንያት ኾኗል።

ትውልዱ፡ ወደፊት፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሶ፡ በእግዚአብሔራዊው፡ የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት በሚያደራጃቸው፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው አቋሞቹ አማካይነት መተዳደርን የሚመርጥበት ቀን ሲመጣ፡ በዚያን ጊዜ፡ በዘወትሩ የሃይማኖት ጸሎታችን በምናዘክራት፡ በአጠቃላይዋ ቤተ ክርስቲያናችን ተሰባስበን፡ የአምልኮ ቍርባናችንን፡ በአንድነት ለማቅረብና ለመፈጸም ይቻለናል። ያችም፡ አጠቃላይዋ ቤተ ክርስቲያናችን፡ "ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፥ በኪዳነ ልቦና ዘአበው ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ በላዕለ ኵሉ ጉባዔ ዘሐዋርያት። በውስቴታ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ።"

ማለትም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንት፡ በቀደሙት አበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና ከኹሉ በላይ በኾነችው፡ በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ ካህናት፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባት፥ ምእመናንም፡ የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ልዩ ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።" እያልን፡ በዘወትሩ የሃይማኖት ጸሎታችን የምናዘክራት ናት።

እስከዚያች ቀን ድረስ ግን፡ እናንተ እና እኛ፡ መለኮታዊው መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ወዓዲ እብለክሙ፥ ለእመ ኀብሩ ክልኤቱ አው ሠለስቱ እምኔክሙ በውስተ ምድር፡ በእንተ ኵሉ ግብር ዘኀሠሡ፥ ይትገበር ሎሙ፡ በኀበ አቡየ ዘበሰማያት፤ እስመ ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ ወሠለስቱ ጉቡአን በስምየ፥ ህየ ሀለውኩ አነ ማእከሎሙ።"

ማለትም፡ “ዳግመኛም እላችኋለሁ፥ ከእናንተ፡ ኹለታችሁ፥ ወይም፡ ሦስታችሁ፡ በምድር ላይ፡ ተስማምታችሁ፡ ስለማናቸውም ነገር ብትጠይቁ፡ ከሰማዩ አባቴ ዘንድ ይደረግላችኋል፤ ኹለት፥ ወይም፡ ሦስት፡ በስሜ በተሰበሰቡበት፡ በዚያ፡ እኔ፡ በመካከላቸው እገኛለሁና።” ያለውን፡ ሕያው መመሪያውን፡ በሃይማኖት ተቀብለንና ተከትለን፥ በምግባር እየፈጸምን፥ በመንፈስ ቅዱስና በእውነተኛው አምልኳችን አማካይነት፡ እርሱን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ካህናችንና ገባሬ ሠናይ ቄሳችን፥ ቅድስት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ መሠዊያ ታቦት መንበራችን አድርገን፡ ሥርዓተ ቅዳሴያችንን ጭምር እያካኼድን፡ እነሆ፡ ተልእኳችንን እንደቀጠልን እንገኛለን። (ማቴ. ፲፰፥ ፲፱-፳።)

ከእውነተኛነቱና ከመንፈስ ቅዱሳዊነቱ፡ ቅንጣት ጒድለት ያለበት አምልኮ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ የሓሰት (የውሸት) ስለኾነ፥ ይህም የሚስማማው፡ ራሱ፡ “ሓሰት” ኾኖ፡ “የሓሰት አባቷ” ለተባለው፡ ለዲያብሎስ ብቻ ስለኾነ፡ ይህን ዓይነቱን አምልኮ እንደማይቀበለው፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ ሰው ከመኾኑም በፊት፥ ሰው ከኾነም በኋላ፡ እንዲህ ሲል፡ በቃሉ አረጋግጦ ነግሮናል፤ አስተምሮናልም።

“እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን፡ ይሰግዱ ለአብ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ፤ እስመ አብኒ፡ ዘከመዝ የኀሥሥ፡ እለ ይሰግዱ ሎቱ። እስመ እግዚአብሔር መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ፡ ሀልዎሙ ይስግዱ ሎቱ።”

ማለትም፡ “በቀናች ሃይማኖት ኾነው፡ እግዚአብሔር አብን፡ የሚያመልኩት ኹሉ፡ አምልኳቸውን የሚፈጽሙት፡ በመንፈስና በእውነት ነው፤። እግዚአብሔር አብ፡ የሚያመልኩት ኹሉ፡ እንዲህ፡ በመንፈስና በእውነት እንዲያመልኩት ይሻልና። እግዚአብሔር መንፈስ ስለኾነ፡ የሚያመልኩት፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ይገባቸዋል።” (ዮሐ. ፬፥ ፳፫-፳፬።)

በዚህ መለኮታዊ ቃሉ፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ እያንዳንዳችን፡ በግል፥ በማኅበርም፡ ኹላችን፡ ከእርሱ ጋር የሚያገናኘንን የአምልኮ ሥርዓት፡ እንዴት አድርጎ እንዳቃለለልን፡ እናንተ እና እኛ፡ በጥልቅ እንዳስተዋልነው እናምናለን። ይኸውም፡ አምልኳችን፡ በመንፈስና በእውነት ብቻ እንዲካኼድና እንዲፈጸም ማድረጉ ነው።

የኋላ ኋላም፡ በእርሱ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የተተካውን፡ የእንስሳትን ሥጋ በማረድና ደምን በማፍሰስ፡ ለእግዚአብሔር ይቀርብ የነበረውን፡ የኦሪቱን የምሥዋዕት አቀራረብ እንኳ፡ በስንዴ ኅብስትና በወይን ጭማቂ ብቻ እንዲዘጋጅ በማድረጉ፡ እጅግ ከባድ የነበረውን ሥርዓት እንዴት እንዳቃለለው አውቀነዋል።

ይህም ማለት፡ ኹሉም የሚኾነው፡ ሲቻልና ሲያመች እንጂ፡ አለዚያ፡ ሳይቻልና ሳያመች ሲቀር፡ እንደኦሪቱና ዛሬም፡ በክርስትናው የአምልኮ ሥርዓታችን እንደሚታየው ሳይኾን፡ ምንም ዓይነት፡ ግዙፍ ነገር፡ ማለትም፡ ጽላትና ታቦት፥ መንበርና ቤተ መቅደስ፥ ካህንና ቤተ ክርስቲያን፥ መሥዋዕትና ቊርባን፥ ሥዕልና መስቀል፥ መብራትና ማዕጠንት፡ የመሳሰሉት ንዋያት ቅድሳት እንኳ ሳያስፈልጉን፥ ቦታም፡ ሳይወስነን፡ በማናቸውም ሥፍራና ኹኔታ፡ አምልኳችንን፡ በቀላሉ ልናካኺድና ልንፈጽም እንድንችል ማድረጉን፡ እናንተም፥ እኛም፡ እንዳስተዋልነው እሙን ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪው ጋር ያለውን የአምልኮ ግንኙነት ለማካኼድና ለመፈጸም፡ በእውነት ከፈለገ፡ የሚከለክለውና የሚያዳግተው፥ ወይም፡ የሚያስቸግረውና የሚከብደው፡ አንዳችም ምክንያት የለም ማለት ነው። እግዚአብሔር፡ ከሚያመልከው፡ ከእያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውና የሚጠይቀው፡ አንዲት ነገርን ብቻ ነው፡- ያችም፡ አምልኮቱ፡ በእርሱ፡ በአምላኪው በኩል፡ በእውነት እንዲቀርብ ነው። በዚህ ጊዜ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ በቅዱስ መንፈሱ ይገኝለታል።

እንግዲህ፡ እግዚአብሔር፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ለእርሱ የሚያቀርብለትን አምልኮት፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ እጅግ አቅልሎ የሠራለትን ሥርዓት፡ ሰዎች ደግሞ፡ በየበኩላቸው፡ እንዴት አድርገው እንዳከበዱበት፡ መመልከቱ፡ ለማንም አያዳግትም። ስለዚህ፡ ኹሉም፡ ይህን አውቆና ተረድቶ፡ በአምልኮቱ ረገድ፡ ምንም ዓይነት ምክንያት ሳይፈጥር፡ በየራሱ፡ ተገቢውን መፈጸም እንዳለበት ሊገነዘበው ይገባል።

ለዚሁ፡ ለእውነተኛው ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ እያንዳንዳችን፡ በግል፥ ኹላችንም፡ በማኅበር፡ የምናቀርበው አምልኮ፡ የእውነት፥ ወይም፡ የሓሰት መኾኑን ደግሞ፡ የየራሳችን ሕሊና፡ ራሱ እንዲነግረን ስላደረገ፡ ሌላ አስተማሪ አያስፈልገንም።

ካለፉት የኢትዮጵያ ትውልዶች መካከል ብዙዎቹና ዛሬ ያለው፡ ራሱን፡ "ኢትዮጵያዊ" ብሎ የሚጠራው ትውልድ ጭምር፡ ኹሉም፡ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው አምልኮ፡ እውነተኛና ትክክለኛ አለመኾኑን፡ በገሃድ ያሳየውና የሚያሳየው፥ ያስረዳውና የሚያስረዳው፥ የመሰከረውና የሚመሰክረው፥ ያሳመነውና የሚያሳምነው፡ የያንዳንዳቸው፡ ምድራዊና ሥጋዊ ህልውናቸው ያበቃውና የሚያበቃው፡ ምንጊዜም፡ በሰዎች ደም መፍሰስ መኾኑ ነው። የሰዎች ደም እንዲፈስስ፡ "ሥራዬ!" ብሎ የሚፈልገውና የሚደክመው ደግሞ፡ ዲያብሎስ ብቻ ነው።

መለኮታዊ ዓላማውና ዕቅዱ፡ ጥንትም ኾነ፡ ኋላ፥ ዛሬም ቢኾን፡ ፍጥረቱን ማዳን ብቻ የኾነው፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔርማ፡ ለፍጥረቱ ደኅንነት ሲል፡ ሰው ኾኖ ራሱን፡ ከመሠዋት አልፎ፡ በቃሉ ያበሠረን፡ በእርሱ ዘንድ፡ እንኳንስ የሰው ደም እንዲፈስስና ሕይወቱን እንዲያጣ ይቅርና፡ የእያንዳንዳችን፡ የራስ ጠጕር እንኳ፡ የተቈጠረችና የተጠበቀች መኾኗን ነው። (ማቴ. ፲፥ ፳፰-፴፩።)

የእግዚአብሔር መንግሥት ብለን የምንኖርባትና የምናገለግላት አገራችን ኢትዮጵያ፡ በዚህ ረገድ፡ በእምነቷም ኾነ በአምልኮዋ፥ በአመራርዋም ኾነ፡ በአስተዳደርዋ፡ የምትከተለው፡ ቀዳሚና ጥንታዊ ሥርዓት እንዳላት፡ እናንተም፥ እኛም፡ እናውቃለን። ይኸውም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደበት ሰውነቱ፡ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ፡ እነሆ፡ በየጊዜውና ባለማቋረጥ፡ እርስ በርስ በመጋደልና በመተላለቅ፡ የሚፈስሰውን፡ ሰብኣዊዉን ደም ብቻ ሳይኾን፡ ለ"መሥዋዕት" እየተባለ፡ የሚቀርበውን፡ እንስሳዊዉን ደም ጭምር እንኳን፡ በራሱ ተቤዥቶ፡ ያስቀረበት፡ መለኮታዊ ሥርዓቱ ነው።

ስለዚህ፡ ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ይህን፡ የእርስ በርስ ደም መፋሰስና የመተላለቅ ልማዱን አስወግዶ፡ ፈጣሪው፡ እግዚአብሔር፡ በቅድስት እናቱ አማካይነት የገባለት፡ መልካሙ የቅዱሱ ኪዳን ምሕረት ይመጣለት ዘንድ፡ ከኹሉ አስቀድሞ፡ ከዚሁ፡ ከቃል ኪዳን አምላኩ ጋር፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ መታረቅ ያስፈልገዋል። ለዚህ፡ ፍጹም መለኮታዊ ዕርቅ ደግሞ፡ በተከታይ የሚያፈልገው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተመሠረተና ያን የተከተለ፡ የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኮውን ማስተካከል፥ አስተካክሎም መፈጸም ይኖርበታል።

ይህ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ በብርቱ አስፈላጊ የኾነበት ምክንያት፡ "አነ ውእቱ፡ እግዚእ እግዚአብሔር አምላክከ! ኢታምልክ ባዕዳን አማልክተ፤ ወኢምንተኒ፡ ዘእንበሌየ። እስመ አነ፡ እግዚእ እግዚአብሔር አምላክከ፡ አምላክ ቀናኢ፥ ዘእፈዲ ኃጢኣተ አብ፡ ላዕለ ውሉድ፥ እስከ ሣልስ፥ ወራብዕ ትውልድ፡ ለእለ ይጸልኡኒ። ወእገብር ምሕረተ፡ ለዐሥርቱ ምዕት ትውልድ፡ ለእለ ያፈቅሩኒ፥ ወለእለ የዐቅቡ ትእዛዝየ፥ ወሕግየ።"

ማለትም፡ "አምላካችሁ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር ነኝ። እኔን ከማምለክ በቀር፡ ሌሎች ባዕዳን አማልክትን ማምለክን፡ ፈጽማችሁ አታስቡት፤ አታድርጉትም! በሚጠሉኝ ዘንድ፡ የአባቶችን ኃጢአት ፍዳ፡ እስከሦስትና አራት ትውልድ ድረስ፡ በልጆች ላይ የማደርስ፥ በሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንና ሕጌን በሚጠብቁት ዘንድ ግን፡ እስከሺህ ትውልድ ድረስ፡ ምሕረትን የማደርግ፡ ፈጣሪያችሁ፡ እኔ እግዚአብሔር፡ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።" ብሎ ያስጠነቀቀን፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር፡ መመለክ የሚፈልገውና የሚወድደው፡ በእውነት መንፈስ እንጂ በሓሰት (በውሸት) መንፈስ ባለመኾኑ ነው። (ዘጸአ. ፳፥ ፩-፮።)

በዚህ ረገድ፡ እናንተ እና እኛ፡ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገን፡ ፈጣሪያችንንና አምላካችን የኾነውን፡ አንድ፡ እርሱን፡ እግዚአብሔርን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ማምለክ ብቻ ሳይኾን፡ እርሱንና ቅድስት እናቱን፡ በሥጋችንም፥ በነፍሳችንም፥ በመንፈሳችንም ለማገልገል፡ ሰውነታችንን፡ የእርሱ ቤተ መቅደስ፥ ቤታችንን፡ የእርሱ ቤተ ክርስቲያን፥ እየራሳችንንም፡ የእርሱ ካህናትና ምሉካን ለማድረግ በመቻላችን፡ አዎን! እጅግ ከፍ ያለ ኹለንተናዊ እርካታና ደስታ ሊሰማን፥ ከዚህ የተነሣም፡ "የምሥራች!" ልንባባል ይገባል።

## ክፍል ኹለት

ከላይ፡ በተጠቃቀሱት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃላትና ባጫጭር ሓተታዎች ተገልጸው በተዘረዘሩት ቊም ነገሮች መሠረት፡ እናንተ እና እኛ፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ እየራሳችንን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት በማብቃታችን፡ እያንዳንዳችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፈጣሪነትና አምላክነት፥ ካህን፡ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥትነት፥ ደግሞም፡ በድንግል ማርያም ሃይማኖትነትና አገርነት፥ እናትነትና ንግሥትነት በምትመራው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ የእግዚአብሔር ካህናትና ምሉካን፥ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶችም ኾነን፥ ቤታችንንም፡ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አድርገን የምንገኝበትን የህልውና ዓይነት አውቀናል።

እንዲህ ከኾነ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን ስፍነትና መስፋፋት በሚመለከት፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ደርሶና እየደረሰ፥ ተፈጽሞና እየተፈጸመ፥ ኾኖና እየኾነም ያለውን ትንግርታዊ የአዝመራ መከር፡ እስኪ፡ እናንተ እና እኛ፡ በማስተዋል እንመልከተው!

ይህም፡ የብሉዩ ኪዳን፡ ነቢዩ ኤልያስ፡ ፈጽሞ ተስፋ በመቊረጥ፡ ሊገድሉት ከሚያሳድዱት ተቃዋሚዎቹ ሸሽቶ፡ በአንድ ዋሻ ለብቻው ተቀምጦ ሳለ፡ በፈጣሪውና በእርሱ መካከል ከተካኼደው፥ በተስፋው እንዲጸናና እንዲበረታታም ለማድረግ፡ ከደረሰለት የረድኤት ኹኔታ ጋር፡ ተመሳሳይነት ያለው በመኾኑ፡ ስለዚያ ኹኔታ የሚገልጸውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ እንደሚከተለው ጠቅሰነዋል፡-

"ወመጽአ ቃለ እግዚአብሔር ኀቤሁ፤ ወይቤሎ፡ 'ለምንት መጻእከ ዝየ፡ ኤልያስ?! ወይቤ፡ 'ቀኒአ ቀናእኩ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ። እስመ ኀደጉ ሕገከ ደቂቀ እስራኤል፤ ምሥዋዒከኒ ነሠቱ፤ ወቀተሉ ነቢያቲከ በኲናት፤ ወተረፍኩ አነ ባሕቲትየ፤ ወየኃሥሥዋ ለነፍስየ፡ ከመ ይንሥእዋ።' ወይቤሎ እግዚአብሔር፡ ...'ወአትረፍኩ፡ ሰብዐ ምእተ ብእሴ፥ ኵሎሙ እለ ኢሰገዱ ለበኣል፤ ወኵሉ አፍ ዘኢያምለኮ።'"

ማለትም፡ "'ኤልያስ ሆይ! በዚህ ምን ታደርጋለህ?' የሚል የእግዚአብሔር ድምፅ ወደእርሱ መጣ። እርሱም፡ 'ለፍጥረቱ ኹሉ አምላክ ለእግዚአብሔር፡ እጅግ ቀንቻለሁ፤ የእስራኤል ልጆች፡ ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፤ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፤ ነቢያትህንም ገድለዋልና። እኔም፡ ብቻዬን ቀርቻለሁ፤ ነፍሴንም ሊወስዷት ይሻሉ።' አለ። እግዚአብሔርም አለው፡- '...እኔ፡ ከእስራኤል መካከል፡ ጒልበታቸውን፡ ለበኣል ያላንበረከኩትን ኹሉ፥ አንደበታቸውም ጣዖትን ያላመለከውን ኹሉ፡ ሰባት ሺህ ሰዎች፡ ለእኔ አስቀርቻለሁ።'" (፩ነገ. ፲፱፥ ፱-፲፰። ሮሜ ፲፩፥ ፩-፯።)

እነሆ፡ ያ፡ ለእውነተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር፡ ቀናተኛ ለነበረው ነቢይ፡ እንዲህ ሲል የተናገረ ፈጣሪ፡ ዛሬም፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና በሠራዒው መንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በእናንተና በእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሰውነት ላይ ያስገኘው፡ ዘለዓለማዊው የመከር አዝመራ፡ እንግዴህ፡ ይህ ነው።

በዚህ መልኩ፡ ከየራሳችን ጀምረን ስንቆጥር፡ በአኹኗ ሰዓት፡ እኛ የማናውቃቸው፥ እግዚአብሔር ግን፡ ለራሱ አስቀርቶ፥ በሕይወት መጽሐፉም ውስጥ መዝግቦ የሚያውቃቸው፡ በአገራችን በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ተበትነው የሚገኙ፡ ሥፍር ቊጥር የሌላቸው፡ ስንት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ይኖራሉ? እልፍ አእላፋት? የቊጥሩን ልክ፥ የብዛቱን መጠን፡ እናንተ እና እኛም፥ ሌላውም፥ ማንም የሚያውቀው የለም። የሚያውቀው፡ ራሱ፡ መዝጋቢው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፤ ምናልባት፡ ቊጥሩ፡ ወደፊት፡ በጊዜው ተገልጦ እስኪታወቅ ድረስ።

ለመኾኑ፡ ቊጥራቸው እንዲታወቅ የተፈለገው፡ እኒህ፡ እነማን ናቸው? እነዚህማ፡ የፈጣሪያችንና የቅድስት እናቱ ቃል ኪዳን የኾነውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸውን ሳያፈርሱ አጽንተው የያዙ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ናቸው።

እነርሱም፡ እግዚአብሔር፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ሊመለክባቸው የሚሻውን፡ የየራሳቸውንና የሌሎችን ሰውነት፡ በክህደትና በዓመፅ፥ በምንዝርናም ሳያረክሱ፡ በቅድስና አክብረው የጠበቁ፥ ሊገድሏቸው ከሚያሳድዷቸው፡ ከሓሰተኞቹ ነቢያት፡ ራሳቸውን ለይተው፡ በእየራሳቸው ሰውነት ቤተ መቅደስነትና በየቤታቸው ቤተ ክርስቲያንነት፡ በኹለንተናቸው ባደረው፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመሩት ናቸው፡፡ እነዚህም፡ ደስ ይበላችሁ! እናንተ እና እኛ ነን፡፡

የእግዚአብሔሩ እውነታ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የሚገኙት፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን አማኞችና ልጆች፥ ካህናትና ምሉካን፥ ቤተ መቅደሶችና ቤተ ክርስቲያኖች ስንት ሊኾኑ ነው? ግምቱ፡ ለእያንዳንዳችን ቢተውም እንኳ፡ ትክክለኛው የቍጥሩ ልክ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ተመዝግቦ የሚታወቀው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የሕይወት መጽሓፍ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

በዚህም፡ ዕፁብ ድንቅ በኾነው፡ የመለኮት ጥበብ፡ በኢትዮጵያ ምድር፥ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ለ፯ሺ፭፻፩ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ አንድ) ዓመታት፡ በይፋ ሰፍና የኖረችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በአኹኑ ዘመን ደግሞ፡ እንዲሁ፡ በመላው ዓለምም መስፈኗን፡ እነሆ፡ በይፋ አረጋግጣ ማሳወቋን እናበሥራለን፡፡

እንግዴህ፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ፍላጎታቸውና ዕቅዳቸው፥ ውጥናቸውና ሥራቸው፥ ጥረታቸውና መሥዋዕትነታቸው፡ እንዲህ፡ እናንተ እና እኛ፡ ዛሬ ኾነን እንደተገኘነው፡ ኾነን እንድንገኝላቸው መኾኑን እናውቃለን፡፡ ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እናንተ እና እኛ፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለን፡ በዓለሙ ኅብረተሰብ መካከል፡ በፍጹም ደስታ የምንኖረውን፡ ይህን፡ የህልውና ኹኔታችንን ሲመለከቱ፡ እናትና ልጁ፡ ምንኛ ደስ ይላቸው?

ደስ የሚላቸውም እኮ፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ለዚህ ደስታቸው፡ አዎን! በቂ ምክንያት አለ፡- ድካማቸውና ጥረታቸው፥ መሥዋዕትነታቸውና ቤዛነታቸው፡ ከንቱ ኾኖ ሳይቀር፡ የሚፈልጉትና የደከሙበት፥ የተሠዉለትና የተቤዡት፡ ያ፡ የተቀደሰው ሕያው ዓላማቸው፡ ዛሬ፡ በእናንተ እና በእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ማንነታችንና ምንነታችን ተፈጽሞላቸው፡ ያን፡ እናንተ እና እኛ የምንመገበውን፡ ጣፋጩን ፍሬ ስላስገኘላቸው ነው፡፡

ይህ ጣፋጭ ፍሬ ሊመረት የተቻለው ደግሞ፡ እንዲያው፡ በቀላል ድካምና ጥረት፥ መሥዋዕትነትና ቤዛነትም አይደለም፤ አለመኾኑንም ለመረዳት፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በቍጥብ ለቀረቡት መጠይቆች፡ መልስ በመስጠት፡ መገንዘብ ይቻላል፡-

- እንዲያው ስናስበውና አተኵረን ስንመለከተው፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ በራሱ መልክና "ሰው፡ ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" ባሰኘን፡ በሥላሴ ብቅዓት ለፈጠረን፡ ለእናንተ እና ለእኛ፡ ሰብአውያን ፍጡሮቹ፡ በቅድሚያ፡ ይህን ፍጥረተ ዓለም አዘጋጅቶ፡ በገነት ተድላ ያስቀመጠን፡ ለምን ኖሩዋል?

- ከመጀመሪያውስ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የመኾንን፡ የመጨረሻውን የክብር ዘውድ ያቀዳጀን ለምን ነበር?

- ይህ ኹሉ ቸርነት የተደረገለት ሰብአዊው ፍጡር፡ "የሰው ልጆች" በተባሉት የዘር ግንዶቹ አማካይነት፡ በገዛ ፍላጎቱና ምርጫው፡ ያን የመሰለውን፡ የልዕልና ማዕርጉን፡ አሽቀንጥሮ ጥሎ፥ ከዲያብሎስ የባርነት አገዛዝ፥ ከኃጢኣት ጽኑ ቀንበርና ከሞት የፃዕር ፍዳ የተነሣ፡ ከህልውናው፡ ጨርሶ ሊደመሰስ በተቃረበበት፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ምሳሌ ከማይገኝለት የአምላክነቱ ዙፋን ወርዶና ተዋርዶ፡ ከተቃዋሚው ጋር፡ በጠላትነት የወገነበትን፡ የዚያኑ የሰብአዊ ፍጡሩን መልክ በመውረስ፥ ሰውነቱንም በመልበስ፡ ለምን፡ ወደዚህ ዓለም መጣ?

- መጥቶስ፡ ለልጁ እናትነት ፍጹም በቅታ ከተገኘችው፥ እጆቿንም ወደእርሱ ዘርግታ ከጠራችው፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም፡ ለምን፡ በሰውነት ተወለደ?

- ተወልዶስ፡ ወደር የሌለውን መሥዋዕትነት፡ በራሱ ቤዛነት ከፍሎ፡ ስለምን፡ የካደውንና ያመፀበትን፡ ያንኑ፡ ሰብአዊ ፍጡሩን፡ ከዲያብሎስ፥ ከኃጢኣትና ከሞት አዳነው?

- ማዳን ብቻም ሳይኾን፡ እናንተን እና እኛንም ጭምር፡ ስለምን፡ በጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር፡ እንደገና በመንፈስ እንድንወለድ፥ በዚህም ልደታችን፡ እንደሥጋችንና ነፍሳችን፡ ለምን፡ መንፈሳዊዉን አካልና ባሕርይ እንድንለብስ አደረገ?

- ለሥጋችንና ለነፍሳችን፥ ለመንፈሳችንም፡ ምግብና ማጽኛ፥ መድኃኒትም የኾነነን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንስ፡ ለምን አበረከተልን?

- ከኃጢአት፡ በፍጹም አንጽቶን፡ ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል የሚያበቃንን፡ የንስሓን ጸጋስ፡ ስለምን ሰጠን?

- በዚህ ዓለም፡ በአካለ ሥጋ እያለን፡ በገነት ተድላ እንኖርስ ዘንድ፡ ስለምን፡ የፊተኛውን፡ የመንፈስ ትንሣኤን ሕይወት አደለን?

አምላካችን እግዚአብሔር፡ እንዲህ ባለ መልክና ይዘት፡ ልጁን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ሠውቶ፥ ቅዱስ መንፈሱንም በምልዓት አፍስሶ፡ ለመላዎቹ ሰብአውያን ፍጡሮቹ ኹሉ፡ ይህን የመሰለ ቸርነቱን ያበረከተልንና ፍቅሩን የፈጸመልን፥ ምሕረቱን ያደረገልንና ጸጋውን የሰጠን ለምን ይመስለናል? <u>እናንተ እና እኛ፡ ዛሬ ኾነን ለምንገኝበት ህልውናና ሕይወት በቅተን እንድንገኝ ሊያደርግ አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው።</u>

እንግዲያ፡ የፈጣሪያችን ፈቃድና ፍላጎት እንዲህ ከኾነ፡ እናንተ እና እኛ፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በፊቱ፡ እንዲህ ኾነን ለመቅረብ በመቻላችን፡ ማለትም፡ የተፈጠርንበትን፡ የእርሱን የእግዚአብሔርን መልክ መስለን፥ ከእግዚአብሔር የተወለድንበትን ልጅነት አጽንተን፥ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነታችንም፡ የእርሱ ማደሪያዎች፥ አገልጋዮቹ ካህናትና ሥዩማኑ ምሉካን ኾነን፥ ቤታችንንም፡ ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንነት አብቅተን በመገኘታችን፡ አዎን፡ ፈጣሪያችንና ቅድስት እናቱ፡ በእርግጥ ደስ ይላቸዋል፤ ከዚህ የተነሣ፡ እኛም፡ እጅግ ደስ ብሎን፡ ሓሤት ልናደርግ ይገባናል።

እዚህ ላይ፡ በትኵረትና በማስተዋል ልንመለከተው የሚገባን፡ “የሰው ልጆች” የፈጸሙትና እየፈጸሙት ያለ፡ አንድ አሳፋሪና አሳዛኝ ድርጊት አለ፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ የእርሱ አማኞች፡ የኾኑት ወገኖቹ፡ ይከተሉትና ይኖሩት ዘንድ፡ ገና ከፍጥረት መነሻ ጀምሮ፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዓቅዶ ያዘጋጀውንና ያካኼደውን፥ ራሱም ፈጽሞት፡ ለተከታዮቹ ያስተማራቸውን፥ ዛሬም፡ በመንፈስ ቅዱስ የቀጠለውን፥ በአኹኑ ጊዜም፡ እናንተ እና እኛ፡ በቅተንበት፡ እየኖርነው ያለነውን ይህን፡ የሕይወት ሥርዓት፡ በአንድ ወገን፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ በንቀትና በብልጠት፡ ገሸሽ አድሮ የተወው መኾኑ ነው። የዚህ አንጻር በኾነው፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በባዕድ አምልኮ ላይ የተመሠረተ፡ የተለያየ እምነት ያላቸው፡ የቀሩት የዓለም ሕዝቦች፡ የክርስቶስ ተቃዋሚው በኾነው፡ በዲያብሎስ አነቃቂነትና አበጋዝነት፡ ይህንኑ ሥርዓት በሚመስል አሳሳች መልኩ፡ ዘዴውን፡ በሥራ ላይ አውለው፡ ሲጠቀሙበትና የየሃይማኖታቸውን መሠረ ዓላማ ሲያስፋፉበት ማየቱ ነው።

በዚህ ረገድ፡ እየራሱን፡ በግል፡ “ክርስቲያን ነኝ!”፥ በማኅበርም፡ “ቤተ ክርስቲያን ነን!” እያለ የሚጠራው፡ ከላይ የተጠቀሰው ክርስቲያኑ ዓለም፡ የዚህን መለኮታዊ ሥርዓት፡ በሚቃረን መልኩና ይዘቱ፡ እያካኼደ ያለው አሠራር፡ ራሱን፡ ወደመጨረሻው፡ የውድቀቱ ገደል፡ ወርውሮ ሊጥለው፡ እየገፋፋውና እያቃረበው መኾኑ፡ እነሆ፡ በገሃድ ይታያል። ይህም፡ የዚሁ፡ የክርስቲያኑ ዓለም ባልደረቦችና መሪዎች የኾኑት፡ እነዚሁ ግለሰቦችና ድርጅቶች፡ ዓይነተኛ ግዳጃቸው የኾነውን ተግባር በመፈጸም ፋንታ፡ ለየራሳቸው ክብርና ጥቅም፥ ደኅንነትና ሥልጣን ሲሉ፡ የሚያካኺዱት ተቃራኒ ድርጊታቸው ነው። ያም የግዳጅ ተግባራቸው፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና ቤተ ክርስቲያን ኾኖ፡ ፈጣሪውን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ እያመለከው ይኖር ዘንድ፡ የእያንዳንዱን ሰብአዊ ፍጡር፡ የሰውነት ሕንፃ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር በማነጽና በመንከባከብ፡ ለመልካሚ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ማብቃት ነበር።

ዳሩ ግን፡ እኒሁ ግለሰቦችና ድርጅቶች፡ ለፈጣሪያቸውና ለቅድስት እናቱ፡ በቃል ኪዳን ተስማምተው የተቀበሉትን፡ ይህን፡ ቋሚ ግዳጃቸውን ትተው፡ ያለ የሌለ አሳባቸውንና ጊዜያቸውን፥ ኃይላቸውንና ገንዘባቸውን፥ ጥበባቸውንና ሥልጣናቸውን የሚያውሉትና የሚያባክኑት፡ ለሌላ ዓላማና ተግባር ኾነ።

ያም፡ ታላላቅ ሰው-ሠራሽ ሕንፃዎችን በመገንባትና የምድር ቊሳቊሶችን በመሰብሰብ፥ እንዲሁም፡ የራሳቸውን ሰብአዊ ሥርዓት እየፈለሰፉ፡ በሥራ ላይ በማዋልና በምእመናኖቻቸው ላይ በመጫን ብቻ መኾኑ፡ በታሪክ የተመሰከረና ዛሬም በግብር እየተፈጸመ የሚታይ እውነታ ነው።

ይህን የመሰለውን አፍራሽ ተግባራቸውን ሲያካኺዱ፡ የእግዚአብሔር አንድ ልጁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደዚህ ዓለም፡ መጥቶ፡ ሰው በመኾን፡ ራሱ ያደረገውንና ለደቀ መዛሙርቱም ያስተማረውን እየሻሩ፥ እንዲያውም፡ የዚያ፡ ተፃራሪ የኾነውን፡ ያላደረገውን፡ እያደረጉ፥ ያላስተማረውንም፡ እያስተማሩ መኾኑ፡ እንዴት ሳይታወቃቸው እንደቀረ ያስገርማል።

ለነገሩማ፡ ግለሰቦቹ፡ እየራሳቸውን፡ የስም "ክርስቲያን"፥ ወይም፡ "ምእመናን"፥ ወይም፡ "ካህናት" ብቻ ብለው ከመጥራት ይልቅ፡ እናንተ እና እኛ፡ ዛሬ ኾነን ለተገኘንበት ሕይወት አብቅተው፥ በቅዱሱ ኪዳን፡ "የእግዚአብሔር ዜጎች" ኾነውና ተብለውም መኖር ሲገባቸው፥ ድርጅቶቻቸውንም፡ "ቤተ ክርስቲያን" ብቻ ብለው፡ የማስመሰልና የሽንገላ ስያሜን ከመስጠት ይልቅ፡ እውነተኛ ማንነታቸውን በማረጋገጥ፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት" ኾነውና እየራሳቸውን የእግዚአብሔር መንግሥት አባሎችና ዜጎች አድርገው፥ እነርሱም፡ "እንዲህ ነን!" ብለው በአዋጅ ሊያሳውቁ ይገባቸው አልነበርምን? አዎን! ነበረ። ግን፡ ይኸው፡ እንደሚታየው፡ አልኾነም፡

ይኼ ቊም ነገር ቀርቶ፡ "እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት!" ማለትም፡ "መንግሥት፡ የእግዚአብሔር ናት!" የሚለውን የመለኮት ቃል፡ በድፍረት ጥሰውና አፍርሰው፥ ራሱ፡ የዚችው መንግሥት ፈጣሪዋ፥ መሥራቿና ጠባቂዋ፥ ባለቤቷና መሪዋ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "'እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት!'" ማለትም፡ "'መንግሥት፡ የአንተ ናትና!' ብላችሁ ጸልዩ!" ብሎ ያስተማረውን ቃል፥ እንዲሁም፡ "በአልባቢነ፡ ናስተማስል፡ አምሳለ መንግሥትከ ቦቱ!" ማለትም፡ "ይህችው መንግሥትህ፡ እንደቃል ኪዳንህ፡ በየልቦናችን ላይ እንድትመሠረት፥ በዚያም፡ ሰፍና እንድትኖር አደረግህ!" የሚለውን፡ የዘወትር የኪዳን ጸሎት፡ በእርሱና በቅድስት እናቱ መንበር ፊት፡ በየሰዓቱ እየጸለዩ፡ ይህችን የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በይፋ፡ ለሌሎች አሳልፈው ሰጥተው፡ የማስመሰልና የሽንገላ ድርጊታቸውን፡ ይኸው፡ ያለኀፍረትና ያለፍርሃት፥ ያለይሉኝታም፡ በማናለብኝነት እንደቀጠሉበት ይገኛሉ።

ይኹን እንጂ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ወይም፡ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚል አንድ ሰው፡ "ይህን በመሰለ ሃይማኖታዊ አቋም ላይ ያለሁ ነኝ!" ብሎ፡ ለራሱና ለእግዚአብሔር፥ ለሌላውም ወገኑ፡ በይፋ መስክሮና አረጋግጦ ካሳወቀ በኋላ፡ እንደገና ደግሞ፡ መልሶ፡ በይፋ፡ ራሱን፡ የኹለት መንግሥታት፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር መንግሥትና የሰዎች፥ ወይም፡ የዲያብሎስ መንግሥት "ተገዥና አገልጋይ ነኝ!" ማለት፡ በፈጣሪ ላይ፡ ታላቁን የክህደት ኃጢኣትን መፈጸም አይደለምን? ራስን ማቅለል፥ በአረማውያንና በአሕዛብም ዘንድ፡ ከከፍተኛ ትዝብት ላይ መጣል አይደለምን? በአንድ ጊዜ፡ ለኹለት ጌቶች መገዛትና ማገልገል "ይቻለኛል!" ብሎ፡ ለራሱስ፡ ሊያደርገው ቀርቶ፡ ሊያስበው እንኳ፡ እንዴት ሞከረ?

ዛሬ፡ በዓለም ላይ ያሉ፡ ሌሎቹ ሃይማኖታውያን ሕዝቦች ኹሉ፡ ለምሳሌ፡ ቻይናውያን፥ ጃፓናውያን፥ ሕንዳውያን፥ አይሁድና እስላሞች፡ ኹሉም፡ የየሃይማኖታቸውን መመሪያ ተከትለው፡ ግላዊና ቤተሰባዊ፥ ብሔራዊና መንግሥታዊ የኾነውን ሕይወታቸውን ሲመሩ ይታያሉ። ለዚሁ ሃይማኖታቸውም ሲሉ፡ የሌላውን ብቻ ሳይኾን፥ የራሳቸውንም ሕይወት ሳይቀር፡ በራሳቸው እጅ፡ እስከማጥፋት ድረስ፡ እንደማይመለሱ፡ እነሆ፡ ያለማቋረጥ እናያለን። እነርሱም፡ ከክርስትና እምነት ውጪ ስለኾኑ፡ ሃይማኖታቸው የሚጠይቃቸውንና ከእነርሱ የሚጠብቀውን፡ ማናቸውንም ግዳጅ፥ ክፉውንና ሰይጣናዊ የኾነውን ጭምር ቢሠሩ፡ የሚያስደንቅ አይኾንም። እንዲያውም፡ ያንኑ፡ የሃይማኖታቸውን ሥርዓትና መመሪያ፡ በተግባር ፈጻሚ ተብለው፡ በወገኖቻቸው ዘንድ ይወደሱበታል፤ ይሞገሱበታል።

"ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው፡ የዓለም ኅብረተሰብ ግን፡ በግሉም ኾነ በቤተሰብ፥ በአገርም ኾነ፡ በመንግሥት ደረጃ፡ የክርስትና ሃይማኖቱን የተቀደሰ ዓላማ፡ በአግባቡና በትክክል መፈጸም ሳይችል ሲቀር፥ እንዲያውም፡ በተቃራኒው፡ አንድ ክርስቲያን ግለሰብ፥ ወይም፡ ቤተሰብ፥ ወይም፡ ሕዝብ፥ ወይም፡ መንግሥት፡ በክርስቲያንነቱ፡ ሊያደርገው የሚገባውን ትቶ፡ የማይገባውን ተግባር፡ እያካኼደ ሲፈጽም መታየቱ፡ እጅግ ያሳዝናል።

ክርስቲያኑ ዓለም፡ ሃይማኖቱ፡ ከእርሱ የሚጠይቀውን ግዳጅ፡ እንዲህ፡ ሊፈጽም ባልቻለበት፡ በዚህ አንጻራዊ ኹኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ፡ አማኞቻቸው እንደተከተሏቸው፡ እንደሌሎቹ የክርስትና ተቃራኒ የሃይማኖቶች መሪዎች ኹሉ፡ "ታዲያ! ለምንድር ነው፡ ክርስቲያኖች፡ የሃይማኖታቸው መሥራችና መሪ የኾነውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ተከትለው የማይኖሩት?" ብለው፡ እኒሁ ተቃራኒዎቻችን፡ ለሚያቀርቡት ጥያቄ፡ በአኹኑ ኹኔታና በዚህ ረገድ፡ መልስ ለመስጠት ያስቸግራል፤ ያሳፍራልም።

ይህን በሚመለከት፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊወሳ የሚገባው፡ ዓቢይ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ የገዛ ሃይማኖቱን መሠረታዊ አቋም፡ ጨርሶ የሚያፈራርስ ፍልስፍና ፈጥሮ፡ ማንነቱን ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔር፡ ከጥንት ጀምሮ ያቆማትን፥ ኋላም፡ ሰው ኾኖ ያጸናትን፡ መለኮታዊ መንግሥት እየተጻረረ፡ ራሱንና የራሱን የኾነው ሥራ ሲያፈራርስ መገኘቱና መታየቱ ነው። ይህም፡ የክርስትና እምነት ተጠሪዎች ነን የሚሉት፡ ወገኖች የፈጠሩት፡ "ሃይማኖት የግል፤ አገር የጋራ!" የሚለው ሰብአዊና ሰይጣናዊ ፈሊጥ ሲኾን፡ ባዕዳኑ ፈረንጆች፡ Church and State (ቸርች ኤንድ ስቴት)፡ ማለትም "ሃይማኖት እና መንግሥት የተለያዩ ናቸው!" ከሚለው ፍልስፍናቸው የተቀዳው ፈሊጥ ነው።

በዚህ ዐጉል ፍልስፍና ምክንያት፡ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ወገን ቀንደኛ መሪነት፡ ራሱን፡ በነፍስና በሥጋ፡ ለኹለት ከፍሎ፡ የዚህ ዓለም ህልውናውን፡ በሰብአዊነት ብቻ ሳይኾን፡ በሰይጣናዊነት ጭምር፡ እንዲመራ እየተደረገ ስለኾነ፡ ዲያብሎስ፡ በእነዚህ ክፉዎች ሰዎች የአገዛዝ መሣሪያነት፡ እነሆ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም በሚመሩዋት፥ ኢትዮጵያንና ፍጥረተ ዓለሙንም በሚያስተዳድሩባት፡ በአንዲቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ፡ ከጥንት ጀምረው የወጠኑትንና ሲያካኺዱ የኖሩትን የማጥቃት ዘመቻቸውን፡ ይኸው፡ በተጠናከረ ኹነታ ተያይዘውት፡ ቀጥለውበታል።

በአንድ ወገን፡ ራሱ፡ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው የዓለም ክፍል፡ በዚህ የጥፋት ዘመቻ ላይ በሚገኝበት ጊዜ፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የክርስትና ተቃራኒ የኾኑት የቀሩት የዓለም ክፍሎች፡ በዚችው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ፡ በገሃድ እያካኼዱ ያሉትን የማጥቃት ዘመቻ መመልከቱ፡ ለአስተዋይ ተመልካች፡ አሳዛኝ ትርኢት ነው። ይህን የመሰለውን ዘመቻ ከሚያካኺዱት መካከል፡ እስላም የኾነውን ወገን፡ በምሳሌነት ብንወስድ እንኳ፡ ይህ ሃይማኖት፡ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መመሪያና ሥርዓት በኾነችው፡ በቅዱሱ ኪዳን የክርስትና ሃይማኖት ላይ፡ በሰውና በንብረት ረገድ፡ ያደረሰው ጉዳት፥ ዛሬም እያፋፋመ የሚያኪያኺደው የጥፋት ድርጊት፡ በቃላት ሊነገር፥ በሥፍርም ሊተመን ያዳግታል።

የሚያመልከውን አምላክ፡ "አላህ" ብሎ የሚጠራውና "አላህ ወአክበር!" ማለትም፡ "አምላኬ ታላቅ ነው! ሌላ አምላክ የለም!" በሚል ዘፎ እየተመራ ያለው፡ ይኸው የእስልምና ሃይማኖት፡ ሃይማኖቱ በሚያዝዘው መሠረት፡ በክርስቲያኑ ዓለም ላይ "ጂሃድ" ብሎ፡ የ"ገሃድ" ጦርነት አውጆ፡ "በዓለም ላይ የሚኖር፡ የማናቸውም ግለሰብና ቤተሰብ፥ አገርና መንግሥት፡ ህልውናውና ሕይወቱ መመራትና መካኼድ ያለበት፡ በሃይማኖቱ ሥርዓት ብቻ ነው!" በማለት፡ ከየራሱ አገርና ሕዝብ አልፎና ተርፎ፡ መላው ዓለም፡ ክርስቲያኑ ዓለም ጭምር፡ ይህንኑ፡ የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበል ለማድረግ፡ ከቀድሞ ጀምሮ ሲያካኺድ የኖረውን ጦርነት፡ በተለይ፡ በአኹኑ ዘመን፡ እነሆ፡ እያፋፋመው ይገኛል። ይህም እውነታ፡ ዛሬ፡ በእስልምናው ወገንና በክርስቲያኑ ወገን መካከል፡ በዘመናዊው የጦር መሣሪያ እየቀጠለ በኼደው፡ በግዙፉ ጦርነት፥ ከዚህም የተነሣ እየደረሰ ባለው፡ ደም መፋሰስና እልቂት ምክንያት፡ መላውን ፍጥረተ ዓለም፡ ወደትንቢቱ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው አይጠረጠርም።

ኹኔታው፡ በዚህ መልክ ከቀጠለ፡ ውጤቱ፡ ለክርስቲያኑ ዓለም፡ እጅግ አሳሳቢና አሥጊ መኾኑ ግልጽ ነው፤ ይኸውም፡ የእስልምናው ወገን፡ የኃይል ምንጩ ያደረገው፡ ራሱን፡ ሃይማኖቱን ስለኾነና ያም፡ ሃይማኖት፡ በክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ የሚመራ ሲኾን፥ የክርስቲያኑ ዓለም ደግሞ፡ የኃይል ምንጩን፡ ሥጋዊ በኾነው እውቀትና ጥበብ፥ ገንዘብና መሣሪያ ላይ ብቻ መሥርቶ የሚያካኺድ በመኾኑ፡ የጦርነቱ ፍጻሜ፡ የሚያበቃው፡ በየትኛው ወገን፡ ድል አድራጊነት እንደሚኾን ማወቁ አያስቸግርም፡፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ መስሎት እንደሚፍጨረጨረው፡ የዲያብሎስ የሓሰት ድርጊቱና የክፋት መንፈሱ ኃይል፡ ድል የሚደረጉት፡ በሰብአዊው እውቀትና ጥበብ፥ በሥጋዊው ኃይልና መሣሪያ፥ በዓለማዊው ገንዘብና ንብረት አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኮት ብቻ እንጂ፡፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ በግልም ኾነ በኅብረት፡ ይህን እውነታ፡ አረጋግጦ ማወቅ አለበት፡፡

አዎን! መንፈሳዊ የኾነው፡ ሃይማኖታዊው ኃይል፡ ቅዱሱም፡ ኾነ ርኵሱ፡ በሥጋዊው ኃይል ላይ የአሸናፊነትን አክሊል እንደሚቀዳጅ ሊታበል አይቻልም፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ሥጋዊ በኾነው፡ በግዙፉ ኃይል በተመካው፡ በክርስቲያኑ ዓለም ላይ፡ ድሉን የሚያገኘው፡ መንፈሳዊ በኾነው፡ በሃይማኖት ኃይል የታመነው፡ የእስልምናው ወገን ይኾናል፡፡ ይህም ማለት፡ ይህ ኹኔታ፡ በክርስቲያኑ ዓለም በኩል፡ በሃይማኖታዊ አስተሳሰቡና በምግባራዊ አፈጻጸሙ ረገድ፡ ምንም ዓይነት፡ መሠረታዊ ለውጥ ሳያደርግ፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ ከቀጠለ፡ እንግዴህ፡ የክርስቶስ ተቃዋሚ የኾነው ዲያብሎስ፡ በምድር ላይ፡ በሚኖሩ "የእግዚአብሔር አማኞች ነን!" በሚሉት ወገኖች በተያዘው በክርስቲያኑ ዓለም ሳይቀር፡ ፈጽሞ ይሠለጥናል ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ፡ "ሃይማኖቴ፡ ክርስትና ነው!" እያለ ለሚመጻደቀው፡ ለዚሁ፡ ለዓለሙ ግብዝ ኅብረተሰብ፡ እንዲህ የሚለው፡ የሓዋርያው ቃል፡ ሊጠቀስለት ያስፈልጋል፦

"አንተሰ ተአምን፡ ከመ አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር፡ ሠናየ ትገብር፡፡ ከማሁሰ፡ አጋንንትኒ የአምኑ፤ ወይደነግፁ፡፡ ትፈቅድኑ ታእምር፡ አ ብእሲ ዓብድ፡ ከመ ሃይማኖት፡ ዘእንበለ ምግባር፡ ምውት ይእቲ?"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ አንድ እንደኾነ፡ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፡፡ አጋንንት ደግሞ፡ ያምናሉ፤ ይንቀጠቀጡማል፡፡ አንተ፡ ከንቱ ሰው! ሃይማኖት፡ ከምግባር ሲለይ፡ የሞተ መኾኑን፡ ልታውቅ ትወድዳለህን?" (ያዕ. ፪፥ ፲፱-፳፡፡)

በህልውናው፡ ሃይማኖታዊ ምግባርን ትቶ፡ በሃይማኖት ብቻ መኖር የሚቻል መስሎት፡ በዕብሪት የሚዝናናው፡ ይኸው፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ ከዚህ አደገኛና አሥጊ ፍጻሜ ለመዳን፡ ያለው ምርጫና ዕድል አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም፡ በበጎው ሳይኾን፡ ሰይጣናዊ በኾነው፡ የክፋት ዝንባሌው ምክንያት፡ በቅዱሱ ኪዳን የክርስትና ሃይማኖቱ ላይ፡ በገሃድ ከፈጸመው የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ ምንዝርናና የእርስ በርስ መገዳደል ኃጢአቱ ተጸጽቶ፡ በግልና በቤተሰብ፥ በአገርና በመንግሥት ደረጃ፡ እየራሱን፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት መመለስ ነው፡፡

የአይሁድ ፈሪሳውያን፡ "ማእዜ ትመጽእ መንግሥተ እግዚአብሔር?" ማለትም፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መቼ ትመጣለች?" ብለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጠየቁት ጊዜ፡ የሰጣቸው መልስ፡ "ኢትመጽእ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ በተዐቅቦ፡፡ ወኢይብልዋ፡ ነያ ዝየ! ወነያ ከሓክ! መንግሥተ እግዚአብሔርሰ፡ ነያ፡ ማዕከሌክሙ ይእቲ፡፡"

ማለትም፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በመጠባበቅ አትመጣም፡፡ ደግሞም፡ 'እነኋት በዚህ! እነኋት በዚያ!' አይሏትም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እነሆ፡ በመካከላችሁ ናትና፡፡" የሚል መኾኑን፡ "እኔ፡ ክርስቲያን ነኝ!"፥ "እኛ፡ ቤተ ክርስቲያን ነን!" የሚሉት እኒሁ፡ የክርስቲያኑ ዓለም ተመጻዳቂዎችና ግብዞች፡ ይህን ጥቅስ፡ በቃላቸውና ከመጻሕፍቱ እያወጡ፡ በየጊዜያቱ ስለሚያነበንቡት፡ አሳምረው ያውቁታል፡፡ (መዝ. ፳፩፥ ፳፰፡፡ ማቴ. ፮፥ ፲፫፡፡ ሉቃ. ፲፯፥ ፳-፳፩፡፡)

እንግዴህ፡ በክርስቲያኑ ዓለም ዘንድ፡ "በምድር ላይና በዓለም ሕዝቦች መካከል፡ የእግዚአብሔር ባለአደራዎችና ተጠሪዎች ነን!" ብለው፡ ራሳቸውን ያስተዋወቁ፥ የምድር ወገኖችም ኹሉ፡ በዚሁ ማንነታቸው የተቀበሏቸው፡ እኒህ ግለሰቦችና ድርጅቶች ናቸው፦

- እንዲህ አድርገው፡ የእግዚአብሔር ብቸኛ ጥሪቱ የኾነችውን፡ "መንግሥት"ን፡ ለሰው ብቻ ሳይኾን፡ ለዲያብሎስ ጭምር ያደሏቸው፤

- በዚህም ዕድል፡ በሕዝቦቻቸው ዘንድ፡ እውቅናን ያስሰጧቸው::

- ተከታዮቻቸውን፡ "ክርስቲያን"÷ ድርጅታቸውንም፡ "ቤተ ክርስቲያን" ብለው ከመጥራት ጋራ፡ እነዚህኑ መንጎቻቸውን፡ በሙሉ÷ ካህናቶቻቸውን ጭምር፡ ለእነዚያ፡ ለሰዎችና ለዲያብሎስ መንግሥታት፡ ተገዦችና አገልጋዮች እንዲኾኑ ያሰናበቷቸው፤

-ፈጣሪ ዓለማት እግዚአብሔር፡ ቀድሞ፡ በሥነ ፍጥረት አሳምሮ የመሠረተው÷ ኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ መልሶ ያስተካከለው፡ የሰው ልጆች ህልውና÷ በተለይም፡ የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ሕይወት ሊቃወስ የቻለው፤

-በመጨረሻም፡ ይኸው ቀውስ፡ በዚህ መልክ እንዲሰፍን በይፋ በመፍቀዳቸው፡ ሰብአዊው የዚህ ዓለም ኑሮ፡ በጠቅላላ፡ እነሆ፡ እንዲህ የተመሰቃቀለ ኾኖ ሊቀር የበቃው::

## ክፍል ሦስት

እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ለምን ይህን መልእክት "**የምሥራች**!" ብለን፡ በታላቅ ዜናነት አቀረብነው? ለምንስ፡ "በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!" አልን?

ለዚህም መጠይቃዊ ቃል፡ መልሶች የኾኑ፡ ከዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ከገለጽናቸው ጋር የተያያዙ፡ ሌሎችና ብዙዎች፡ በቂ ምክንያቶች ስላሉ፡ እነርሱንም፡ በዚሁ መልእክት ውስጥ፡ ጨምረን ልናቀርባቸው፡ ተገቢ ኾኖ አግኝተነዋል:: በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት፡ ለእያንዳንዳችንና ለኹላችንም፡ ያለልዩነትና ያለአድልዎ፡ በግል ሰውነታችንና በኢትዮጵያዊው ኅብረተሰብአዊነታችን፡ የተከሠቱልንን፡ እነዚህን፡ የመለኮት እውነቶችና የተደረጉልንን፡ የፈጣሪ ቸርነቶች በማጠቃለል፡ እንደሚከተለው አሥፍረናቸዋል:-

### አንደኛ:- <u>የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪና ባለቤት፡ እግዚአብሔር ብቻ ስለመኾኑ፤</u>

ከዚህ "የምሥራች" መልእክት መግቢያ ላይ እንደገለጽነው፡ ራሱ፡ መንፈስ የኾነው እግዚአብሔር፡ በረቂቁ መንፈስ እየኖረ ሣለ፡ ይህን ዓለም፡ ጥንቱኑ አግዝፎ የፈጠረልን፡ ማለትም፡ የምንተነፍሰውን አየር÷ የምናይበትንና የምንሞቀውን ፀሓይ÷ የምንጠጣውንና የምንታጠብበትን ውኃ÷ የምንኖርባትንና የምትመግበንን ምድር÷ ከዚህም በላይ የምንገለገልባቸውንና የምንደሰትባቸውን፡ እንስሳቱንና አራዊቱን÷ አእዋፋቱንና ዓሣዎቹን÷ አበቦችን ሳይቀር ያዘጋጀው ለማን ነው? አስቀድሞ፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው አካላትና ባሕርያት፡ በመልኩ ለሠራን÷ በመጨረሻም፡ በቅዱስ መንፈሱ ለወለደን፡ ለእናንተ እና ለእኛ አይደለምን? አዎን! ነው::

ፈጣሪ፡ እያንዳንዳችን ሰብኣውያን ፍጡሮቹ፡ ከእርሱ ጋር፡ ያለማቋረጥ፡ በየቅጽበቱ፡ ቀጥተኛ የኾነ ግንኙነት እንዲኖረን ማድረጉንስ ታውቁ የለምን? ምናልባት፡ አላስተዋልነው ይኾናል እንጂ፡ ይህ እውነታ፡ በየአፍታው፡ የየራሳችን ድርጊት ስለኾነ፡ በእርግጥ፡ እናውቀዋለን:: ይህ፡ ከፈጣሪያችን ጋር፡ በቀጥታ የምናደርገው የማያቋርጥ ግንኙነት፡ በነፍሳችን፡ የእግዚአብሔር መልክ በኾነው ረቂቁ ሕሊናችንና የእግዚአብሔርን ልጅነት ባገኘንበት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋችን ብቻ ሳይኾን፡ በግዙፉ ሥጋዊው አካላችን ጭምር መኾኑን፡ ከላይ የተዘረዘሩት የሥነ ፍጥረት ታላላቅ አካላት፡ እያረጋገጡ ይነግሩናል::

ይኸውም፡ ያለማቋረጥ በምንተነፍሰውና በከበበን አየር÷ በምናይባትና በምንሞቃት ፀሓይ÷ በምንጠጣውና በምንታጠብበት ውኃና በቆምንባትና በምትመግበትን ምድር አማካይነት፡ በፈጣሪያችንና በእኛ መካከል፡ ያለማቋረጥ፡ የሚካኼደው፡ ሥጋዊና ግዙፋዊ ግንኙነታችን ነው::

ሥነ ፍጥረቱ ኹሉ፡ እንዲህ፡ ለእኛ መልካም ህልውናና ሕይወት፥ ጥቅምና አገልግሎት፥ ዕረፍትና ደስታ የተዘጋጀልን መኾኑን፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠርንባት በእግዚአብሔራዊቷ እውቀታችን፡ ይህን እውነታ አወቅን፤ ተረዳን፤ ተገነዘብን። ታዲያ! ይህ ብቻ፡ ራሱን የቻለ፡ "ልዩ የምሥራች ምንጭ" ኾኖን፡ "በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሐሤትም እናድርግ!" እንባባል ዘንድ አያበቃንምን? አዎን! በእርግጥ ያበቃናል።

እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የፍጥረተ ዓለሙ ብቸኛ ፈጣሪና ባለቤት፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር ብቻ መኾኑን እንዲህ እናውቃለን፤ አውቀንም፡ እንዲህ እናምናለን፤ አምነንም፡ በዘወትሩ ጸሎታችን፦

"ንሕነ ኢትዮጵያውያን፡ ነአምን፡ በአሐዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብ፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ። ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልደ አብ ዋህድ፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ...ዘቦቱ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ።"

ማለትም፡ "እኛ ኢትዮጵያውያን፡ 'ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ...ኹሉ በእርሱ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም። "

ደግሞም፡ "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት፤ ፍጹም ምሉዕ፡ ሰማያተ ወምድረ!" ማለትም፡ "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብሎ የሚመሰገነው፡ አሸናፊው የሠራዊት አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ በሰማያትና በምድር ፈጽሞ የመላ ነው!"

እንዲሁም፡ "አንተ ውእቱ አምላከ አማልክት፥ ወእግዚአ አጋእዝት፥ ወንጉሠ ነገሥት!" ማለትም፡ "አንተ፡ የአምላኮች አምላክ፥ የገዢዎች ገዢና የንጉሦች ንጉሥ ነህ!" እያልን፡ እናመሰግነዋለን።

እንግዴህ፡ የሥነ ፍጥረት እውነታ፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ የዚህ ዓለም ሰዎች ግን፡ ይህን እውነታ በሚጻረር አቋምና ይዘት፡ እነሆ፡ ምድራዊና ሥጋዊ ህልውናቸውን፡ በግልና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በአገር ደረጃ፥ የአገዛዝ ድርጅታቸውንም፡ "መንግሥት" ብለው እየጠሩ፡ ሲመሩና ሲያካኺዱ ይታያል።

ይህንም የሚያደርጉት፡ የዚሁ ፈጣሪያችን ብቸኛ የባሕርይ ሀብታት የኾኑትን፡ የመጨረሻ አምላክነትንና የገዢነትን ሥልጣን፥ የፍጥረት ባለቤትነትንም ሳይቀር፥ ከእነዚህ ማዕርጋት የሚመነጩትን፡ መፈራትንና መታመንን፥ ክብርንና ምስጋናን ጭምር፡ በገዛ ፍላጎታቸውና ምርጫቸው፡ ለዲያብሎስና ለሰብአውያን መሰሎቹ አሳልፈው በመስጠት ነው። ከዚህ የተነሣም፡ ለእነዚሁ፡ የፍጥረተ ዓለሙ፡ ኢምንት ፍጡራን ለኾኑት፡ የክፋት አበጋዝ እና ለኃይላቱ ያላቸውን፡ የየራሳቸውን ተገዢነትና ታማኝነት፥ አገልጋይነትና መሣሪያነት፡ በአምልኮ መሓላቸው አረጋግጠዋል።

የዚህ ዓለም ሰዎች የሚያካኺዱትንና የሚኖሩትን፡ ይህን ዓይነቱን፡ የክፋትና የሓሰት አኗኗር ዘዬ፡ ከነድርጊቱ፡ እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እናስወግደዋለን እንጂ፡ በምንም መንገድ አንቀበለውም። የማንቀበለውም፡ ከላይ በተገለጸው ምክንያት መኾኑ፡ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። ይኸውም፡ የእግዚአብሔር በኾነችው፡ በአንዲቷ መንግሥት ቦታ፡ የዲያብሎስንና የሰብአውያን አገልጋዮቹን አገዛዝ፡ በሃይማኖት ስም ኾነ በሥጋዊ ድርጅት መልክ ተክተው፡ የአምላክነትንና የፍጥረተ ዓለሙን ባለቤትነት፡ ለእነርሱ ሰጥተው፥ የእነርሱንም የገዢነት ሥልጣን፡ በየራሳቸው ላይ አስፍነው የሚኖሩትን ማለት ነው።

ደግሞም፡ እኒሁ የዓለም ሰዎች፡ በፍጥረተ ዓለሙ ብቻ ሳይኾን፡ በሰው፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊም አካላትና ባሕርያት ላይ ጭምር፡ ዲያብሎስ፡ ድርሻና መብት እንዳለው እያስመሰሉ፡ ይህንኑ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን የፍጥረት ክፍል፡ ለዚሁ፡ የክፋት ኃይልና ለሰብአውያን አገልጋዮቹ አሳልፈው መስጠታቸውን፡ እናውቃለን።

ነገር ግን፡ እናንተ እና እኛ፡ "ማን በፈጠረው ፍጥረትና በማን ባለቤትነት፡ ማን ሊገባበት ይቻለዋል? አይቻልም!" እያልን፡ የዚህን ሓሰተኛ ይትበሃል ድቡሽታዊ አቋም፥ ረቂቅ ጽንሰ ሓሳቡን ሳይቀር ባለመቀበል፡ እንደጥንቱ፡ ዛሬም፡ ከመሠረቱ ጨርሰን አፈራረስነዋል፡፡

አዎን! ሥጋንም፥ ነፍስንም፥ መንፈስንም የፈጠረ እግዚአብሔር ስለኾነ፡ የእነዚህ መለኮታውያን ዕፁብ ድንቆች አካላትና ባሕርያት ኹሉ ባለቤት፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ እስከመጨረሻው ድረስ፥ ለዘለዓለምም፡ ራሱ፡ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር ብቻ መኾኑ፡ በተለይ፡ የዛሬ ኹለት ሺህ አንድ ዓመታት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእትና በድንግል ማርያም የአምላክ እናትነት፡ በማያወላውል ቃልና አገላለጽ ታትሟል፡፡ በዚህ የፈጣሪነትና የባለቤትነት መብትና ሥልጣን፡ ሌላ የሚጋራም እንኳ፡ ማንም እንደሌለ፡ ሊታወቅ ይገባል፡፡

እናንተ እና እኛ፡ እንደማናቸውም ሰብአዊው ፍጡር ኹሉ፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ከነአካላቸውና ባሕርያቸው፡ በተፈጥሮ ያገኘናቸው፡ ከፈጣሪያችን፡ ከእግዚአብሔር ስለኾነ፡ እነርሱንና መላውን ፍጥረተ ዓለም፡ በጥንቃቄ ልንይዛቸውና በአግባቡ ልንንከባከባቸው ይገባናል፡፡ ፈጣሪ፡ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች በፈጠረበት ጊዜ፡ የተፈጠሩባትንና የሚኖሩባትን ምድር፡ ሊጠብቋትና ሊንከባከቧት እንደሰጣቸው፡ እንዲህ የሚለው መመሪያ ቃሉ ያስረዳናል፡-

"ወነሥአ እግዚአብሔር፡ ለእጓለ እመሕያው ዘገብሮ፤ ወሤሞ ውስተ ገነት፡ ከመ ይትገበራ፥ ወይዕቀባ፡፡"

ማለትም፡ "እግዚአብሔርም፡ የፈጠረውን ሰው ወስዶ፡ ያርሳትና ይቆፍራት፥ ይጠብቃትም ዘንድ፡ በገነት አኖረው፡፡" (ዘፍጥ ፪፥ ፲፭፡፡)

በዚህ መልክ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ደጉን፡ ከክፉው፡ ለይቶ የሚያውቅበትን አእምሮ፥ ከኹለት አንዱን የሚወድደውን ሊመርጥ የሚያስችለውን ሕሊና፥ ያን፡ የመረጠውንም ለመፈጸም የሚወስንበትን የፈቃድ ኃይል፡ ፈጣሪው፡ ጥንቱኑ፡ በተፈጥሮው ስለሰጠው፡ ያ ሰብአዊ ፍጡር፡ በዚያ ጸጋው ተጠቅሞ፡ ባደረገው ምርጫ፡ ራሱን፡ ለክፉው ዳርጎ እንደነበረ፥ ዛሬም፡ አብዛኛው፡ በዚያው አካኼዱ እንደቀጠለበት ይታወቃል፡፡

ይኹን እንጂ፡ ያም ኾኖ፥ ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ በባለውለታቢስነት፡ ያን፡ አሳዛኝና አስተዛዛቢ ድርጊት ቢፈጽምም፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር ወልድ፡ በቸርነቱና በርኅራኄው፥ በመሓሪነቱም፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶና ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተወልዶ፥ በመስቀልም ላይ ሞቶና ከመቃብር፡ በድል አድራጊነት ተነሥቶ፡ ያንኑ፡ እርሱ የፈጠረውንና በራሱ ክፋት ጠፍቶ የነበረውን ፍጥረተ ዓለሙን፥ መላውን፡ የሰብአዊዉን ፍጡር ኹለንተና ጭምር፡ ማለትም፡ ሥጋውንም፥ ነፍሱንም፥ መንፈሱንም፡ ወደራሱ ባለቤትነት መልሶታል፡፡ ስለዚህ፡ "እኒህ ሀብታት ኹሉ፡ ማለትም፡ ሥጋዊውና ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊውም፡ የእግዚአብሔር ብቻ እንጂ፡ የሌላ ሊኾኑ፡ ከቶ አይቻልም!" የሚያሰኘው፡ ይህ እውነታ ነው፡፡

እኒሁ የዓለም ሰዎች፡ ይህ ሳያንሳቸው፡ በዚሁ መልክ፡ ብርሃንንና ነጭን፥ ደግሞ፡ ብርሃንና ነጭ የኾነውንም ብቻ፥ እንዲሁም፡ ቀኝንና ቀኝ የኾነውንም ብቻ፡ የእግዚአብሔር እንደኾኑና ለእርሱ እንደተሰጡ፥ እንዲያውም፡ እርሱ የፈጠረው፡ እነዚህን ወገኖች ብቻ፥ ባለቤትነቱም፡ ለእነዚሁ ብቻ እንደኾነ አድርገው፡ ራሳቸው አምነው፡ ሌላውንም ለማሳመን ሲሞክሩ ኖረዋል፡፡ በዚህም አንጻር፡ ጨለማንና ጥቍርን፥ ደግሞ፡ ጨለማና ጥቍር የኾነውንም ኹሉ፥ እንዲሁም፡ ግራንና ግራ የኾነውንም ኹሉ፡ የዲያብሎስ እንደኾኑና ለእርሱ እንደተሰጡ፥ እንዲያውም፡ እነዚህን ወገኖች የፈጠረው፡ እርሱ፡ ዲያብሎስ፥ የእነዚህ ወገኖች ባለቤትነቱም፡ የእርሱ እንደኾነ አድርገው፡ ራሳቸው አምነው፡ ሌላውንም ለማሳመን ሲሞክሩ ኖረዋል፡፡

ይህንኑ፡ የእምነትና የማሳመን ሙከራቸውን፡ በዚህ ሳያቆሙ፡ ምሥራቁን ብቻ ለእግዚአብሔር በመተውና ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ስግደት፡ ወደምሥራቅ ብቻ እንዲኾን በመወሰን፡ ምዕራቡንና የቀሩትን የዓለም ማዕዝናት፡ ለዲያብሎስ መድበውና አደላድለው ሰጥተዋል፡፡

እናንተ እና እኛ፡ ይህን ክፉና ሓሳዊ ድልድል ባለመቀበል፡ ብርሃንም፥ ጨለማም፥ ቀኝም፥ ግራም፥ አራቱም ዓበይት ማዕዝናት፡ ማለትም፡ ምሥራቁና ምዕራቡ፥ ሰሜኑና ደቡቡ፡ እንዲሁም፡ አራቱ ንዑሳን ማዕዝናት፡ ማለትም፡ መስዑና ዓዜቡ፥ ሊባውና ባሕሩ፥ ኹሉም፡ በአንዱ፡ ፈጣሪ፡ በእግዚአብሔር የተፈጠሩና፥ ባለቤታቸውም፡ እርሱ መኾኑን አምነን፡ ሌላውንም፡ እናሳምናለን።

እኒሁ፡ ክፉዎቹ የዓለም ሰዎች ካልኾኑ በቀር፡ ጨለማንና ጥቍርን፥ ግራንም፡ ለዲያብሎስ የሰጠው ማነው? አላዋቂነታቸው እንጂ፡ ጨለማኮ፡ የብርሃን አለመኖር፡ የሚፈጥረው ኹነታ ነው፤ በራሱ ብቻ ሊኖር፥ ወይም፡ ሊገለጥ የሚችል ነገር አይደለም። ብርሃን ሲኖር፡ እርሱ የለም። ጥቁርም፡ እንደነጭና እንደሌሎቹ ቀለማት፡ ራሱን የቻለ የቀለም ዓይነት ነው። ግራም፡ የቀኝ፡ መንታ፡ ኹለትዮሽና ረዳት ነው።

የዓለም ማዕዝናትን በሚመለከት፡ ምሥራቁ ብቻ ሳይኾን፡ ኹሉም ማዕዝናት፡ የፈጣሪያቸው፡ የእግዚአብሔር ስለኾኑ፡ እናንተ እና እኛ፡ የአምልኮ ስግደታችንን፡ ክብ የኾነውን ቤተ መቅደሳችንን ማዕከል በሚያደርገው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት መሠረት፡ ወደምሥራቅና ወደኹሉም ማዕዝናት አግጣጫ አድርገን እንፈጽማለን።

በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ኾነን፡ በኹሉም ማዕዝናት፡ ለሥሉስ ቅዱስና ለቅድስት ድንግል ማርያም፥ ለቅዱስ መስቀልም በምንሰግድበት ጊዜያት፡ መሬቱን ስንስም እኮ፡ "ሰማይኒ፡ መንበርየ፤ ወምድርኒ፡ መከየደ እገርየ።"

ማለትም፡ "ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት፤" ያለውን፡ መለኮታዊ ቃል ተከትለን፡ የእግዚአብሔርንና የአምላክን እናት፡ እግሮቻቸውን መሳማችን አይደለምን? በመስቀል ስግደትስ ጊዜ፡ ከችንካሩ የተነሣ፡ በደም የታለሉ፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እግሮች መሳማችን አይደለምን? መኾኑንማ፡ እናንተ እኛ እናውቀዋለን። (የሓዋ. ፯፥ ፵፱።)

የኹሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላክ፡ በረቂቅ ጥበቡ፡ ፍጥረታቱን ኹሉ የፈጠረው፡ ለበጎ ብቻ መኾኑ፡ በሥነ ፍጥረቱና ባልተቋረጠው ሥራው፥ በሃይማኖትና በቅዱሳት መጻሕፍት ታውቋል፤ ተረጋግጧልም። ያን፡ በጎውን ትቶ፡ ክፉውን ያመጣው፡ ሰው መኾኑ፡ ገና፡ ከመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን ዝንባሌና ድርጊት ታይቷል፤ ያም ኹኔታ፡ በሰዎች በኩል ሳይቋረጥ፡ እስከዛሬ መቀጠሉ፡ እነሆ፡ እናንተ እና እኛ፡ የዓይን ምስክሮች ነን።

እግዚአብሔር፡ ለፍጥረቱ መልካም ሕይወት እንዲያገለግል፡ የፈጠውን፡ ያን፡ በጎ ፍጥረት፡ ሰው፡ በተፈጥሮው፡ በተሰጠው የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን፥ የማድረግም ችሎታ በመጠቀም፡ ከራሱ ጀምሮ፡ ለክፉው በማዋል፡ ይኸው፡ እስከዛሬ የደረሰበትንና ዛሬም እየደረሰበት ያለውን ጠንቀኛ ችግር፡ ኹሉም የሚያውቀው ነው። ይህም ኹኔታ፡ እስከዓለም ፍጻሜ እንደሚቀጥል፡ እስካኹን ደርሶ የታየው፡ "የሰው ልጆች" ዝንባሌና ድርጊት፡ በቂ ማስረጃ ነው።

ከፍጥረት ልደት አንሥቶ፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ በጎውና ክፉው፡ እየታዩ መኖራቸው፥ ዛሬም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፡ ከእርሱ በፊት እንደነበሩት፡ እንደቀድሞዎቹ ትውልዶች፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ እያደረገ ያለው፡ ክህደትና ዓመፅ፥ የአምልኮ ምንዝርናም፡ እንደእንግዳ ነገር ተቆጥሮ፡ ሊያስደንቅ አይቻልም፤ ጥንቱም ቢኾን፡ መልካሙ በጎነትና ደግነት ብቻ ሳይኾን፡ መጥፎውና አጥፊው ክፉው ጭምር፡ ኹለቱም የሥነ ፍጥረት ገጽታዎች፡ በአዳምና በሔዋን ተከሥተው የታዩትና ተፈጽመው የተገኙት፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ ምድር ነውና።

በዚህ መሠረት፡ ፈጣሪ፡ ፍጥረታቱን ኹሉ፡ ኹለት ኹለት እያደረገና በኹለት ተቃራኒ ጾታዎች እየለየ የሠራቸው፡ ለበጎ እንጂ ለክፉ እንዳይደለ፡ በፈጣሪነት ባሕርዩና በግብሩ ፍጹም መልካምነት፡ አንድ ጊዜ ታውቋል፤ ይኸውም፡ ፍጡራኑ ኹሉ፡ እንደቀኝ እጅና እንደግራ እጅ፡ እንዲተጋገዙና እንዲደጋገፉ፥ ተባብረው፡ የሚፈልጉትን እንዲፈጽሙ፥ ያንዱን ጕድለት፡ ሌላው እንዲያሟላው፥ እንደብርሃንና ጨለማም፡ እንዲነጻጸሩና ህልውናቸውን ፍጹም መልካም እንዲያደርጉት፥ ከተለያየው ኹለት ጾታነታቸውም፡ መሰላቸውን ሕያው ፍጡር እንዲያስገኙ ሊያበቃቸው መኾኑን የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።

ብርሃን፡ በገላጭነቱ፥ ቀኝ፡ በብርታቱ፥ በግ፡ በየዋህነቱ፡ ሦስቱም ፍጡራን፡ ለመልካሙ ወገን ቢመሰሉ፥ በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ጨለማ፡ በዝግነቱ፥ ግራ፡ በድክመቱ፥ ፍየል፡ በብልጠቷ፡ ሦስቱም ፍጡራን፡ ለክፉው ወገን ቢመሰሉ፡ ከተፈጥሮ ባሕርይያቸው ምክንያት እንጂ፡ ኹሉም፡ የእግዚአብሔር ፍጡሮች የመኾናቸውን እውነተኛነት የሚለውጠው፥ ወይም፡ የሚሽረው፡ አንዳችም ነገር ከቶ የለም።

እነዚሁ፡ የዓለም ሰዎች፡ ከዚሁ፡ ከተዛባው የክፋት አስተሳሰባቸውና አዝማሚያቸው የተነሣ፡ በዚህ ረገድ የሚያናፍሱትንና የሚያካኺዱትን፡ ሌላውን ጎጂ አመለካከታቸውን፡ እዚህ ላይ፡ በተጨማሪ ማውሳት አግባብ ይኾናል። ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ በእርሱ የጊዜ አለካክ በሚመጠኑት፡ በስድስቱ ቀኖች ውስጥ የፈጠረውን፡ በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሰውን ፍጥረትና የማይንቀሳቀሰውን ተክል ኹሉ፡ የሠራቸው፡ እየራሳቸው መልካም ኾነው፥ ለመልካም ህልውናና ጥቅም መኾኑን የሚያረጋግጠውን፡ መለኮታዊ ቃሉን የሚቃረነው ድርጊታቸው ነው።

እግዚአብሔር፡ ዓለሙን በፈጠረበት ጊዜ፡ በእያንዳንዱ ቀን የሠራውን፡ "ወርእየ እግዚአብሔር፡ ከመ ሠናይ!"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ በዚያች ቀን የፈጠረው ፍጥረት፡ መልካም፡ እንደኾነ አየ!"፥ በመጨረሻውም፡ በስድስተኛው ቀን የፈጸመውን፡ "ወርእየ እግዚአብሔር፡ ኵሎ ዘገብረ፡ ከመ ጥቀ ሠናይ!"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ በስድስቱ ቀኖች የፈጠረውን ፍጥረት ኹሉ፡ እጅግ መልካም እንደኾነ አየ!" በሚለው፡ መለኮታዊ ቃሉ፡ ያዘጋጀውን ፍጥረት፡ በሙሉ፡ በአንድነት ያሞገሰውና የቀደሰው መኾኑን፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ እንዲህ አድርገው ይመሰክራሉ። (ዘፍጥ. ፩፥ ፩-፴፩።)

እውነታው ይህ ኾኖ ሣለ፡ ነገር ግን፡ እነዚሁ የዓለም ሰዎች፡ በአንድ በኩል፡ ከዚያ፡ እግዚአብሔር፡ "መልካም" አድርጎ ከፈጠረው ፍጥረት መካከል፡ ለምሳሌ፡ ስንዴንና ወይንን፥ በግንና ርግብን፡ ለእርሱ አምልኮ መፈጸሚያ፥ እንዲሁም፡ ንብን የመሰሉትን በራሪዎች ጨምሮ፡ ለሰው አገልግሎትና ጥቅም እንዲኾኑ፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔር እንደተፈጠሩ ይቈጥራሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ፡ ለምሳሌ፡ እንክርዳድን፥ ትምባሆንና ቡናን፡ የመሰሉት፡ አንዳንድ የአዝርዕት፥ የአትክልትና የዕፅዋት ዓይነቶች፡ ለዲያብሎስ አምልኮና አገልግሎት፥ ለክፉ፥ ወይም፡ ለመጥፎ ተግባር ብቻ እንዲውሉ፥ እንዲያውም፡ እነዚህን፡ ከላይ የተጠቀሱትን የዘር፥ የተክልና የዛፍ ዓይነቶችን የመሰሉትን ጨምሮ፡ ዝንብንና ቍራን የመሰሉት በራሪዎች ኹሉ፡ በራሱ፡ በዲያብሎስ እንደተፈጠሩ በማስመሰል፡ በገሃድ የሚነዙት የማሳሳቻ ቃል፡ በእጅጉ ያስገርማል።

ፈጣሪያችን፡ በእርሱ ፊት፡ እንስሳት፥ አራዊትና አእዋፋት፡ እንደሰው የሚታዩና ከሰው እኩል መኾናቸውን ሊያሳምነን፡ በሰማያት፡ "አርባዕቱ እንስሳት" ተብለው፡ ከሰው ጋር፡ መንበረ ጸባዖቱን እንዲሸከሙ የማድረጉ ምሥጢር ተዘንግቶ፡ ከአራዊት ወገን፡ ለምሳሌ፡ እመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በጫማዋ ውኃ ያጠጣችው ውሻ፡ እንደርኵስ፥ ድመት ደግሞ፡ እንደቅዱስ እየታዩ፡ በእነዚህ፡ የእግዚአብሔር ፍጡራን መካከል የሚካኼድ አስከፊና አሠቃቂ ልዩነት እንዳለ፡ ኹሉ የሚያውቀው ነው።

እዚህ ላይ፡ ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት፡ ቀደም ብለው፡ ለዓይነት ያህል፡ በምሳሌነት፡ ስለተጠቀሱት፡ እንክርዳድ፥ ትምባሆና ቡና ስለተባሉት የሣር ዘር፥ የተክል ቅጠልና የዛፍ ፍሬ ዓይነቶች፥ እንዲሁም፡ ስለውሻና ድመት፡ አጫጭር ሓተታን መስጠት አግባብ ይኾናል። እነዚህ፡ በደመ ነፍስ ተንቀሳቃሽ የኾኑ ፍጡሮችና የምድር በቀልቶች፡ እግዚአብሔር፡ ለፍጥረቱ ኹሉ ጥቅምና አገልግሎት ይውሉ ዘንድ ከፈጠራቸው፡ ሥፍር ቍጥር ከሌላቸው፡ በራሪና ሩዋጭ ፍጡራን፥ ልዩ ልዩ ዘሮች፥ ተክሎችና ዛፎችም መካከል የሚገኙ ፍጥረታት እንጂ፡ በተለይ፡ የሰብአዊ ፍጡሩን ጤንነት እንዲጎዱ፥ ወይም፡ ለባዕድ አምልኮ እንዲውሉ፥ ቅዱስ፡ ርኩስ ተብለውም እንዲደለደሉ፡ እግዚአብሔር፡ በተለይ፡ ለዚህ፡ የክፋትና የጥፋት ዓላማ፡ ኾን ብሎ የፈጠራቸው አይደሉም።

በዚህ ረገድ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከተናገራቸው ቃላት መካከል፡ አንደኛውን፡ ለማውሳት ያህል፡ "ኢተሀቡ ቅድሳተ፡ ለከለባት! ወኢትደዩ ባሕርየክሙ፡ ቅድመ አሕርው! ከመ ኢይኪድዎ በእገሪሆሙ፤ ወተመይጦሙ ይነፅሑክሙ፡፡"

ማለትም፡ "በእግራቸው፡ እንዳይረግጡት፥ ተመልሰውም እንዳይነክሷችሁ፡ የተቀደሰውን፡ ለውሾች አትስጡ! ዕንቈቻችሁንም፡ በእሪያዎች ፊት አትጣሉ!" ያለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ (ማቴ. ፯፥፮ ፡፡)

ጌታችን፡ በዚህ መለኮታዊ ቃሉ፡ "እሪያዎቹ፡ በእግራቸው እንዳይረግጡት፥ ውሾቹም፡ ተመልሰው እንዳይነክሷችሁ!" ብሎ፡ ቃሉን፡ እዚያው ተረጒመው እንጂ፡ "ውሻ ርኵስ ነው፤ ድመት ቅዱስ ነው፤" የሚል አስተሳሰብን አላመለከተም፡፡ "የሰው ልጆች" ናቸው፡ ይህን የመሰለውን ልዩነት ፈጥረው የደለደሉት፡፡ በጌታ ቃል፡ የተሰጠው ትምህርት፡- "ማናቸውም፡ የምታደርጉት ነገር፡ አለአግባብና አለቦታው እንዳይኾን ተጠንቀቁ!" ማለቱ መኾኑን፡ ለተናገረው ቃል፡ ራሱ፡ ጌታ የሰጠው ትርጓሜ ያስረዳል፡፡ ለቁም ነገሩማ፡ ቅዱስ ተብሎ፡ ወደቤተ መቅደስ እንዲገባ ከተፈቀለት፡ ከድመት ይልቅ፡ ውሻ፡ በአገልግሎቱና በአዋቂነቱ፥ በፍቅሩና በታማኝነቱ፥ በታዛዥነቱና በቻይነቱ፡ ከድመት ቀርቶ፡ ከሌላው፡ ከማናቸውም ፍጡር፥ ከሰውም ጭምር፡ ቢበልጥ እንጂ፡ የማያንስ መኾኑን፡ ፍጥረት በሙሉ የሚመሰክረው እውነታ አይደለምን?

ይህንንም እውነታ፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን፡ የእንስሳትንና የአራዊትን፥ የአእዋፋትንም ዓይነት ኹሉ የያዘች፥ በአራቱም ማዕዝናተ ዓለም የተዘረጋች ታላቅ ሸማን፡ በራእይ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ እያሳየ፡ "ኀርድ፥ ወብላዕ!" ማለትም፡ "አርደህ ብላ!" ብሎ ሲያዝዘው፡ "ሐሰ ሊተ እግዚኦ! ግሙራ ኢቦአ ርኩስ ውስተ አፉየ፤ ወኢበላዕኩ ዘኢኮነ ንጹሐ!" ማለትም፡ "ጌታ ሆይ! አይኾንም፤ አንዳች ርኵስ፡ ወደአፌ ገብቶ፥ የሚያስጸይፍም፡ ከቶ በልቼ አላውቅም፤" ባለው ጊዜ፡ "ዘእግዚአብሐር አንጽሓ፥ አንተ ኢታስተራኵስ!" ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ በንጽሕና፡ ለንጽሕና የፈጠረውን፡ አንተ አታርክሰው!" በሚል የግሣጼ ቃል ገላልጾ አብራርቶታል፡፡ (የሓዋ. ፲፥፲፪-፲፮ ፡፡)

ደግሞም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ፈክር ለነ፡ ምሳሌ ዘክርዳድ፥ ወዘሥርናይ፥ ወዘገራህት!" ማለትም፡ "የእንክርዳዱንና የስንዴውን፥ የእርሻውንም ምሳሌ ተርጉምልን!" ብለው ለጠየቁት ደቀ መዛሙርቱ፡

"ዘይዘርእ ሠናየ ዘርአ፡ ወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ፡፡ ወገራህቱኒ፡ ዓለም ውእቱ፡፡ ወሠናይኒ ዘርእ፡ ውሉደ መንግሥት እሙንቱ፡፡ ወክርዳድኒ፡ ውሉዱ ለእኩይ፡፡ ወፀራዊኒ ዘዘርኦ፡ ዲያብሎስ ውእቱ፡፡ ወማእረሩኒ፡ ኀልቀተ ዓለም ውእቱ፡፡ ወዓፀድኒ፡ መላእክት እሙንቱ፡፡"

ማለትም፡ "መልካም ዘርን የዘራው፡ የሰው ልጅ ነው፡፡ እርሻውም፡ ይህ ዓለም ነው፡፡ መልካሙም ዘር፡ የመንግሥት [የእግዚአብሔር] ልጆች ናቸው፡፡ እንክርዳዱም፡ የክፉው ልጆች ናቸው፡፡ የዘራውም ጠላት፡ ዲያብሎስ ነው፡፡ መከሩም፡ የዓለም መጨረሻ ነው፡፡ አጫጆችም፡ መላእክት ናቸው፡፡" ሲል፡ የሰጣቸው የመልስ ቃሉ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀንደኛ ጠላት የኾነው ዲያብሎስ፡ በዐረምነቱ፡ ሊጎዳ የሚችለውን፥ ለፍሬያማ ምግብነትም የማይጠቅመውን፡ "እንክርዳድ"ን፡ እንዴት፡ ለክፉ ሥራው መጠቀሚያ እንዳደረገው፡ ያስተማረበት ምሳሌ ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ ምን ትርጉም ሊሰጠው ይቻላል? (ማቴ. ፲፫፥፲፰-፴ ፡፡)

ይህ የጌታ ምሳሌና ከላይ የተጠቀሱት ቃሎቹ፡ ማንኛውም ፍጡር፡ ግዑዝም ኾነ ሕያው፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን ሌላውን፡ ማንኛውንም የፍጥረት አባል የኾነውን ወገን፡ ለደግ ወይም ለክፉ ዓላማ ዐውሎ ሊገለገልበት የሚችል መኾኑን ከመግለጽ ያለፈ ትርጉም ሊኖራቸው ከቶ አይችልም፡፡

የትንባሆም አገልግሎት፡ ከዚሁ ከእንክርዳዱ፡ የተለየ አይኾንም፤ ኹለቱም ቢኾኑ፡ በደመ ነፍስ ለሚንቀሳቀሱ ፍጥረታት ምግብነት፥ እንዲሁም፡ ለእነዚሁ ፍጡራንም ኾነ፡ ለሰው፡ በመድኃኒትነት እንዲያገለግሉ፡ "ለአንዳች በጎ ዓላማ የተፈጠሩ ናቸው!" ብሎ ከማመን በስተቀር፡ ሌላ ምን ሊባል ይቻላል?

ክፉዎቹ እንደሚሉት፡ እግዚአብሔር፡ "ለሰይጣናዊ ሥራ መጠቀሚያ የፈጠራቸው ናቸው!" ብሎ፡ መናገሩ ቀርቶ፡ ማሰቡ እንኳ፡ የፈጣሪን እውነተኛ ማንነት መካድ አይኾንምን? አዎን! በእርግጥ፡ እንደመካድ ይቈጠራል። ስለቡና ሊሰጥ የሚቻለውም ሓተታ ከዚህ የተለየ አይኾንም።

እንግዴህ፡ እንክርዳድንና ትንባሆን፥ ይልቁንም፡ ቡናን፡ "ለዲያብሎስ ብቻ መጠቀሚያ፥ ወይም፡ ለእርሱ መመለኪያ፥ ወይም፡ የእርሱ ድርሻ ይኹን!" ብሎ የበየነ ማነው? እንክርዳድንና ትምባሆን፥ ቡናንም፥ ዝንብንና ቁራንም፡ እንደማናቸውም ሌላው ፍጡር የፈጠረ፡ እግዚአብሔር ሲኾን፡ የእነዚህን ፍጡራን ፈጣሪነት፡ ለዲያብሎስ የሰጠው ማነው? ዲያብሎስ፡ ራሱ ፍጡር ስለኾነ፡ ፍሬ የሚሰጠውን የቡናን አንዲት ዛፍና እነዚህን ፍጡራን ይቅርና፡ አንዲቷን የሜዳ ሣር ቅጠል፥ ወይም፡ አንዲቷን የጹር ዓውሬ ጠጕር፡ እንኳንስ ፈጥሮ ማብቀል፥ ነጩን ጥቁር አድርጎ መለወጥ፥ ወይም፡ አንዲት ጋት ማሳደግ እንኳ አይችልም።

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው፡ ከአዝርዕት፥ ከአትክልትና ከዕፀዋት ዓይነቶች መከካል፡ ለሥጋና ለነፍስ፥ ለመንፈስም የዘለዓለም ሕይወት መውረሻ፥ በንስሓ፡ ለኃጢኣት ማስተስርያ፥ ከሞት መዳኛና ከደዌ መፈወሻ ኾኖ በመለኮታዊ መሥዋዕትነት ለሚቀርበው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ፡ ኅብስትና ጽዋ ይኾኑ ዘንድ የመረጣቸው፡ ስንዴና ወይን አሉ። የቡና ዛፍና ፍሬው፥ ሌሎቹም ከላይ የተጠቀሱት ፍጡራን ነገሮች እኮ፡ ከእነዚህ፡ ተለይተው የሚታዩ አይደሉም። ክፉዎች የሰው ልጆች፡ የስንዴውን ዳቦና የወይኑን ጠጅ፡ ለሰይጣኑም አምልኳቸው፡ መሥዋዕት አድርገው ያቀርቧቸው የለምን?

ለቅዱስ ቍርባንነት የሚቀርቡት፡ የስንዴው ኅብስትና የወይኑ ጭማቂ፡ ተለውጠው፡ ሥጋ መለኮትና ደመ መለኮት የሚኾኑትም እኮ፡ በካህኑ እና/ወይም በምእመኑ እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ አምልኮት ነው፤ አለዚያማ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የሚቀርበው ሃይማኖታዊውና ምግባራዊው አምልኮ፡ በኹለቱም ዘንድ ከሌለ እኮ፡ ያ ቍርባን፡ ቅዱስ መኾኑ ቀርቶ፡ ተራ ኅብስትና ተራ ጭማቂ ኾኖ የሚቀር አይደለምን?

በማዕጠንት መልክ፡ ለእግዚአብሔር አምልኮ የምናቀርባቸውና የምንጠቀምባቸው፡ ዕጣንና ከርቤ፥ ሌሎቹም የዛፍ ሽቱዎችስ፡ በእነዚሁ ክፉዎች ሰዎች፡ በአደባባይ፡ ለዲያብሎስና ለጣዖት አምልኮዎች ማካኼጃ መገልገያዎች ኾነው የሚሠራባቸው አይደለምን? እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! ስለምንድር ነው፡ እነዚሁ፡ የአምልኮ መገልገያዎች፡ ወደእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከመግባትና ለማዕጠንትነት ከመቅረብ የማይከለከሉት? ዕጣን፡ ለእግዚአብሔር አምልኮ የተመረጠው፡ በመልካምና ጣፋጭ መዓዛው ሲኾን፥ ትንባሆ ደግሞ የተጠላው፡ በሽታው ክርፋት እንጂ፡ ኹለቱም፡ እግዚአብሔር፡ ለበጎ የፈጠራቸው መኾኑ ተዘንግቶ፥ ወይም፡ ተሽሮ አይደለም።

እንደቅዱሳት መጻሕፍቱ ቃል፡ ፍጥረት ኹሉ፥ ዕፀዋት ጭምር፡ ከነፍሬዎቻቸው፡ ለመልካም የተፈጠሩ ለመኾናቸው፡ ማሳመኛው፡ በእግዚአብሔር የተፈጠረችው፡ ዕፀ በለስ እንኳ፡ ሰው፡ ፈጣሪው፡ "ሞትን ትሞታለህና፥ ከእርሷ፡ ፍሬዋን አትብላ!" ያለውን ተላልፎ፡ የዚችኑ ዛፍ ፍሬ በመብላቱ፡ ተጠቀመ እንጂ አልተጎዳም፤ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረበትን፡ የቀደመውን ደጉን ብቻ ሳይኾን፡ ክፉውን ጭምር ለማወቅ፥ እንዲሁም፡ በደግነትና በክፋት መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ እንዲያውቅ ለማድረግ ያስቻለች፥ በፈጣሪም አንደበት፡ "ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ!" ማለትም፡ ሰው፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" የሚለውን መለኮታዊ ውሳኔ ያስገኘች የዛፍ ፍሬ ናትና።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ይህን የተናገረ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተወልዶ፡ "ዘዚአነ ሞተ ነሥአ፤ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ። ...ሥጋነ ነሥአ፥ ወመንፈሶ ቅዱሰ ወሀበነ፡ ወረሰየነ ዕሩያነ ምስሌሁ፡ በብዝኀ ኂሩቱ።"

ማለትም፡ "የእኛን ሞት ለእርሱ ወሰደ፤ የእርሱንም ሕይወት ለእኛ ሰጠ። ...የእኛን ሥጋ፡ ለእርሱ ወሰደ፤ የእርሱንም ቅዱስ መንፈስ፡ ለእኛ ሰጠ፤ በቸርነቱ ብዛት፡ እንዲህ አድርጎ፡ ከእርሱ ጋር አስተካከለን።" እያልን፡ እናንተ እና እኛ፡ ዛሬ፡ በዘወትር ጸሎታችን፡ ደስ ብሎን፡ ፈጣሪያችንን እንድናመሰግነው ያደረገችን፡ የዚች ዕፀ በለስ ፍሬ ናት እኮ! (ከዓርብ ውዳሴ ማርያም።)

እርግጥ ነው፤ ፍጥረቱና ኹሉም የዛፍ ፍሬዎች፡ አገልግሎትና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው፡ በአግባብና በመጠን፥ አስፈላጊ ለኾነም ተግባር እንጂ፡ ከዚያ ውጪ ቢሠራባቸው፡ ሊጎዱ እንደሚችሉ፡ ከንብ የሚገኘውን ማርን እንኳ በምሳሌነት ብንጠቅሰው፡ የዚህን ነገር እውነተኛነት፡ በቀላሉ ሊያስገነዝበን ይችላል። ማር፡ በፍቱን መድኃኒትነቱ ይጠቅማል፤ መጥነው ቢበሉት፥ በውኃ በርዘውና ጠምቀውም፡ በመጠን ቢጠጡት፡ ለሰውነት ይስማማል፥ ጤንነትን ይሰጣል፤ በምግብነቱና በመጠጥነቱም፡ ይበጃል። አብዝተው ቢበሉት ግን፡ ከሕመም ያደርሳል፤ ጠጁንም፡ አድርቀው ቢጠጡት፡ ያሰክራል፤ ከጉዳትና ከሕመምም ያደርሳል። ቡናም፡ እንደዚሁ ነው፤ ከማር፥ ከወይንና ከዕጣን ተለይቶ ሊታይና ሊነቀፍ ሊከለከልና ሊወገዝ አይገባውም። ትንባሆም የማይፈለገው፡ ለጤንነት ጠንቅ ስለኾነ ነው።

ይህ፡ የዓለሙ ሰዎች ድርጊት፡ ዲያብሎስ፡ በትዕቢቱ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ የፈጣሪነትንና የፍጥረት ባለቤትነትን ማዕርግ በመፃረር፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ የሚያሳየውን የድፍረት ፉክክር፡ ሊያጠናክሩለት፡ እኒሁ ሰብአውያን አገልጋዮቹና ጭፍሮቹ የሚያካኺዱት፡ አንዱ፡ የሙከራና የጥረት ክፍል ነው። ይህም ሊኾን የቻለው፡ በተለይ፡ እኒሁ ሰዎች፡ ከየራሳቸው የሃይማኖት ጒድለትና ድክመት የተነሣ፡ በየስሜታቸው ውስጥ በፈጠሩት ፍላጎትና ምርጫ ምክንያት፡ ዲያብሎስ፡ በእነርሱ ላይ የአገዛዝ እውቅናንና የመፈራትን ኃይል፥ የሓሰት ሉዓላዊነትንና የባርነት አክብሮትን እንዲያገኝ ስላሠለጠኑት ብቻ ነው። ይህም፡ በእውነተኞች ዘንድ ስለሚታወቅ፡ ከዚህ ያለፈ ሓተታ አያስፈልገውም።

እናንተ እና እኛ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ለሰብአውያን፥ ለሌሎቹም ፍጡሮቹ ጥቅምና አገልግሎት እንዲውል የፈጠረውን፡ ቡናንና እርሱን የመሰሉትን የምድር ፍሬዎች፡ የሚጎዱንንና የሚበጁንን ለይተን በማወቅ፡ እንድንገለገልባቸውና እንድንጠቀምባቸው ከማድረግ በስተቀር፡ "ቡናን፡ ጠጡ! አትጠጡ!" በሚል ነገርና አተካራ፡ በየራሳችንም ኾነ፡ በሰዎች ምድራዊ ኑሮ ላይ፡ ሸክምና ችግር የሚፈጥሩ፥ ግራ የሚያጋቡና ለጥርጣሬ የሚዳርጉ አስተሳሰቦችን በማፍለቅ፥ ወይም፡ በመከተል፥ ወይም፡ በመከራከር፡ የቸሩ ፈጣሪያችንን በጎ ዓላማ መቃረን፥ ውድ ጊዜያችንንም፡ ማባከን አይገባንም።

ይህን ችግር በሚመለከት፡ መፍትሔ ይኾን ዘንድ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል፡ እስኪ፡ እዚህ ላይ ጠቅሰን እንመልከተው፡-

"ወኵሉ ይከውነኒ፤ ወኵሉሰ፡ አኮ ርቱዕ። ወኵሉ ብውሕ ሊተ፤ ወባሕቱ፡ አኮ፡ ኵሉ፡ ዘየሓንጽ። ኢታድልዉ ለርእስክሙ፡ ዘእንበለ ለቢጽክሙ። ወዓዲ፡ ኵሎ ዘይሠይጡ በምሥያጥ፡ ብልዑ፥ ወኢትሕትቱ፥ እስመ ለእግዚአብሔር ምድር፡ በምልዓ። ወለእመቦ ዘጸዋዐክሙ ዘኢየአምን፡ ወፈቀድክሙ ትሑሩ፡ ኵሎ፡ ዘአቅረቡ ለክሙ፡ ብልዑ፥ ወኢትሕትቱ። ወእመሰ ቦ ዘይቤለክሙ፡ 'እስመ ዝንቱ ዝቡሕ ለአማልክት!' ኢትብልዑ እንከ፡ በእንተ ዘይቤለክሙ፤ ወበእንተ ትሕዝብተ ቢጽክሙ።"

ማለትም፡ "ኹሉ ተሰጥቶኛል፤ ኹሉ ግን፡ የሚጠቅም አይደለም። ኹሉ፡ ተፈቅዶልኛል፤ ነገር ግን፡ ኹሉ፡ የሚያንጽ አይደለም። ለባልንጀራችሁ እንጂ፡ ለራሳችሁ አታድሉ! ዳግመኛም፡ በገበያ የሚሸጠውን ኹሉ፡ ሳትመራመሩ ብሉ! ምድርና በእርሷ ያለው ኹሉ፡ የእግዚአብሔር ነውና። ከማያምኑ ሰዎች መካከል፡ አንዱ ቢጠራችሁ፥ ልትኼዱም ብትወድዱ፡ የሚያቀርቡላችሁን ኹሉ፡ ሳትመራመሩ ብሉ! ማንም ግን፡ 'ይህ፡ ለጣዖት የተሠዋ ነው!' ቢላችሁ፡ እነሆ፡ ገልጸው ስለነገሩዋችሁና ስለባልንጀራችሁ ትዝብት ስትሉ፡ አትብሉ!" (፩ኛ ቆሮ. ፲፥ ፳፫-፳፰።)

በእነዚህና እነዚህን በመሰሉት፡ በሌሎቹ የእምነት አስተሳሰቦች ረገድ ሳይቀር፡ እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በሃይማኖታችን የምናረጋግጠው እውነታ ቢኖር፡ የሥነ ፍጥረት ፈጣሪና ባለቤት፡ ኹሉን የፈጠረው፡ እግዚአብሔር ብቻ መኾኑን ነው። ስለዚህ፡ ኹሉ፡ የእርሱ፡ የእግዚአብሔር ነው፤ ኹሉ፡ የኾነው፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔር ነው፤ ኹሉም፡ ለእርሱ፡ ለእግዚአብሔር ነው።

ይኹን እንጂ፡ ክፉዎች ሰዎች፡ በሃይማኖታቸው ጒድለት ምክንያት፡ በውስጣቸው ከተፈጠረባቸው፡ ጽኑ ፍርኀትና ጭንቀት፥ ስስትና ምኞት የተነሣ፡ ምን እንዳደረጉ መመልከት ነው፡-

የእግዚአብሔር ብቸኛ መብትና ሥልጣን የኾነውን፡ ይህን ፈጣሪነትና የሥነ ፍጥረት ባለቤትነት፡ ከእርሱ፡ ለመንጠቅ በመሞከር፡ በክፋትና በሓሰት፡ ለዲያብሎስና መሰሎቻቸው ለኾኑት፡ ለጭፍሮቹ ሰዎች፡ ከመዳረግ ደረሱ።

እነዚሁ ክፉዎች ሰዎች፡ በዚሁ፡ የስሕተትና የጥፋት ሥራቸው፡ የየራሳቸውን ምድራዊ ኑሮ፥ የሌሎችንም ደካሞችና አላዋቂዎች ሰዎች አኗኗር፡ እንዲህ አማስነው፡ ኹሉም፡ በዚያ ኑሮአቸው፡ በሥጋዊ አካላቸው፡ በምድር ላይ ሲሠቃዩበት ከቆዩ በኋላ፡ ፍጻሜያቸው፡ በሞት ፃዕር እንዲያበቃ፥ በነፍሳቸውም፡ ይኸው ሥቃይ እንዲቀጥል አድርገው፡ ለዚያ ዘለዓለማዊ ፍዳ ይዳርጉታል።

የእግዚአብሔር፡ የብቻ ገንዘቡ የኾነውን፡ ይህን ታላቅ መለኮታዊ መብትና ሥልጣን፡ ለዲያብሎስና መሣሪያዎቹ ለኾኑት ሰዎች ሰጥቶ፡ በየራሱ ላይ ያሠለጠናቸው፡ የዓለሙ ኅብረተሰብና የዚህ ኢትዮጵያዊ ትውልድ አባል የኾነው፡ ራሱ፡ እያንዳንዱ ሰው እንጂ፡ ማንም ያስገደደው ኖሮ አይደለም። ይኸውም፡ ፈጣሪውን፡ እግዚአብሔርን ትቶ፡ ራሱን፡ ለእነርሱ ለማስገዛት በየራሱ ፈቃድና ምርጫ፡ በመፈለጉና በመወሰኑ ብቻ መኾኑ፡ ሊካድ፥ ወይም፡ ሊታበል አይቻልም። ይህንም እውነታ፡ እግዚአብሔር እና ራሱ፡ ያ፡ የዓለሙ ኅብረተሰብ አባል፥ ወይም፡ ያ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ግለሰብ፡ የሚያውቁት ድርጊት ኾኖ፡ በእናንተ እና በእኛ፥ በዓለም ሕዝብም ፊት እንኳ ሳይቀር፡ ይኸው፡ በገሃድና በግዘፍ ተረጋግጦ ይታያል።

በተለይ፡ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ያ ፍላጎቱና ምርጫው፥ ያ ውሳኔውም፡ ያስገኘለትን መራራ ፍሬ፡ ቋቅ ቢለውም፡ በግዱ እየዋጠው መኾኑን፡ እናንተ እና እኛ ጭምር፡ እማኞች በኾንንበት፡ በዚህ ዘመን፡ ባገር ውስጥ ያለው፥ በውጭና በባሕር ማዶም የተበተነው፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ፡ የሚማቅቅበት "የልቅሶና ጥርስ የማፋጨት" ኑሮው፡ እየመሰከረበት ነው።

## ኹለተኛ፦ <u>የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መሰል የሌላት መልካም ስለመኾኗ፤</u>

እናንተ እና እኛ፡ ፈጣሪያችን በለገሠን የየግል የተፈጥሮ ተሰጧችንና በትምህርት ባገኘነው ሙያችን፡ እነሆ፡ በያለንበት፡ እያገለገልናት ያለችውን፡ ይህችን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት የመሰለች፡ እውነተኛና ትክክለኛ፡ የሕዝብ አመራርና የአገር አስተዳደር አቋም፥ ደግሞም፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና ድንግል ማርያምን የመሰሉ መሪዎች፡ ዓለም ከተፈጠረ እስከዛሬ፡ በምድር ላይና በሰዎች ዘንድ ሊኖሩ እንዳልተቻለ፥ ወደፊትም፡ እንደማይቻል፡ በማያወላውል ግልጽነት ተረጋግጧል።

ይህንም እውነታ፡ እኛ፡ ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ እየኖርን ያለነው፡ በቃላችን የምናረጋግጠው፥ እነዚያ፡ የቀደሙትም፡ በዜና መዋዕል መዛግብታቸውና በትውፊታቸው የሚመሰክሩት ነው። ይህን እውነታ፡ አሌ የሚል፡ ከሰዎች ቀርቶ፡ ከሰይጣናትም መካከል፡ አንድም ፍጡር ይገኛል ለማለት ያዳግታል።

ታዲያ! እውነታው ይህ ከኾነ፡ እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እያንዳንዳችን፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች፥ አገልጋዮችና ባለሥልጣኖች በመኾናችን፡ ይህ ብቻ፡ ራሱን የቻለ፡ "ልዩ የምሥራች ምንጭ" ኾኖን፡ "በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!" እንባባል ዘንድ አያበቃንምን? አዎን! በእርግጥ ያበቃናል።

ፍጥረተ ዓለሙ፡ ካለመኖር ወደመኖር መጥቶ፡ በአዳም ንጉሥነትና በሔዋን ንግሥትነት መተዳደር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬ፡ ሰዎች፡ በገዛ ፈቃዳቸውና ምርጫቸው፡ እየራሳቸውን፡ ከእግዚአብሔር መልካም ሕይወት አውጥተው፡ ወደሰይጣናዊው ክፉ አገዛዝ ቢያስገቡም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሉዓላዊው አመራርዋና አስተዳደርዋ፥ እንክብካቤዋና ጥበቃዋ ሳይጓደልና ሳይቋረጥ፡ በጸጥታና በሥርዓት የቀጠለ መኾኑ፡ ይኸው፡ በማይቃወሰውና በማይዛባው፥ በረጋውና በጸናው፡ የሥነ ፍጥረት ሕይወታዊ የህልውና ገቆ፡ ገሃድ ኾኖ ይታያል።

የመጨረሻዎቹና ዘለዓለማውያኑ አዳምና ሔዋን የኾኑት፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በአኹኑ የመንፈስ ቅዱስ ህልውናቸው፡ በመካከላችን የሚገኙት፡ በመንፈስ እንደመኾኑ መጠን፡ የዚችን፡ የመለኮታዊቷን መንግሥታቸውን መልካም አመራርና አስተዳደር፥ እንክብካቤና ጥበቃ፡ ዛሬ፡ በበላይነት እየተቈጣጠሩ የሚያካኺዱት፡ በመንፈስ ቅዱስ መኾኑ፡ በእናንተ እና በእኛ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በማንኛውም ምእመን ዘንድም፡ የሚታወቅ እውነታ ነው።

በዚሁ ምእመናዊ እውቀት ውስጥ የተጠቃለሉ፡ ሌሎች ሕያዋን ቍም ነገሮች አሉ፤ ከእነዚህም መካከል አንዱ፡ ራሷ መንፈስ የኾነችው ይህች የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ማደሪያዋ የሰው ልቦና ሲኾን፡ ያም ሰውነት፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ከእግዚአብሔር በመወለድ፡ ባገኘው፡ መንፈሳዊ ባሕርይና አካል፡ የሥጋና የነፍስ ባሕርያቱና አካላቱ፡ አንድ የኾኑበት፡ ሙሉና ፍጹም አካል መኾኑ ነው። ያም፡ ዛሬ፡ ሕያው ኾኖ፡ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውና በፊተኛው የትንሣኤ ሕይወት የሚኖረው፡ የእናንተ እና የእኛ ሰብአዊ አካል ነው።

ሌላው ደግሞ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም፡ በቀጥታ፡ በመንፈስ ቅዱስ እየመሩና እያስተዳደሩ፥ እየተንከባከቡና እየጠበቁ ያሉት፡ ከጥንት ጀምራ፡ እነርሱን፡ ማለትም፡ እናትና ልጇን፡ በእውነተኛ ማንነታቸው፡ ከነመንግሥታቸው፡ በሃይማኖት ተቀብላ፡ ሥርዓታቸውን፡ በምግባር እየፈጸመች ያለችውን፡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ብቻ አለመኾኑ ነው። በሥጋዊው፥ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው አካላቱና ባሕርያቱ፡ በምድር ላይ የሚኖረውን፡ ሕያዉንና ምውቱን የሚያካትተውን፡ ይህን ፍጥረተ ዓለም፥ የሰማያት ሠራዊትን ጭምር እንጂ።

የኢትዮጵያና የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪና አምላክ፥ ካህንና ሊቀ ካህናት፥ ንጉሥና ንጉሠ ነገሥት የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የኢትዮጵያና የፍጥረተ ዓለሙ ሃይማኖትና አገር፥ እናትና ንግሥት ከኾነችው፡ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ጋር፡ በመጨረሻው ትንሣኤ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በገሃድ ተገልጾ፡ ለሰብአዊው ፍጡሩ ያዘጋጀውን፡ የመልካም ህልውና አዲስ ሥርዓት የሚያውጅበት ቀን እንዳለ፡ እናንተ እና እኛ፡ እናምናለን።

እንዲህ ከኾነ፡ እኒህ ዘለዓለማውያኑ መሪዎቻችን፡ እንደቀድሞውና እንደዛሬው ኹሉ፡ እስኪዚያች ቀን ድረስ፡ ይህችኑ መለኮታዊት መንግሥታቸውን የሚመሩት፥ ሕዝባቸውንና ፍጥረታቸውንም የሚያስተዳድሩትና የሚጠብቁት፡ በመንፈስ ቅዱስ መኾኑን በሚያረግጥልን ሃይማኖታችን ጸንተን፡ በመልካሙ የገነት ህልውናችን እንቀጥላለን።

ይህንም እውነታ፡ እንዲህ የሚለው የዘወትሩ፡ የቃል ኪዳን ጸሎታችን ክፍል እያስታወሰ ያጠናክረናል፦ "ወእምድኅረ አጽንዖቱስ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ፡ ዘተወልደ እምድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት እምዛቲ ሥርው ምልዕት፡ <u>አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡</u> በፍጻሜ ዘመን ዘሕይወት፡ <u>በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ።"</u>

ማለትም፡ "በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና <u>ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።"</u>

አዎን! ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ ለሕዝባቸው፡ አባትና እናት፥ መልካም እረኛም ኾነው የሚመሩዋትና የሚያስተዳድሩዋት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንግዴህ፡ ይህች ናት።

<u>"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"</u> ተብላ፡ ላለፉት ፯ሺ፭፻፩ (ሰባት ሺህ አምስት መቶ አንድ ዓመታት) የነጻነት ዓመታት፡ ራሷን፡ በኩራትና በይፋ ምስክርነት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ስታስታውቅ የኖረች፥ ዛሬም ያለች፥ ወደፊትም፡ በመላው ዓለም ሰፍና ለዘለዓለም የምትኖረው፡ የእግዚአብሔርዋ መንግሥት፡ ይህች ናት።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የመሰሉት፡ የቅርቦቹና የቀደሙት ዘመናት ተጠሪዎቿ፥ ልጆቿና አገልጋዮቿ፡ በአጼነት ዙፋናቸው ላይ እያሉ፡ ሲያጠፉና ሲበድሉ፥ ይልቁንም፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት ወጥተው፡ በሥልጣን ሲባልጉ፡ አስቀድማ የምትመክራቸው፥ አልመለስ ሲሉም፡ የምትገሥፃቸውና የምትቀጣቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ይህች ናት።

በአጼዎቿ መሪነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ የክህደትንና የአምልኮ አመንዝራነትን ኃጢአት በመፈጸም፡ ያመፀ ትውልድ ሲነሣባትም፡ ትምህርቷንና ምክሩዋን፥ ተግሣፅዋንና ቅጣቷን፡ ለጣፋጩ ፍሬያማነት አብቅቶ፡ በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ተቀባይነት ባለው፡ በእውነተኛ አምልኮው፡ ንስሓ ሲገባ፡ ፍጹሙን ምሕረት አድርጋ፡ ወደነበረ ክብሩና ሥልጣኑ፥ ሰላሙና ብልጽግናውም የምትመልሰው፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ እነሆ፡ ይህች ናት።

ቃኤል፡ ደግ ወንድሙን፡ አቤልን፡ በክፋት ተነሣሥቶ በመግደሉ፡ መሰሎቹ ዘሮቹ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከመባል ይልቅ፡ "የሰው ልጆች" መባልን በመምረጣቸው፡ ዛሬ፡ በዚሁ ስያሜ፡ ተለይቶ የሚታወቀው፡ የፍጥረተ ዓለሙ ሰብአዊ ወገን፥ ይህን፡ የዘመኑን የኢትዮጵያን ትውልድ ጨምሮ፡ "አልቀበላትም!" ብሎ፡ በይፋ የጠላትና የጣላት፥ የተቃወማትና የካዳት፥ ያመፀባትና ያመነዘረባት፡ <u>የእግዚአብሔርዋ መንግሥት፡</u> ይህች ናት።

እርሷም፡ ይኸው፡ የፍጥረተ ዓለሙ ሰብአዊ ወገን፥ ጥንት፡ ከመነሻው ጀምሮ፡ በዲያብሎስ አበጋዝነት፡ ሲያደርግ እንደኖረው ኹሉ፡ ዛሬም ሊያጠፋት አሲሮ፡ በቍርጥ የተነሣሣባትና በሙሉ ኃይሉ የዘመተባት፥ እናንተ እና እኛ ብቻ ግን፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት እውነት የቆምንላት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት።

በአንድ ፊት፡ ዓለማውያን ግለሰቦች፡ ቀድሞም ኾነ፡ ዛሬ፡ የሰዎችን መንግሥት የመሪነት ሥልጣን ለመያዝ፥ ሕዝቦቻቸውም፡ ይህንኑ የሰዎችን መንግሥት የመሪነት ሥልጣን፡ ለእነዚሁ ግለሰቦች ለማስጨበጥ፡ ኹሉም፡ በየበኩላቸው፡ በኃይል፥ ወይም፡ የተለያዩ ፈሊጦችን በመፈልሰፍና የውድድር አንጃዎችን በማቋቋም፡ የሚያደርጉት ከባድ ትግል፥ ብርቱ ትንንቅና ኃይለኛ ጦርነት፥ የሚያጠፉት የሰብአዊ ሕይወት ብዛትና የሚያባክኑትም ከፍተኛ የገንዘብ መጠን፡ እነሆ፡ በገሃድ ይታያል።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም የሚመሩዋት የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በእነዚሁ፡ ዓለማውያን ግለሰቦችና ሕዝቦቻቸው ዘንድ ተገፍታና ተንቃ፥ ተጥላና ተጠልታ ትታያለች።

ይህን የተዛባ ኹኔታ፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው፡ የዛሬው ትውልድ፡ ባዕዳኑ አረማውያንና የአሕዛብ ቅሬቶች እያካኼዱ እንደሚገኙት ድርጊት ኹሉ፡ እርሱም፡ ከእነርሱ ጋር ግብረ አበር በመኾን፡ የራሱ የኾነችውንና የቀደሙት ወላጆቹ የተሠውላትን፡ ይህችን፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ገፍቷትና ንቋት፥ ጥሏትና ጠልቷት፡ ወደመጨረሻ ውድቀቱ ሲጓዝ፡ የሚመለከት አስተዋይ ታዛቢ ቢኖር፡ የቱን ያህል ያስገርመው!? ያሳዝነውም!?

ራሱ ፈጣሪ፡ በሰውነት ወደዚህ ዓለም ከመጣ በኋላ፡ በሕዝቡና በአሕዛብ መካከል ተገኝቶ ሣለ፡ ወደዚህ የዝቅጠት ማጥ ውስጥ ገብቶ የማሰነውን፡ ይህን፡ የሰዎችን፥ ይልቁንም፡ የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድ ድርጊት፡ መጪውን በሚያውቀው መለኮታዊ ባሕርዩ ተመልክቶ፡ የተናገረው አምላካዊ ቃል አለ፤ ያም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምንነትና ማንነት በሚመለከት፡ የዚህ ዓለም ሰዎች፡ በእርሷ ላይ ስላላቸው አስተያየትና ግምት፥ ከእነርሱ ስለሚደርስባት በደልና ስለሚፈጸምባትም ግፍ የሚገልጽ ነው።

ለዚህ አስተዛዛቢና መፈራረጃ ለኾነው፡ የሰዎችና የሕዝቦች፥ በተለይም፡ የኢትዮጵያዊው ትውልድ የተሳሳተ አስተሳሰብ፡ እውን መኾንና በሥራ መፈጸም፡ ማረጋገጫ የኾነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መሢሓዊ ቃል፡ እንዲህ ይላል፦

"አማን እብለክሙ! ...<u>እመዋዕለ ዮሐንስ መጥምቅ እስከይእዜ፡ ትትገፋዕ መንግሥተ ሰማያት፡ ወግፋዓን ይትማሰጥዋ።</u>"

ማለትም፡ "እውነት እላችኋለሁ! ...ከመጥምቁ ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በግፈኞች ትገፋለች፤ የተገፉትም ይናጠቋታል።" (ማቴ. ፲፩፥ ፲፪።)

እንግዲህ፡ “የሰው ልጆች” በሙሉ፥ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ጭምር፡ ፈጽመው ያልፈለጓት፥ እንዲያውም፡ በማይታበለው፡ በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፡ የገፏትና የናቋት፥ የጠሏትና የጣሏት፥ ነገር ግን፡ እናንተ እና እኛ ብቻ፡ እነሆ፡ ፈቃደኞች ኾነን፡ ዛሬ፡ በታማኝነት፡ እየኖርንባትና እያገለገልናት የምንገኘው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ይህች ናት።

እርሷም፡ አዎን! እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ በአዳምና በሔዋን መሥርቷትና አቋቁሟት፥ አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ አምነውባትና በቃል ኪዳን፡ ከፈጣሪያቸው ተቀብለዋት፡ እስከዛሬ፡ ለሰባት ሺህ አምስት መቶ አንድ ዓመታት ጠብቀዋትና አጽንተዋት ያቆዩዋት፥ ዛሬም፡ እናንተ እና እኛ፡ ከእነርሱ፡ ከቀደሙት የተረከብናት ናት።

እናንተ እና እኛ፡ **“በእንተዝ፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኀቤሁ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሥረ ተዋሕዶ።”**

ማለትም፡ **“ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።”** በሚለውና ከላይ፡ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው፡ በዘወትሩ የቅዱሱ ኪዳን ጸሎታችን፡ ያለማቋረጥ የምናሰማው የእምነት ቃል፡ ምን ይመስለናል?

የኢትዮጵያና በእርሷ ጸንታ የምትኖረው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የኹለቱም ህልውና፡ ዛሬ፡ በሕያውነት እየቀጠለ ያለው፡ በእያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊ ሰውነት መኾኑን፡ ለፈጣሪያችንና ለየራሳችን ብቻ ሳይኾን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ጭምር መመስከራችን አይደለምን? አዎን! በእርግጥ መመስከራችን ነው።

ከኹሉም ይልቅ፡ እናንተ እና እኛ፡ ለመለኮታዊው ጸጋ፡ የቱን ያህል የታደልን መኾናችንን አውቀን፡ እጅግ ደስ እንዲለንና ፈጣሪያችንን እንድናመሰግን፥ በየራሳችንም እርካታ እንዲሰማን የሚያደርግ፥ ልዩና ታላቅ የኾነ፡ የአንድ፡ የባለሙያነት ምግባር ባለቤቶች መኾናችንን አውቃችኋልን? አውቃችሁት ከኾነ፡ መልካም። ካላወቃችሁት ግን፡ ኹላችንም ልናውቀው ስለሚገባን፡ እንግለጽላችሁ! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡-

በአኹኑ ጊዜ፡ በሙላዋ የመሬት ገጽ ላይ የሚኖሩት የዓለም ሕዝቦችና አሕዛብ፡ በየወገናቸውና በየስማቸው፥ በየሃይማኖታቸውና በየፍልስፍናቸው፡ አገርና መንግሥት፥ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ እምነት ተብለው፡ ተቋቁመውና ተደራጅተው፡ የተቋቋሙበትንና የተደራጁበትን፡ የየራሳቸውን ሥጋዊ ዓላማና ምድራዊ ተግባር እያካኼዱ እንደሚገኙ ይታወቃል። ዳሩ ግን፡ ከእነርሱ መካከል፡ አንዳቸውም፡ “የእግዚአብሔር መንግሥት ነን!” ብለው፥ ወይም፡ ስሙን እንኳ ጠርተው የሚሠሩ እንደሌሉ፡ እነሆ፡ በይፋ ተረጋግጦ የሚታይ እውነታ ነው።

እንግዲህ፡ ይህን የመሰለው፡ የሰዎች ድርጊት፡ ተስፋፍቶ በሠለጠነበትና በሰፈነበት ኹኔታ ውስጥ ነው፡ እናንተ እና እኛ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ብለን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ ማለትም፡ በዚች ምድር ላይ ለሚርመሰመሰው፡ ለመላው ሰብአዊ ኅብረተሰብ፥ ለዓለም አህጉርና መንግሥታት፥ አብያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት ተቋማት፥ የእነርሱ ለኾኑት ድርጅቶችና ማኅበራት ኹሉ ጭምር፡ በይፋና በአዋጅ አሳውቀናት፡ እየኖርንባትና እያገለገልናት ያለነው።

የእግዚአብሔር እውነት፡ በእናንተ እና በእኛ ሰውነትና ሕይወት የገለጠችው፡ ይህ እውነታ፡ በእርግጥ ገዝፎ የሚታይ ድርጊት መኾኑን ሊያሳምን፡ እግዚአብሔር፡ በዘመናዊው የፍጡሩ ጥበብ በመጠቀም፡ በቸርነቱ ያደረገውን ድንቅ ሥራ ደግሞ፡ እስኪ በአትኵሮት እንመልከተው!

ይኸውም፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** የሚለው ስም፡ ለአገልግሎታችን መለያና መታወቂያ ኾኖ፡ እነሆ፡ በአለም አቀፉ አውታር ላይ፡ በጎዋው ሰሌዳ ተጽፎና ተሥሎ፥ ተዘርግቶና ተሠራጭቶ፡ ፍጥረተ ዓለሙ፡ እንዲያየውና እንዲያነብበው፥ እንዲቀርፀውና እንዲያትመው ማስቻሉና ማብቃቱ ነው።

በዚህ ችሎታና በዚህ ብቅዓት፡ እነሆ፡ አንድ ምሥጢር ተገለጠ። ያም ምሥጢር፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ፡ ቀደም ብለው፡ ከሚታዩት ታላላቅ ምልክቶች መካከል፡ አንዱና ዓይነተኛ የኾነው ምልክት፥ ዛሬ፡ ይኸው፡ በእናንተ እና በእኛ፡ ተፈጽሞ በተገኘው ሃይማኖታዊው ምግባር፡ እንዲከሠት ማድረጉ ነው።

እርሱም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመጨረሻውን ፍርድ ሊሰጥ፥ ይህን፡ በክፋቱ፡ ራሱን፡ ለጥፋት የዳረገውን፡ አሮጌ ዓለም ሊያሳልፍ፥ የእግዚአብሔር እውነትና ሰላም፥ ብልጽግናና ደስታ፡ በአዲስ የነጻነት ዓለም፡ በይፋ የሚሰፍኑባትንም፡ የዘለዓለም መንግሥቱን፡ ለፍጥረቱ ሊገልጥ፡ በትንሣኤ አካሉና በመለኮት ግርማው፡ ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያምና ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር፡ ወደዚች ምድር፡ ተመልሶ ለሚመጣባት ቀን፡ ቀዳሚ ማስጠንቀቂያና ማስታወቂያ የኾነው፡ አንዱ ምልክት ነው።

ይህን እውነታም፡ ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአትና ስለዓለሙ መጨረሻ፡ የዛሬ፡ ኹለት ሺህ አንድ ዓመት፡ በዘለዓለማዊው ጌታ፡ እንዲህ ሲል፡ የተነገረው፡ መሢሓዊ ቃል እያረጋገጠ ያጸድቀዋል። "**ወይሰበክ፡ ዝ፡ ወንጌለ መንግሥት፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፤ ከመ ይኩን ስምዐ፡ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ። ወይእተ አሚረ፡ ይበጽሕ ኅልቀት።**"

ማለትም፡ "**ይህ የ[እግዚአብሔር] መንግሥት ምሥራች፡ በአሕዛብ ኹሉ ላይ ምስክር ይኾንባቸው ዘንድ፡ በመላው ዓለም ይነገራል። በዚያን ጊዜም፡ መጨረሻው ይደርሳል።**" (ማቴ ፳፬፥ ፲፬።)

በዚህ መሢሓዊ ቃል መሠረት፡ በቅድስት ድንግል ማርያምና በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውን ምሥራች (ወንጌል)፡ <u>በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት</u> ስም፡ በዚህ፡ አገልግሎታችን፡ የጎዋ ሰሌዳ ላይ፡ ለመላው ዓለም ሕዝቦችና አሕዛብ እየተላለፈ መነገሩ፡ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአትና ለዓለሙ ፍጻሜ፡ ምልክት መኾኑን፡ ማመን፥ ወይም፡ አለማመን፡ ከዓለም ሕዝቦችና አሕዛብ መካከል ያለው፡ የየአንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ምርጫና ውሳኔ ነው።

እናንተ እና እኛ ግን፡ እርሱ፡ ዘለዓለማዊው መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "**ወበከመ ኮነ በመዋዕለ ኖኅ፡ ከማሁ፡ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ እጓለ እመሕያው።**"

ማለትም፡ "**የሰው ልጅ (የኢየሱስ ክርስቶስ) ዳግመኛ አመጣጥ፡ በኖኅ ዘመን እንደኾነው፡ እንደጥፋት ውኃ አመጣጥ ይኾናል።**" ሲል ባስጠነቀቀን መሠረት፡ ስለአመጣጡ፡ የቅድሚያ ምልክቶች፡ የነገረንን ቃሉን፡ እንደኖኅ አምነንና ተቀብለን፡ እየፈጸምነው ስለምንገኝ፡ ደስ ሊለን ይገባል። (ማቴ ፳፬፥ ፴፯።)

## ሦስተኛ፦ <u>ክርስቶስ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዳግም የመጣ ስለመኾኑ፤</u>

እንግዲህ ወዲህ፡ እግዚአብሔር፡ ለእናንተ እና ለእኛ፥ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፥ ለኢትዮጵያና ሌላውን ሰብአዊ ፍጡሩን ጨምሮ፡ ለመላው ፍጥረተ ዓለም፡ የሚያደርገው፥ ሳያደርገው የቀረ፥ ምንም መልካም ነገር፡ ፈጽሞ የለም። ከእርሱ የምንጠብቀው፥ የሚያስፈልገንም፥ ያልተሟላና የጎደለብን፡ አንዳች ነገር ከቶ የለምና። የቀረብን መልካም ነገር ኖሮ፡ "ይደረግልን!" ብለን፡ የምናቀርብለት፡ አንዳች ጥያቄ፥ ወይም፡ አንዳች ልመና፡ ከቶ የለም፤ ኹሉ ተመልሶልናልና፤ ኹሉ፡ ተሰጥቶናልና፤ ኹሉ ተፈጽሞልናልና።

ኹሉ፡ ኾኖልናል፤ ኹሉ፡ ተደርጎልናል፤ ኹሉን አግኝተናል፤ ኹሉን ኾነናል፤ እርሱን፡ እግዚአብሔርን እስከመምሰልና እስከመኾን ደርሰን በቅተናል፤ ልጆቹና የዘለዓለማዊት መንግሥቱ ባለቤቶች ኾነናል፤ በእርሱ፡ የክህነትና የንግሥ ቅብዓትን ተቀብተን፡ ካህናት፥ ነገሥታትና ንግሥታት ኾነናል። ያልኾንነውና የቀረብን መልካምነት፡ ምን አለ? ምንም የለም።

ስለዚህ እኮ ነው፡ ለእርሱ ለፈጣሪያችንና ለቅድስት እናቱ የምናቀርባቸው የውዳሴና የቅዳሴ ጸሎቶቻችንና ዝማሬዎቻችን ኹሉ፡ ልመናና ጥያቄ ሳይኖርባቸው፡ በምስጋና ቃላት ብቻ ተመልተው የሚገኙት! ስለዚህም እኮ ነው፡ እናንተ እና እኛ፡ በፊተኛዪቱ ትንሣኤ የምትገኘውን የገነት ሕይወትን፡ ዛሬ፡ እየኖርናት ስለኾንን፡ እንደሌሎች ሰዎች እምነት፡ ነፍስ፡ ከሥጋ ተለይታ፡ የዚህ ዓለም ህልውናዋ የሚያበቃበትን የሞት ጽዋን የማንጠብቀው!

ልዑል እግዚአብሔር፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት ያሳየውን አማናዊ ሕልም ኹሉ፥ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተፀንሶ በተወለደ ጊዜ፡ ፈጽሞታል፤ የገለጸውን ራእይ ኹሉ፡ እውን አድርጎታል፤ የሰጠውን መለኮታዊ ተስፋ ኹሉ፡ ከውኖታል፤ ያናገረውን ትንቢት ኹሉ፡ አሟልቶታል፤ የገባውን ቃል ኪዳን ኹሉ፡ ለጣፋጩ ፍሬያማነት አብቅቶታል። ኹሉንም፡ በመጨረሻ፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዘለዓለማዊ ምሕረትነት አትሞታል። በቃ!

ትስብእቱ፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር ሰው የመኾኑ ትንግርት፡ የዛሬ ኹለት ሽህ አንድ ዓመት፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል አንደበት በተነገረውና በእግዚአብሔር እናት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ጆሮ በተሰማው ምሥራች ከተፈጸመባት፡ ከዚያች ቅጽበት ወዲህ፥ ተያይዞም፡ እርሱ፡ ሰው ኾኖ ከተናገረውና ካስተማረው ቃሉ፥ ካሳየውና ካደረገው ተአምራቱ በቀር፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ሌላ የሚታይ ሕልም የለም፤ የሚገለጽ ራእይ የለም፤ የሚሰጥ ተስፋ የለም፤ የሚነገር ትንቢት የለም፤ የሚደረግ ቃል ኪዳን የለም። ኹሉም፡ ለአንዴ እና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለም አብቅቷል።

ከዚህ የተነሣ፡ አዎን! እንግዲህ ወዲህ፡ ከቸሩ ፈጣሪያችን የምንጠብቀው፥ የቀረንና የሚያስፈልገን አንድም በጎ ነገር የለም፤ እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ማንነቷና ምንነቷ፡ ከላይ፥ ቀደም ብሎ ተብራርታ የተገለጸችው፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት አባሎችና አገልጋዮች፥ ዜጎቿም ስለኾንን፡ በበጎው ተልእኳችን ጸንተን በመቀጠል፡ ይህችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ያበረከተችልንን፡ በምድር ላይ፡ በአካለ ሥጋ እያለን፡ መልካሙን የትንሣኤና የገነት ሕይወት ከመኖር በስተቀር።

ለዚህ እውነታ፡ ማለትም፡ በጥንተ ፍጥረት፡ በሕይወት ዛፍ ፍሬ የተመሰለው፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስና በራሷ፡ በሕይወት ዛፍ የተመሰለችው፡ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ይህችን፡ የምንኖርባትንና የምናገለግላትን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንዲህ አድርገው፡ ለዚህ ፍጹም መልካምነትና የሕይወት ገነትነት ያበቋት ለመኾኑ፡ የሚቀርቡ አያሌ ምስክሮችና ማስረጃዎች ሊኖሩ ይቻላል፤ ተጨባጭ ማረጋገጫዎች ከኾኑት ከእነዚህ መካከል፡ ቀዳሚውና ዋነኛው ተጠቃሽ ግን፡ "ኢትዮጵያ" የተባለችው እናት አገራችንና "ልጆቿም፥ ሕዝቦቿም" የኾንነው፡ እናንተ እና እኛ፡ በአገርነት፥ በሕዝብነትና በመንግሥትነት፡ የኖርንበት፥ እየኖርንበትም ያለነው፡ <u>የሰባት ሺህ አምስት መቶ አንድ ዓመታት የነጻነት ህልውናችን</u> ኾኖ ይገኛል።

ስለዚህ፡ እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግመኛ ምጽአት እንኳ አንጠብቅም። ለእናንተ እና ለእኛ፡ ከቅድስት እናቱ ጋር፡ አንድ ጊዜ፡ በመንፈስ ቅዱስ መጥቶልን፡ እነሆ፡ እናትና ልጁ፡ ኹለቱም፡ ዘወትር፡ በየአፍታዋ ሳይለዩን፡ አብረውን እየኖሩ ናቸውና። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደሰማያዊ ዙፋኑ ባረገ፡ በአሥረኛው ቀን፡ መለኮታዊ ሕይወቱ በኾነው በመንፈስ ቅዱስ መልክና አካል ተመልሶ፡ በእያንዳንዳቸው፡ በሓዋርያት ላይ፡ በእሳት ላንቃ ቅርጽ በመውረድ፡ ከተዋሓዳቸው ቅጽበት ጀምሮ፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ ዳግመኛ መጥቶልን፡ እነሆ፡ ለፊተኛው የትንሣኤ ዕድል ስላበቃንና በዚያ የትንሣኤ ሕይወት እንድንኖር ስላደረገን፡ አዎን! እናንተ እና እኛ፡ የክርስቶስን ዳግም ምጽኣት አንጠብቅም።

ይህንም እውነታ፡ "ወአውጻእከነ እመንሱት ዘዘዚአሁ፤ ወአድኃንከነ እምኵሉ እኩይ፤ ወሞዕክዎ ለዲያብሎስ፥ ወአሰሰልከ ለሞት፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ <u>አሠለጥከነ ንሄሉ፡ በሕይወተ ትንሣኤከ።</u>"

ማለትም፡ “ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን÷ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን፡፡” በሚለው፡ በዘወትሩ፡ የምስጋና ጸሎታችን፡ እናንተ እና እኛ፡ በበኩላችን አረጋግጠነዋል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍትም፡ እንዲህ በሚለው የእግዚአብሔር ቃላት ይመሰክሩለታል፡- “በአርብዓ ዕለት፡ እንዘ ያስተርእይዎሙ÷ ወይዜንዎሙ÷ ወይነግሮሙ፡ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ...አዘዞሙ፡ ኢይፃኡ እምኢየሩሳሌም፤ አላ፡ ይጽንሑ፡ ተስፋሁ ለአብ፡፡ ...ወይቤሎሙ፡ ...'ሶበ ይወርድ ላዕሌክሙ መንፈስ ቅዱስ፡ ትነሥኡ ኃይለ፤ ወትከውኑኒ ሰማዕትየ በኢየሩሳሌም÷ ወበኵሉ ይሁዳ÷ ወሰማርያ÷ ወእስከአጽናፈ ምድር፡፡'”

ማለትም፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለሐዋርያት፡ “ለአርባ ቀኖች ተገልጦ እየታያቸው÷ ስለእግዚአብሔር መንግሥት እያበሠራቸውና እየነገራቸውም ሣለ፡ ...የአብን ተስፋ ደጅ እየጠኑ እንዲቆዩ እንጂ፡ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፡፡ ...'ነገር ግን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በላያችሁ በወረደ ጊዜ፡ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም÷ በይሁዳና በሰማርያ÷ እስከምድር ዳርቻም ኹሉ፡ ምስክሮቼ ትኾናላችሁ!' አላቸው፡፡” (የሐዋ. ፩÷ ፫-፰፡፡)

ደግሞም፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመስቀል መከራውና ትንሣኤው አስቀድሞ፡ እንዲህ አላቸው፡- “ወናሁ እብለክሙ፡ ከመ አነ አሐውር፤ ወአስተዳሉ ለክሙ መካነ፤ ...ወእምከመ ሖርኩ÷ ወአስተዳሎኩ ለክሙ፡ መካነ÷ ወምዕራፈ÷ ወማኀደረ፡ እመጽእ ካዕበ÷ ወእነሥአክሙ ኀቤየ፡ ከመ ተሀልዉ አንትሙኒ፡ ኀበ ሀሎኩ አነ፡፡

“...አማን አማን እብለክሙ፤ ዘየአምን ብየ፡ ግብረ፡ ዘአነ እገብር፡ ውእቱኒ ይገብር፤ ወዘየዓቢ እምኔሁ ይገብር÷ እስመ አነ አሐውር ኀበ አብ፡፡ ...ወአነ እስእሎ ለአብ፡ ይፈኑ ለክሙ ጰራቅሊጦስሃ ካልአ፡ ዘይሄሊ ምስሌክሙ ለዓለም፤ መንፈሰ ጽድቅ፡ ዘኢይክል ዓለም ነሢኦቶ፡ እስመ ኢይሬእዮ÷ ወኢየአምሮ፡፡ ወአንትሙሰ፡ ተአምርዎ፤ እስመ ኀቤክሙ ይነብር፤ ወውስቴትክሙ ይሄሉ፡፡

“ወኢየኀድገክሙ፡ እጓለ ማውታ ትኩኑ፤ እስመ አነ እመጽእ ኀቤክሙ፡፡ እምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል፡ ኢይሬእየኒ እንከ ዓለም፡፡ ወአንትሙሰ ትሬእዩኒ፤ እስመ አነ ሕያው፤ ወአንትሙሂ ተሐይዉ፡፡ ይእተ አሚረ፡ ተአምሩ፡ ከመ አነ በአብ፤ ወአብ፡ ብየ፤ ወአንትሙሂ፡ ብየ፤ ወአነሂ፡ ብክሙ፡፡ ...ዘያፈቅረኒ፡ ይዕቀብ ቃልየ፡፡ ወያፈቅሮ አቡየ፡፡ ወእመቦ፡ ዘዓቀበ ቃልየ፡ አነ÷ ወአቡየ ንመጽእ በኀቤሁ፤ ወንገብር ምዕራፈ ውስቴቱ፡፡

“...ወዘንተ ነገርኩክሙ፡ እንዘ ሀሎኩ ምስሌክሙ፡፡ ወባሕቱ፡ ጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ፡ ዘይፌኑ አብ በስምየ፡ ውእቱ ይሜህረክሙ ኵሎ፤ ወያዜክረክሙ ኵሎ፡ ዘነገርኩክሙ አነ፡፡ ...ወሶበ መጽአ ጰራቅሊጦስ፡ ዘአነ እፌኑ ለክሙ እምኀበ አብ፡ መንፈሰ ጽድቅ፡ ዘይወጽእ እምኀበ አብ፡ ውእቱ ሰማዕትየ፡፡ ወአንትሙሂ ሰማዕትየ÷ እስመ እምትካት፡ ሀለውክሙ ምስሌየ፡፡”

ማለትም፡ “እነሆ፡ እላችኋለሁ፤ ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ፡ እኔ እኼዳለሁ፡፡ ...ኼጄም፡ ለእናንተ የሚኾነውን ሥፍራ÷ ማረፊያና ማደሪያ አዘጋጅቼላችሁ፡ ዳግመኛ እመጣለሁ፤ እኔ ባለሁበት፡ እናንተም፡ ትኖሩ ዘንድ፡ ወደእኔ እወስዳችኋለሁ፡፡

“...እኔ፡ ወደአብ በመኼዴ፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርገዋል፤ ከዚያም የሚበልጥ ያደርጋል፡፡ ...እኔም፡ አብን እለምናለሁ፤ ለዘለዓለም፡ ከእናንተ ጋር እንዲኖር፡ ሌላ አጽናኝ ይልክላችኋል፡፡ እርሱም፡ ዓለም፡ የማያየውና የማያውቀው ስለኾነ፡ ሊቀበለው የማይቻለው፡ የእውነት መንፈስ ነው፡፡ እናንተ ግን፡ ታውቁታላችሁ፤ በእናንተ አድሮ ይኖራልና፤ በመካከላችሁም ይገኛልና፡፡

“እንደሙት ልጆች ትኾኑ ዘንድ፡ አልተዋችሁም፤ እኔ፡ ወደእናንተ እመጣለሁና፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ዓለም፡ እንግዴህ ወዲህ አያየኝም፡፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ÷ እኔ፡ ሕያው ነኝና፤ እናንተም፡ ሕያዋን ትኾናላችሁ፡፡ በዚያን ጊዜም፡ እኔ፡ በአብ እንዳለሁ÷ አብም፡ በእኔ እንዳለ÷ እናንተም፡ በእኔ እንዳላችሁ÷ እኔም፡ በእናንተ እንዳለሁ ታውቃላችሁ፡፡

"...የሚወድደኝ፡ ቃሌን ይጠብቅ! አባቴም ይወድደዋል፡፡ ቃሌን የጠበቀ ቢኖር፡ እኔና አባቴ፡ ወደእርሱ እንመጣለን፤ እርሱንም፡ መኖርያችን እናደርገዋለን፡፡

"...ይህንም፡ ከእናንተ ጋር ሣለሁ፡ ነገርኋችሁ፡፡ ነገር ግን፡ አብ፡ በስሜ የሚልከው፡ አጽናኝ፡ የእውነት መንፈስ፡ እርሱ፡ ኹሉን ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ኹሉ ያስታውሳችኋል፡፡ ...እኔ፡ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ÷ እርሱም፡ ከአብ የሚወጣ፡ የእውነት መንፈስ፡ በመጣ ጊዜ፡ እርሱ፡ ስለእኔ ይመሰክራል፡፡ እናንተም፡ ከመጀመሪያው፡ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና፡ ስለእኔ ትመሰክራላችሁ፡፡" (ዮሐ. ፲፬÷ ፳-፫፤ ፳፬-፳፮፤ ፲፭÷ ፳፮-፳፯፡፡)

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እንኳንስ፡ ዛሬ፡ በፊተኛው የትንሣኤ ሕይወት በሚኖሩበት፡ በኪዳነ ምሕረቱ ዘመን ይቅርና፡ ጥንት፡ ከፍጥረት ልደት አንሥቶም ቢኾን፡ በሃይማኖትና በአምልኮ፡ ከፈጣሪያቸው ጋር፡ ያለማቋረጥ፡ አብረው ስለኾኑ፡ በመንፈስ ቀርቶ፡ በነፍስና በሥጋ እንኳን፡ ለቅጽበት፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከቶ፡ ተለይተው ኖረው አያውቁም፡፡

ስለዚህ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመለኮታዊው አባቱ፡ በእግዚአብሔር አብ ግርማና ምስጋና÷ በንግሥታዊ ክብርዋና ሞገሷ፡ በቀኙ ከምትቀመጠው፡ ከሰብአዊት እናቱ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር፡ ዳግመኛ የሚገለጥበት ምጽአቱ፡ ለማያምኑ "የሰው ልጆች" እንጂ፡ የቀደሙት ቅዱሳን አባቶቻቸውና ቅዱሳት እናቶቻቸው፡ ነቢያትና ሐዋርያት÷ ጻድቃንና ሰማዕታት÷ ወንዶችና ሴቶች፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ኾነው፡ ለደረሱበት ሕይወት፡ እየራሳቸውን ላበቁት፡ እናንተን እና እኛን ለመሰሉት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አይደለም፡፡

እርሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም÷ ቅዱሳንና ቅዱሳት ባለሚሎቻቸው፡ ነቢያትና ሐዋርያት÷ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ መላእክትና ሊቃነ መላእክት፡ ኹሉም፡ ከእናንተ እና ከእኛ፡ የሚፈልጉትና የሚጠብቁት፡ ምን እንደኾነ÷ ባለፈው፡ የደከሙትና የተሠዉት÷ አኹንም፡ ያለማቋረጥ እየጸለዩ ያሉት፡ ለምን እንደኾነ፡ እንደተረዳችሁት እናምናለን፡፡ ይኸውም፡ እናንተ እና እኛ ብቻ ሳንኾን፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ጭምር÷ ኹላችንም፡ እንደነርሱ ኾነን፡ እነርሱ ደርሰውበት ለተቀዳጁትና ለሚኖሩበት፡ ለመጨረሻው ዘለዓለማዊ መልካም ሕይወት እንድንበቃላቸው እንጂ፡ ሕይወተ ሥጋችንን ሙሉ፡ "አማልዱን!" በማለት ብቻ ዕድሜያችንን እንድንጨርስ አለመኾኑን ነው፡፡ መለኮታዊ ምሕረቱንማ፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ሰው ኾኖ፡ በፈጸመው ቤዛነቱ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም የዘለዓለም ኪዳንነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ጨርሶ አድርጎልን የለምን?

እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከፈጣሪያችንና ከአምላካችን ከእግዚአብሔር፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በተስፋ የምንጠብቀው÷ የምንመኘውም፡ አንዳችም አዲስ ነገር ከቶ የለም፡፡ የምንጠብቀው ቢኖር፡ አንድ ነገር ብቻ ነው፤ እርሱም፡ ያ፡ የምጽአቱ ጊዜ ደርሶ፡ የመጨረሻው መለኮታዊ ፍርድ፡ በማያምኑት ላይ እንዲፈጸም ያደርግ ዘንድ፡ ቸሩ ፈጣሪያችንን፡ በምስጋና ጸሎታችን መማለድ ነው፡፡ ይህንም ምልጃችንን፡ እንዲህ የሚለው፡ የዘወትሩ የምስጋና ጸሎታችን ይገልጠዋል፡-

"ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ፡ ትኄንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዘተብህለ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"፤ እለ ንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፡ ከመ ትትረአይ ወትሰፍን በገሃድ፡ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሜርዎሙ ለእከይ÷ ወለኃጢአት÷ ወለሞት፡፡ እስመ ለከ፡ ኃይል÷ ወስብሐት÷ ወመንግሥት፤ ይእዜኒ÷ ወዘልፈኒ÷ ወለዓለም ዓለም፤ አሜን፡፡"

ማለትም፡ "'ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ' በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን÷ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን፡፡

*ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ የአንተ ናቸው፤ ዛሬም፤ ዘውትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።።"*

በዚያ፡ ምጽአቱ ጊዜ፡ በፌተኛዪቱ ትንሣኤ ሕይወት ውስጥ የምንኖር፡ እናንተ እና እኛ፡ ምን፥ ወይም፡ እንዴት እንደምንኾን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በሓዋርያው አንደበት የተናገረውና የጻፈው፡ እንዲህ የሚለው ቃል ያስረዳናል፦

*"ወዘንተ ንነግረክሙ በቃለ እግዚአብሔር፤ ንሕነ ሕያዋን፡ እለ ንተርፍ፡ አመ ምጽአተ እግዚእነ፡ ኢንበጽሖሙ ለሙታን። እስመ ይኤዝዝ እግዚእነ፡ ምስለ ሊቀ መላእክት፤ ወንፍሓተ ቀርን ዘእግዚአብሔር፥ ዘይወርድ እምሰማይ። ወይትነሥኡ ምውታን መቅድመ፡ እለ ሞቱ በሃይማኖተ ክርስቶስ። ወእምዝ፡ ንሕነ ሕያዋን፡ እለ ንተርፍ፡ ንትመሠጥ በደመና ምስሌሆሙ ኅቡረ፡ ከመ ንትቀበሎ ለእግዚእነ ውስተ አየር፤ ወንሄሉ እንከ ዘልፈ ኀበ እግዚእነ። ወይእዜኒ፡ መሀሩ ቢጸክሙ፡ ዘንተ ነገረ።።"*

*ማለትም፡ "በእግዚአብሔር ቃል የምንላችሁ፡ ይህ ነው፦ በጌታችን ምጽአት ጊዜ፡ ሕያዋን ኾነን የምንገኝ እኛ፡ ያንቀላፉትን አንቀድምም። ጌታችን ራሱ፡ በትእዛዝ፥ በመላእክትም አለቃ ድምፅ፥ በእግዚአብሔርም መለከት፡ ከሰማይ ይወርዳልና። በክርስቶስ አምነው ያንቀላፉቱ፡ አስቀድመው ይነሣሉ። ከዚያ በኋላ፡ እኛ፡ በሕይወተ ሥጋ ቀርተን ያለነው፡ ጌታችንን በአየር ላይ ለመቀበል፡ ከእነርሱ ጋር አብረን፡ በደመና ተነጥቀን እንመጠቃለን። እንግዴህም፡ ኹልጊዜ፡ በጌታችን ዘንድ እንኖራለን። አኹንም፡ እናንተ፡ ይህን ነገር፡ ለባልንጀሮቻችሁ አስተምሩ።።"* (፩ተሰ. ፬፥ ፲፭-፲፰።)

## አራተኛ፦ <u>በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ዲያብሎስ፡ ሽባ ስለመኾኑ፤</u>

እንደእግዚአብሔር ቃል፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ የ፩ሺህኛው ዓመታት ዘመን ተፈጽሞ፡ የ፪ሺህኛው ዓመታት ዘመን በባተበት (በገባበት)፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ ከመለኮታዊው እሥራት፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው፡ "የቀደመው እባብ፥ ዘንዶ፥ ሰይጣን" የተባለው ዲያብሎስ፡ የሚሰፍንባቸውና የሚሠለጥንባቸው ወገኖች አሉ። እነዚህም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑት፥ ደግሞም፡ "አምነናል!" ብለው፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የማያመልኩት፥ እንዲሁም፡ በአራቱም በምድር ማዕዘናት የሚኖሩት፡ አረማውያንና አሕዛብ ናቸው። ይህም፡ በእናንተ እና በእኛ ዘንድ፡ የታወቀ፡ የሃይማኖታችን እውነታ ነው።

እናንተንና እኛን በሚያካትተው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ላይ ግን፡ ይኸው፡ የተፈታው ዲያብሎስ፡ አንዳች ሥልጣንና ኃይል ኖሮት፡ በምንም ዓይነትና መንገድ፡ ሊጎዳቸው አይቻለውም። ሊጎዳቸው የማይቻለውም፡ ያለምክንያት አይደለም። እነርሱ፡ ማለትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ጠብቀውና አጽንተው ከሚኖሩበት፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውና የቃል ኪዳን ምልክቶቻቸው የተነሣ፡ የቅዱሱ ኪዳን ማኅተም፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ፡ በየግንባራቸው ላይ ስለታተመ ነው።

"ዘእንበለ ለሰብእ፡ እለ አልቦሙ ማኅተመ እግዚአብሔር፡ ውስተ ፍጽሞሙ!" ማለትም፡ "የእግዚአብሔር ማኅተም፡ በግምባራቸው ከሌለባቸው ሰዎች በቀር፡" የሚለው አምላካዊ የዋስትና ቃል የሚጸናባቸው፥ ማለትም፡ የዲያብሎስ ሥልጣንና ኃይል የሚሰፍንባቸውና የሚሠለጥንባቸው ሰብኣውያን ወገኖች፡ ቅዱሱ የእግዚአብሔር የኪዳን ማኅተም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በየግምባራቸው ባልታተመባቸው ላይ ብቻ በመኾኑ ነው። እኒህም፡ ካለማመናቸው የተነሣ፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ በየልባቸው ጽላት ያልተጻፈባቸው፥ የማኅተም ምልክቶቹንም፡ በሃይማኖት ያልተቀበሉና በምግባር ያልፈጸሙ፡ "የሰው ልጆች" ናቸው። (ራእ. ፱፥ ፬፤ ፳-፳፪።)

ከሺህ ዓመት እሥራቱ፡ ለጥቂት ጊዜ ከተፈታው ከዲያብሎስ፡ የጥፋት ኃይል ተለይቶ ሊያመልጥ፥ ከማናቸውም ዓይነት ሰይጣናዊ ጉዳትም ኹሉ ተጠብቆ ሊድን የሚችለው ሰብአዊ ፍጡር፡ ማን እንደኾነ፡ በእግዚአብሔር ቃል፡ በግልጽ ተነግሮአል።

ይኸውም፡ “ዘአምነ፥ ወዘተጠምቀ ይድኅን! ወዘሰ ኢአምነ፡ ይደየን!” ማለትም፡ “*ያመነ፥ የተጠመቀ ይድናል፡፡ ያላመነ ግን፡ ይፈረድበታል፡፡*” በሚለው መለኮታዊ ቃል መሠረት፡ ሰባቱን፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት አጠቃልሎ በያዘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አምኖና ተጠምቆ፥ ይህንኑ ሃይማኖቱን፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮው፡ በምግባር የሚፈጽም ሰብአዊ ፍጡር ብቻ መኾኑ ነው፡፡ (ማር. ፲፮፥ ፲፮፡፡)

ይኸም የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ አረማውያንና አሕዛብ፥ አይሁድና እስላማውያን፥ ክርስቲያኖችና “ኢትዮጵያውያን ነን!” የሚሉት እንኳ ሳይቀሩ፡ ኹሉ ይድኑበት ዘንድ፡ በምሕረት ተደምድሞ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ የተሰጠው፡ የመጨረሻ መለኮታዊ ጸጋ ነው፡፡

በእናንተ እና በእኛ ላይ፡ ዲያብሎስ፡ እንኳንስ፡ ሥልጣን ሊኖረው ይቅርና፡ ከእናንተ እና ከእኛ፡ ሲሸሽ፡ ሊደርስበት ከሚችለው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥቃት ሊያመልጥ እንደማይችል፡ እንዲህ የሚለው፡ የድል አድራጊው፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የአገልጋዮቹ ቃል ያረጋግጥልናል፡-

“ወተመይጡ፡ እልክቱ ሰብእ፡ እለ ተፈነዉ፡ እንዘ ይትፌሥሑ፤ ወይብሉ፡ 'እግዚኦ! አጋንንትሂ፡ ገረሩ ለነ፡ በስምከ፡፡' ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡ 'ርኢክዎ ለሰይጣን፡ ከመ መብረቅ፡ ወድቀ እምሰማይ፡፡ ወናሁ ወሀብኩክሙ ሥልጣነ፡ ትኪዱ ዲበ አቃርብት፥ ወዲበ አራዊተ ምድር፥ ወዲበ ኵሉ ኃይለ ጸላኢ፤ ወአልቦ ዘይነክየክሙ፡፡ ወባሕቱ፡ በዝሰ ኢትትፌሥሁ፥ እስመ አጋንንት፡ ይገንዩ ለክሙ፡፡ ተፈሥሑሰ፡ ባሕቱ፡ እስመ ተጽሕፈ አስማቲክሙ በሰማያት፡፡'”

ማለትም፡ “እኒህ፡ ጌታችን ኢየሱስ የላካቸው ደቀ መዛሙርቱ፡ ደስ ብሏቸው ተመልሰው፡ 'ጌታ ሆይ! አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዙልን እኮ!' አሉት፡፡ እርሱም፡ እንዲህ አላቸው፡- 'ሰይጣን፡ እንደመብረቅ፡ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ፡፡ እነሆ፡ እባቡንና ጊንጡን፥ የጠላትንም ኃይል ኹሉ ትረግጡ ዘንድ፡ በኹሉም ላይ፡ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ፡፡ የሚጎዳችሁም፡ ምንም የለም፡፡ ርኩሳን መናፍስት፡ ስለተገዙላችሁ፡ በዚህ ብቻ፡ ደስ አይበላችሁ! ነገር ግን፡ ስማችሁ፡ በሰማያት ስለተጻፈ፡ በዚህ እጅግ ደስ ይበላችሁ!'” (ሉቃ. ፲፥ ፲፯-፳፡፡)

ከዚህ መለኮታዊ የምሥራች ቃል የተነሣ፡ እናንተ እና እኛ፡ እጅግ ደስ እያለን፡ ዛሬ፡ በዘወትሩ፡ የኪዳን ጸሎታችን፡ “ንሤልስ ለከ፡ ዘንተ ቅዱሰ ስብሓተ፤ ዘወሀብከነ ዚኣከ ሃይማኖተ፡ ዘኢይትነሣት፤ ወቦቱ፡ ገበርከ ለነ፤ ንግዕ ማእሠሪሁ ለሞት፤ ዘፈጠርከ ኅሊናተ ርቱዓተ፡ <u>ለእለ የአምኑ ብከ፡</u> ከመ እምሰብእ ይኩኑ አማልክተ፡፡ ዘወሀብከነ በመንፈስ፡ ንኪድ ኵሎ ኃይሎ ለጸላኢ፡ ከመ ንፍታሕ፡ ዘኢይትፈታሕ፡፡”

ማለትም፡ “አንተን ያወቅንበትንና በአንተ የታመንንበትን፡ ይህን፡ የማይለወጥ ሃይማኖት፡ ስለሰጠኸን፡ እኛም፡ ይህን፡ ልዩ ምስጋና፡ ለሦስተኛ ጊዜ እናቀርብልሃለን፡፡ በዚህ ሃይማኖታችን፡ የሞት ማሠሪያ የኾነውን ክህደትን፡ ድል እንድንነሣው አደረግህልን፡፡ በመልክህ ለፈጠርከው፡ ለሰው፡ የመንፈስ ቅዱስን እውነት ለመምረጥ የሚያስችለውን፡ ቅን ኅሊና በመስጠትህ፡ <u>የሚያምኑብህ ኹሉ፡</u> ከሰው ወገን፡ “አማልክት” ይባሉ ዘንድ፡ ታላቁን ማዕርግ አቀዳጀሃቸው፡፡ የጠላትንም የዲያብሎስን ኃይል ኹሉ፡ በቅዱስ መንፈስህ ረግጠን፡ እናሸንፈው ዘንድ፤ የማይፈታውንም፡ እንፈታ ዘንድ፡ ሥልጣንህን ሰጠኸን፡፡” እያልን፡ እነሆ፡ ያለማቋረጥ ስናመሰግነው እንኖራለን፡፡

ለነገሩማ፡ በማናቸውም ጊዜያት፥ በተለይም፡ የየዕለቷን ህልውናችንን በምንጀምርበት፡ በንጋቱ፥ በማለዳው፥ ወይም፡ በጧቱ የምስጋና ጸሎታችን መግቢያ ላይ፡ “አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል፡፡ በስመ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፥ እንዘ አአምን፥ ወእትመሐጸን፤ <u>እክሕደከ ሰይጣን፡</u> በቅድመ ዛቲ፡ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ ስምዕየ፡ ማርያም ጽዮን፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡”

ማለትም፡ “ፊቴንና ኹለንተናዬን፡ በመስቀል ምልክት፡ እነሆ አማትባለሁ!” ብለን ካማተብን በኋላ፡ እንዲህ እያልን፡ እንቀጥላለን፡-

"ልዩ በኾነች ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡ በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም አምኜና ተማጽኜ፡ እናቴና መጠጊያዬ፥ ምስክሬና ቤተ ክርስቲያኔ በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት፡ <u>አንተን ሰይጣንን ክጄሃለሁ፡፡</u> ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡" ማለታችን፡ የእግዚአብሔር ወገኖች፥ የዲያብሎስም ተቃዋሚዎች መኾናችንን፡ በይፋ መስክረን፡ በአዋጅ ማሳወቃችን አይደለምን? አዎን! ነው፡፡

## አምስተኛ፡- <u>"ኢትዮጵያዊነት"፡ ከእስራኤላዊነት የሚቀድም ስለመኾኑ፡፡</u>

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እውቀታቸውንና ትምህርታቸውን፡ በእግዚአብሔር እውቀትና ትምህርት ላይ በመመሥረት፡ የኹሉ ፈጣሪና ገዥ፥ ባለቤትም የኾነው እግዚአብሔር፡ ጥንት፡ በአዳምና በሔዋን ወጥኗት፥ "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት ታማኞቹ አገልጋዮቹ፡ ባለአደራነትና ድልድልይነትም አሳድጓት፥ በፍጻሜ ዘመን፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸማት፡ የቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያ፡ በእግዚአብሔር አገርነቷ፥ ሕዝብነቷና መንግሥትነቷ ታውቃ፡ ባልተቋረጠ የነጻነት ህልውና፡ ለሰባት ሺህ አምስት መቶ አንድ ዓመታት ኖራለች፡፡

ይኼ ማንነቷ፡ በእርግጥ፡ በመላው ዓለም ካሉ አገሮች፥ መንግሥታትና ሕዝቦች መካከል፡ የተለየች ብርቅ፥ ቀዳሚትና ጥንታዊት ያደርጋታል፡፡ ይህን ገሃድና ግዙፍ የኾነ እውነታ፡ ለመካድና ለማስካድ፥ ለማስተባበልም ፈጽሞ አይቻልም፡፡

እንግዴህ፡ እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሳለ፥ እንዲህ መኾኑ እየታወቀም፡ ታዲያ! ሰዎች፥ ያውም፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የሚሉ ወገኖች፡ ይህን እውነታ፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ እያስተሓቀሩ፡ ለምንድር ነው፡ እስራኤላዊነትን፡ በኢትዮጵያዊነት ላይ አሠልጥነው ለማስፈን የሚሞክሩት? የሚፍጨረጨሩትም?

ይህንም ሲያደርጉ እኮ፡ የሚያስገርመው፡-

- እኛው ኢትዮጵያውያን፡ ለእስራኤላውያን ሰጥተናቸው፡ እነርሱ ግን፡ ያን፡ ጠብቀውና አጽንተው መኖር አቅቷቸው፡ እግዚአብሔር፡ በጥበቡ፡ ወደእኛው ተመልሶ እንዲመጣ ያደረገውን፡ የሃይማኖትና የሥርዓት ቅርስ እያስታከኩ መኾኑ ነው፡፡

- ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ፡ እስራኤላዊነት እንደሚቀድም፥ ወይም፡ የላቀ እንደኾነ በማስመሰል መኾኑ ነው፤

- የእነመልከጼዴቅ ኢትዮጵያዊነት፡ በገዛ አገሩ ተገፍቶ፡ በእንግዳው፡ በእነአብርሃም እስራኤላዊነት እንዲዋጥ በማድረግ መኾኑ ነው፡፡

ይኸው ሙከራቸውና መፍጨርጨራቸው፡ እጅግ የሚያስተዛዝብና የሚያስወቅስ፥ የሚያስነቅፍና የሚያስጠይቅ ከመኾኑ በቀር ሌላ ትርፍ የለውም፡፡ እግዚአብሔር የሠራውን ዘለዓለማዊ የእውነት ሕንፃ፡ የሰው ሙከራና መፍጨርጨር፡ ሊያፈርሰው ቀርቶ፡ ሊለውጠውና ሊያሻሽለው እንኳ አይቻለውምና፡፡

ለዚህ ሙከራቸውና መፍጨርጨራቸው፡ አያሌ ማስረጃዎች ሊቀርቡ ይቻላል፤ ይኹን እንጂ፡ ከሚዘወተሩት መካከል፡ አንዱን፡ ዋናውን፡ ለዓይነት ያህል፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ ይበቃል፡፡ ይኸውም፡-

- ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፡ በእግዚአብሔር አገርነት፥ ሕዝብነትና መንግሥትነት፡ የሰባት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት የነጻነት ህልውና ባለቤቶች የመኾናቸው መለኮታዊ እውነታ፡ ኾነ ተብሎ፥ በተንኰል፡ ወደጎን ገሸሽ እንዲል መደረጉ፥

- በዚያ ምትክ፡ ይኸው፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ፥ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ህልውና፡ በሦስት ሺህ ዓመታት ዘመን ብቻ ተወስኖ፡ "የሦስት ሺህ ዓመታት የነጻነት ታሪክ ባለቤት ናቸው!" እየተባለ የሚለፈፈው፡ የይፋ ሓሰት፥ ውሸት ነው፡፡

በእነርሱ ዘንድ፡ ከላይ ተብራርቶ የተጠቀሰው፡ ይህ፡ የዛሬው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ማንነት፡ የተመሠረተውና የተጀመረው፥ የታወቀውና የኖረው፡ ከኢትዮጵያዊቷ፡ ንግሥት ማክዳና ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን የተወለደው፡ ቀዳማዊ ምኒልክ፡ ለዚያ ዘመን መነሻ ሓውልት እንደኾነ ተደርጎ ተደንግጓል፡፡

ይህ ሰው ሠራሽ ድንጋጌ የተመሠረተው፡ እስራኤላውያን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ተዋዋይነትና ባለአደራነት ካለመብቃታቸውና ካለመታመናቸው የተነሣ፡ ለእነርሱ፡ ከፈጣሪ የተለገሣቸው በረከት ኹሉ፥ ቃል ኪዳኖቹና ምልክቶቹ ጭምር፡ ወደኢትዮጵያና ወደኢትዮጵያውያን በገቡበት ዘመን እንደኾነ ተቆጥሮ ነው።

ራሳቸውን፡ "ዕብራውያን" እና "አይሁድ" እያሉ የሚጠሩት፡ እስራኤላውያን፡ የህልውናቸው ታሪክ የሚጀምረው፡ ቀድሞ አረማዊና ጣዖት አምላኪ በነበረው፡ በአብራም መኾኑ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ጭምር፡ ተረጋግጦ ታውቋል፤ ተመስክሩዋልም። እርሱም፡ "'የእግዚአብሔር ልጆች' ወገንና የእግዚአብሔር ካህን፥ የኢየሩሳሌም ቈርቋሪና እግዚአብሔር የቀባው፡ የሰላም ንጉሥ" ከተባለው፡ ከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና ስለሥርዓተ አምልኮቱ ተምሮ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ በሃይማኖትና በምግባር ሲቀበል፡ ለግርዛቱ ቃል ኪዳን በመብቃቱ፡ "አብርሃም" ተብሎ የተሰየመው ነው። በመካከለኛው ዘመን፡ ኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር፡ ለሙሴ፥ በመጨረሻውም ዘመን፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ለጠፉት የእስራኤል ቤት" እንዳደረጉት ኹሉ ማለት ነው።

እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ እነዚያ ሰዎች፡ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን የነጻነት ህልውና መዋዕል፡ መነሻውን፡ ከአብርሃም ዘመን ወዲህ እንደኾነ በማስመሰል፡ በአያሌ ምዕታት ዓመታት ወደኋላ አምጥተው፡ መወሰናቸው፡ በእርግጥ፡ ያስገርማል! በዚህ ረገድ፡ በእጅጉ የሚያስገርመው፡ የሌሎቹ፡ የባዕዳኑና ከእነርሱ ጋር ለጥቅሙ ሲል የተባበረው፡ የኢትዮጵያው ቤተ ምልክና ድርጊት ሳይኾን፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" የሚሉት፡ የእኛዎቹ የቤተ ክህነት ምሁራንና ዓይኖቹን ጨፍኖ፡ እነርሱን ሲከተል የኖረው፥ ዛሬም እየተከተለ ያለው የቤተ ሕዝቡ ትውልድ ኾኖ ይገኛል።

እስራኤላውያን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ተዋዋይነትና ባለአደራነት ላለመብቃታቸውና ላለመታመናቸው፡ ማረጋገጫ ኾኖ የሚቀርበውም ምስክር፡ እግዚአብሔር፡ አብርሃምንና ሣራን፥ ይስሐቅንና ርብቃን፥ ያዕቆብንና ራሔልን፥ ሙሴንና ሲጳራን፥ ዳዊትንና ቤትሳባን፥ ሰሎሞንንና ማክዳን ከመሰሉት አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ጋር የተጋባውን ቃል ኪዳን፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአምልኮ አመንዝራነት ማርከሳቸው መኾኑ፡ በገሃድ ይታወቃል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ በመጨረሻ፡ በቃል ኪዳን ያጸናውን፡ ተስፋውንና ትንቢቱን ኹሉ ሊፈጽም፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ወደዚህ ዓለም በሰውነት መጥቶ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ፡ ከልጅነቱ ጀምሮ፡ ሊያገለግላቸውና ሊያስተምራቸው፥ ሊያጸናቸውና ሊያድናቸው፡ በመካከላቸው ቢገኝ፡ አሠቃይተውና ሰቅለው በመግደላቸው፡ ያ የኃጢአታቸው እርግጠኛነትና የርኵሰታቸው ምስክርነት፡ በማያወላውል መልክና ይዘት፡ በዘለዓለማዊው ማኅተም ሊጸናባቸው ችሏል።

እናንተ እና እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ቀድሞ፡ በዘመነ ኪዳነ ልቦና፥ ኋላም፡ በዚህ፡ በዘመነ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ የኖርንበትና እየኖርንበት ያለነው ሃይማኖታችንና ምግባራችን፥ የአምልኮና የህልውና ሥርዓታችን፥ ባህላችንም ኹሉ፡ ያው፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ ከእግዚአብሔር አግኝተን፡ በአዳምና ሔዋን፥ ከዚያም፡ በኖኅና እርሱን በመሰሉት ባለቃል ኪዳኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን አማካይነት የተቀበልነውና የምንከተለው ብቻ ነው። እርሱንም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ የእግዚአብሔር ልጁና ቃሉ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ አስተምሮን፡ አጽንተነዋል።

ይኹን እንጂ፡ በዚህ ረገድ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው፡ በዛሬው ትውልድ ዘንድ፡ ሠልጥኖና ሰፍኖ፥ ጸንቶና ተንሠራፍቶ፡ እየተሠራበት የሚታየው ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና የህልውና ሥርዓት፥ ባህልም፡ እንዳለፉት "ባለሦስት ሺህ ዓመታት ባለታሪክ" ትውልዶች ኹሉ፥ አኹንም ገና፡ ያው፡ <u>ከኦሪታዊነት</u> ቀንበር ያልተላቀቀ በመኾኑ፡ ያ፡ የእስራኤላዊነት ተፅዕኖ፡ በእኒሁ፡ በዛሬዎቹ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" በሚሉት ላይ፡ የቱን ያህል ሥር የሰደደና የተጠናከር መኾኑ፡ በግልጽ ይታያል።

እዚህ ላይ ሊወሳ የሚገባ፡ አንድ ቁም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ ጥንቱኑ፡ “የእግዚአብሔር ልጆች” ተብለው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ታማኝነታቸውና በምግባር ቅንነታቸው፡ እግዚአብሔርን ሲያስደስቱት የኖሩት፡ ኢትዮጵያውያን ሲኾኑ÷ በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ከአረማዊነት ሓረጋቸው የተነሣ፡ “የሰው ልጆች” ተብለው፡ በክህደታቸውና በዓመፀኝነታቸው÷ በአምልኮ ምንዝርናቸውም፡ እግዚአብሔርን ሲያሳዝኑት የኖሩት፡ እስራኤላውያን መኾናቸው ነው።

እግዚአብሔር፡ በማያልቅ ቸርነቱና መሓሪነቱ፡ በእርሱ ፊት፡ እውነተኞች ኾነው ከተገኙት÷ ራሱ፡ የእስራኤላውያን አባት ከኾነው፡ ከአብርሃም÷ የእርሱ ዘሮች ከኾኑትም፡ ከሙሴና ከዳዊት ጋር የተጋባቸውን ቃል ኪዳናት፡ በበኩሉ በመጠበቅ፡ የእኒሁ፡ የታማኞቹ ባለቃል ኪዳኖቹ ቅሬቶች፡ ከሥጋዊው ዘራቸውና ከተመረጡት ልጆቻቸው ጋር፡ በሙሉ ወደኢትዮጵያ መጥተው÷ ከኢትዮጵያዊነትም ጋር ተዋሕደው፡ ህልውናቸውን እንዲቀጥሉ ማድረጉ፡ የማይታበልና በግዙፉን ማስረጃዎች የተረጋገጠ እውነታ ነው።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ከእነዚህ፡ ከእውነተኞቹ እስራኤላውያን ውጪ አፈንግጠው÷ በክህደታቸውና በዓመፃቸው÷ በአምልኮ ምንዝርነታቸውም፡ እስካኹን ጸንተው የቀጠሉ÷ በአኹኑ ዘመን፡ ራሳቸውን፡ “እስራኤል” ብለው ሰይመው÷ በዓለሙም ኅብረተሰብ ዘንድ እውቅናን አትርፈው የሚገኙ መኖራቸው፡ በይፋ ይታወቃል። እነዚህም፡ እውነተኛውን መሲሕ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ አምነው ሊቀበሉት ቀርቶ፡ ሰቅለው በመግደላቸው፡ የኋላ ኋላ እንኳ፡ “በንስሓም አንመለስም!” ብለው፡ ራሳቸውን፡ ለፍርድ ቀን አዘጋጅተው ከኖሩት፡ ከቀድሞዎቹ “አይሁድ” ተያይዘው የወረዱት ናቸው።

በዚያን ጊዜም፡ ያ ሰቅለው የገደሉትና ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ጌታ፡ እንዲህ ሲል የተናገረው ቃል ይፈጸምባቸዋል፡- “ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፤ ወትትፋትሓ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወታስተኃፍራ። እስመ መጽአት፡ እምአጽናፈ ምድር÷ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን። ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ህሎ ዝየ።”

ማለትም፡ “ንግሥተ አዜብ [ኢትዮጵያ] በፍርድ ቀን ተነሥታ፡ ይህን ትውልድ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና። እነሆ፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።” (ማቴ. ፲፪÷ ፵፪።)

እናንተ እና እኛም፡ ዛሬ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት እያስታወስን፡ በዘወትር የአምልኮ ጸሎታችን ጊዜያት፡ ከስግደት ጋር፡ “አይሁድ ክህዱ! ንሕነሰ አመንነ፤ ወእለ አምንነ፡ በኃይለ መስቀሉ ድኅንነ!” ማለትም፡ “አይሁድ ካዱት! እኛ ግን አመንንበት። ያመንንበት እኛም፡ በመስቀሉ ኃይል ዳንን!” የሚለውን ቃል የምናስሰማው በዚሁ ምክንያት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

እነዚህ፡ ራሳቸውን፡ “እስራኤል”÷ ወይም፡ “ቤተ እስራኤል” ብለው የሚጠሩት፡ ሰብአውያን ፍጡራን፡ ይህን ኹሉ፡ ክፉ ተግባራቸውን፡ በፈጣሪያቸውና “ኢትዮጵያ” በተባለችው፡ በቅድስት እናቱ ላይ÷ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያዊነትም ላይ በሚፈጽሙበት ጊዜያት፡ በዘመነ ብሉይ፡ “'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።”

ማለትም፡ “'እናንት የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም!' ይላል፡ ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ እግዚአብሔር' የኾነ።'” የሚለውን መለኮታዊ ቃል፡ የሚያስታውሱት አይመስልም። (አሞ. ፱÷ ፯።)

በዘመነ ሓዲስ ደግሞ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቻይ መሓሪ የኾነውን፡ አባትዬውን፡ ለቸር እግዚአብሔር፡ ምሳሌ÷ የታመነውን፡ ታላቁን ልጁን፡ “የእግዚእብሔር ልጆች” ለኾኑት፡ “ለኢትዮጵያ ልጆች“ ምሳሌ÷ አጥፊውን፡ ታናሹን ልጁን ደግሞ፡ “የሰው ልጆች” ለተባሉት፡ “ለእስራኤል ልጆች” ምሳሌ አድርጎ የሰጠው መለኮታዊ ትምህርቱ፡ እዚህ ላይ፡ ሊጠቀስ ይገባዋል።

ይኸውም፡ ትንሹ ልጁ፡ “የውርስ ድርሻዬን፡ አኹኑኑ ስጠኝ!” ብሎ፡ በድፍረትና በጥጋብ፡ ከአባቱ የወሰደውን ገንዘብ፡ በሙሉ አባክኖ ሲመለስ፡ አባትዬው፡ በደስታ ተቀብሎ፡ የበዓል ድግሥ ስላደረገለት፡ ትልቁ ልጁ አዝኖ፡ አባቱን በወቀሰው ጊዜ፡ ያገኘው መልስ፡ እንዲህ የሚል ነበር፡-

"ወይቤሎ አቡሁ፤ 'ወልድየ! አንተሰ ዘልፈ ሀለውከ ምስሌየ፤ ወኵሉ ዘዚአየ፡ ዚአከ ውእቱ። ወባሕቱ፡ ርቱዕሰ ንትፈሣሕ፤ እስመ ዝንቱ እኁከ፡ ሞተሂ፥ ወሐይወ፤ ተሐጉለሂ፥ ወተረክበ።"

ማለትም፡ "አባቱም፡ እንዲህ ሲል፡ መለሰለት፤ 'ልጄ ሆይ! አንተ፡ ኹልጊዜ፡ ከእኔ ጋር ነህ። ለእኔ የኾነው ኹሉ፡ የአንተ ነው። ጳሩ ግን፡ ይህ ወንድምህ፡ ሞቶ ነበር፤ ሕያው ስለኾነ፥ ጠፍቶም ነበር፤ ስለተገኘ፡ ደስ እንዲለን፥ ሓሴትም እንድናደርግ ይገባናል።" ያለው አምላካዊ ቃል፡ እስከዛሬ፥ ዛሬም፡ የማይሻርና የማይታበል፡ እውነትና ገሃድ ኾኖ፡ እነሆ፡ ስለኢትዮጵያውያንና ስለእስራኤላውያን የሃይማኖት ታማኝነትና ስለምግባር ጣፋጭ ፍሬ፡ ሲመሰክር ይታያል። (ሉቃ. ፲፭፥ ፴፩-፴፪።)

ስድስተኛ፦ <u>"ኢትዮጵያዊነት"፡ ከግብፅ ኦርቶዶክሳዊነት የሚበልጥ ስለመኾኑ፤</u>

እግዚአብሔር፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የፈጸመው ሕያው ሥራው፡ በእስራኤላውያንና በተለይም፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" በሚሉ ወገኖች፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ በደል ሲካኼድበት የኖረው፡ እስራኤላዊነትን በሚመለከተው ጎኑ ብቻ አይደለም፤ ከዚያ ተከታትሎ፡ ክርስትናን ተገን በማድረግ፡ ወደኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የመጣ፡ ሌላም ባዕድ ጠንቅ አለ። ይኸውም፡ ራሳቸው፡ የክርስትና ምሥራች ተሰብኮላቸው፡ ከጣዖት አምልኮ፡ በቀጥታ፡ ወደ ሃይማኖተ እግዚአብሔር የተመለሱት፡ "በወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ ነው!" ተብሎ በሚነገርላቸው ግብፃውያን የተካኼደው ነው። የዚያ ጠንቅ መንስዔም፡ ባጭሩ፡ እንዲህ ነበር፦

ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት፡ በዚያን፡ በቀደመው፡ የክርስትና ዘመን፡ የጊዜውን አዲስ ሥርዓት አውቀውና ቀስመው እንዲመጡ በማለት፡ ራሳቸው ኢትዮጵያውያን፡ ወደኢየሩሳሌም የሰደዷቸው፡ የተመረጡ ልኡካኖቻቸው፡ እግረ መንገዳቸውን፡ በግብፅ አገር ሲያልፉ፡ እኒሁ ግብፃውያን፡ ኢትዮጵያውያኑን ልኡካን ከጉዟቸው አስቀርተው፡ ወደኢትዮጵያ እንዲመለሱ በማድረግ፡ ልክ፡ ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት ቀደም ብሎ፡ እስራኤላውያን፡ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያካኼዱትን የመሰለ፡ የዘመቻ ወረራቸውን ፈጸሙ።

ይኸውም፡ "Orthodox" ("ኦርቶዶክስ") የተሰኘ፡ "የግብፅ ሃይማኖትንና ምግባርን፥ አምልኮንና የህልውና ሥርዓትን፥ ደግሞም፡ ከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ሲያያዝ የመጣውን፡ ጥንታዊዉንና ቀዳሚውን፡ ኢትዮጵያዊዉን የሊቀ ካህናትነት መንበርና ሹመት ደምስሶ የሚተካ፡ "ጵጵስና" የተባለ፡ እንግዳና ባዕድ ሹመት ወደኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በማስገባት ያካኼዱት፡ ያልተቋረጠው የወረራ ዘመቻቸው ነው።

እርሱንም፡ ማለትም፡ "ጵጵስናውንም" ቢኾን፡ ለራሳቸው ብቻ እንጂ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ለዚያ ሹመት ተገቢነት ስለሌላቸው፡ በምንም መንገድ በእጩነት እንዳይቀርቡ፥ እንዳይመረጡና እንዳይሾሙ፥ እንዲያውም፡ ግብፃዊዉን ጳጳስም እንኳ ቢኾን፡ እጩ አድርገው እንዳያቀርቡ፥ እንዳይመርጡም፡ በማያወላውል አገላለጽ በተጻፉ አንቀጾች፡ ግብፃውያኑ፡ ለኢትዮጵያ አዔዎች በሰጡት፡ እንደእግዚአብሔር ቃል በሚከበረውና በሚጠበቀው "ፍትሐ ነገሥት" በሚሉት መጽሓፋቸው ደንግገውታል። ይህም የኾነው፡ ግብፃውያኑ ጳጳሳት፡ "የሰሎሞን ዘር ነን" የሚሉትን ብቻ ሊቀብሉ፥ እነዚህም፡ በእነዚያ፡ በግብፃውያኑ ብቻ ሊቀቀቡ፡ እንዲህ ባለ፡ የጋራ መጠቃቀሚያ በኾነ፡ የምሥጢር ስምምነት፡ ኹለቱም ወገኖች፡ ቃል ኪዳን ስለተጋቡ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ መቼም፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በኪዳነ ልቦና፥ በኪዳነ ኦሪትና በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ጸንቶና ተከናውኖ የቆመው፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና የህልውና ሥርዓት፡ ግብፃውያኑ፡ ክርስትናን ከመቀበላቸው፡ ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት አንሥቶ፡ ተጠብቆ መኖሩ በይፋ ይታወቃል።

ይህ እውነታ፡ እንዲህ እየታወቀና በቅዱሳት መጻሕፍት እየተመሰከረ፡ እኒሁ ግብፃውያን፡ ያለይሉኝታና ያለኃፍረት፥ በማናለብኝነትና በድፍረት፡ በኢትዮጵያዊነት እውነትና ትውፊት ላይ፡ ኾን ብለው፡ በሓሰት ጽሕፈት፥ በስሕተት ትረካና በተዛባ ዘገባ፡ ሲያካኺዱ የኖሩት፥ ዛሬም እያካኼዱ ያሉት የወረራ ዘመቻ፡ በበርካታ መልኩ፡ እነሆ፡ ገሃድ ኾኖ ይታያል።

እኒሁ፡ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን "ጳጳሳት" እና ወገኖቻቸው፡ ካገር ውስጥ ተባባሪዎቻቸው ጋር በመመሣጠር፡ ኢትዮጵያዊነትን አስወግደው፡ በእርሱ ቦታ፡ ግብፃዊነትን ለመተካት በዶለቱት፡ በዚህ የወረራ ዘመቻቸው ውስጥ ከተካተቱት፡ ከብዙዎቹ ፀረ ኢትዮጵያ ድርጊቶቻቸው መካከል፡ እስኪ፥ እዚህ ላይ፡ ለዓይነት ያህል፡ አንዳንዶቹን ብቻ እንጥቀሳቸው፤ ከእነዚህ መካከል፦

አንደኛው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስንና የቅድስት እናቱን ድንግል ማርያምን፡ የልደታት ቀን፡ በትክክል ከሚውልበትና በመለኮት ዕፁብ ድንቅ፡ የሥነ ፍጥረት ሥራዎች ካሸበረቀው፥ በአምልኮተ እግዚአብሔር በዓላትም ከሠመረው፡ ከኢትዮጵያውያኑ መስከረም ፩ (አንድ) ቀን ገንጥለው ወስደው፡ በጣዖት አምልኮና በሰው ልጆች ሥርዓት ወደተወሳሰበው፡ ወደፈረንጆቹ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን እንዲቀየር ያደረጉበት፡ ሰይጣናዊ ግብራቸው ነው።

ኹለተኛው፡ "ኢትዮጵያውያንን፡ ክርስቲያን ያደረግናቸው፥ ቤተ ክርስቲያናቸውንም መሥርተን ያቋቋምንላቸው፡ ወደኢትዮጵያ በገባንበት፡ በአራተኛው ምዕት ዓመተ ምሕረት፡ እኛ ነን!" የሚለው ድርሳናቸው ነው።

ሦስተኛው፡ "በኢየሩሳሌም ያለው፡ የኢትዮጵያውያን ዐጽመ ርስት፡ ለኢትዮጵያውያን ምናቸው ነው? ርስቱም፥ ንብረቱም የእኛ ነው፤ እንኳንስ፡ ርስታቸውና ንብረታቸው፡ እነርሱ ራሳቸው፡ የማን ናቸው? የእኛ፡ የግብፃውያን አይደሉምን?" በማለት፡ እኒሁ፡ ግብፃውያን፡ በቤተ ክርስቲያናቸው መሪ አንደበት፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን፥ በኢትዮጵያዊነትም ላይ ያላቸውን፡ የተፃራሪነት አቋም ግልጽ አድርገዋል።

"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፡ ይህ የዘመኑ ትውልድ ጭምር፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ ይህንኑ የግብፃውያኑን ድርጊትና ሥርዓት ተቀብሎ፥ አጽንቶና እውቅናም ሰጥቶ፥ በሕግና በአዋጅም አጽድቆ፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ የኖረበትን፡ ይህንኑ የተዛባ አቋም "ላስተካክል!" ሳይል፡ ይኸው፡ አኹንም በዚሁ አቋሙ ቀጥሎበት ይገኛል። እንዲያውም፡ የዛሬዎቹ የቤተ ክህነቱ መሪዎች ከኾኑት ሊቃነ ካህናት፥ ካህናትና ምእመናን ጋር በመተባበር፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በፈጸመው፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ታላቅ ኃጢኣት ምክንያት፡ የተያዘበትን መለኮታዊው ውግዘት፡ በንስሓ በማስነሣት ፈንታ፡ የበለጠ እንዲጠብቅ አድርጎታል።

ከዚህ የተነሣ፡ ይህች፡ "በግብፃውያኑ ተቋቋመች!" የተባለችው፡ ቤተ ክርስቲያን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የቤተ ክህነቱ አካል ከኾነችው፡ ከእውነተኛዪቱ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተለየች ኾና፥ በእናንተ እና በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ መታወቂያዋና መጠሪያዋ፡ "የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" ሳይኾን፡ "በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን" መኾኑን፡ ቀደም አድርገን፡ በይፋ አሳውቀናል። ይህም፡ የ"ግሪክ ኦርቶዶክስ"ን፥ የ"ካቶሊክ"ንና የ"ወንጌላውያን"ን እንደመሰሉት፡ እንደሌሎቹ፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ "ተቋቊመን እንገኛለን!" እንደሚሉት፡ ባዕዳን አብያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት ድርጅቶች ኹሉ ማለት ነው።

የግብፅ "ኦርቶዶክሳውያን"፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን፥ በኢትዮጵያዊነትም ላይ የፈጸሙትን፡ የቀረውን፡ የጥቃት ጉድ ዝርዝር፡ በጎዋ ሰሌዳችን ላይ ከወጡት መጽሓፎቻችን፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፍ ውስጥ የተካተተውን ሓተታ፡ መመልከት ይቻላል።

እዚህ ላይ፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ሳይጠቀስ የማይታለፈው፡ እጅግ አሳዛኝ የኾነው ድርጊት፡ ይህን ኹሉ፡ የግብፃውያንን ሐሳዊና ጎጂ ዓላማና ተግባር፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" የሚሉት ወገኖች፡ ለሺህና ለአያሌ ምዕት ዓመታት፥ ዛሬም፡ በዝምታ ተቀብለውና ቀንበሩን ተሸክመው፡ እስከዛሬ መኖራቸውና ወደፊትም እንዲቀጥል ማድረጋቸው ነው።

ሰባተኛ፦ <u>ማሳወቅና ማስፈን የሚገባን፡ "ኢትዮጵያዊነትን" ስለመኾኑ።</u>

እንግዲህ፡ እንዲህ ያለውን ጠንቀኛ የሐሰት ቅርስ ነው፡ ያለፉት የኢትዮጵያ ትውልዶች፡ እውነት መስሏቸውና እንደሙያ ቈጥረውት፡ እስራኤላዊነትንና ግብፃዊነትን በማጋነንና በማነጋገሥ፥ ኢትዮጵያዊነትን ግን፡ በማንኳሰስና በማዋረድ፡ የወረራ ዘመቻቸውን፡ ያለንፍረትና ያለይሉኝታ፡ በማንአለብኝነት ሲያካኼዱ የኖሩት፥ የዛሬውም የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ፡ እየቀጠለበት ያለው።

ይኹን እንጂ፡ በአንድ በኩል፡ ከላይ የተጠቀሱት ባዕዳኑ፡ በተንኰል፥ በሌላውም በኩል፡ "ወገኖች ነን!" ባዮች፡ እንደዛሬዎቹ ኹሉ፡ ከባዕዳኑ ጋር በመመሣጠርና በግብረ አበርነት፡ ይህን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን "ኢትዮጵያዊነት" ደምስሰው ለማጥፋት፥ በእርሱም ቦታ፡ የየራሳቸውን ማንነት፡ ማለትም፡ "እስራኤላዊነትን" ኾነ፡ "ቅብጥነትን" (ግብፃዊነትን) ለመተካት የሚያደርጉት፡ የተቀነባበረውና ያረጀው ዘመቻቸው፡ በምንም መንገድ ሊሠምር ከቶ አይችልም።

ምክንያቱም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅርና ታማኝነት የተነሣ፥ እርሱ ደግሞ፡ ለወደዱትና ለታመኑበት፡ ለእነርሱ፡ ከሌሎቹ ፍጡሮቹ ኹሉ ይልቅ፡ ቅዱሱን ኪዳኑን አክብረው መጠበቃቸውን እየተመለከተ፡ የሚያደርግላቸውን የቸርነት ሥራውን ስለማያቋርጥባቸው ነው። ለኹሉ፡ እንደየሥራው በሚከፍለው በእርሱ፡ የእርሱ፡ የእግዚአብሔሩ ሥራ የኾነው ኢትዮጵያዊነት ጸንቶ፡ የእነርሱ፡ የተቃዋሚዎች ሙከራና ጥረት ፈራርሶ፡ የእነርሱም መጨረሻቸው፡ እንደሌሎቹ፡ አጥፊዎች ይኾናል።

እዚህ ላይ፡ አኹንም ሳይወሳ የማይታለፍ፡ አስተዋይ ተመልካችን የሚያስገርም፥ ምናልባትም፡ ግራ የሚያጋባ፡ አንድ እንቆቅልሽ አለ። ይህም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" የሚሉ ወጣቶችና ጎልማሶች፥ አረጋውያን ጭምር፥ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ በሃይማኖታቸውና በአገራቸው፥ በወገናቸውና በራሳቸው ላይ የሚፈጽሙትን አሳዛኝ ድርጊት ይመለከታል። ይኸውም፡ በአንድ በኩል፡ ባዕድና ጎጂ ለኾነው፥ "እግዚአብሔር የለም!" እስካሰኘው፡ እስከሌላው የእምነት ዓይነት ድረስ፡ ለዚያ፡ ለአዲሱ ባዕድ እምነታቸው፡ ያላቸው ቀናተኝነት፡ እስከአክራሪነት ደርሶ፡ እርሱን ለማሳወቅና ለማሳመን፥ ለማስፋፋትና ለማጠናከር፥ ወገኖቻቸውን ሳይቀር፡ ካሉበት ጥንታዊ እምነታቸው አስክደው፡ ወደዚያ፡ ወደእንግዳው እምነት ለማስገባት፡ ባለ፡ በሌለ ኃይላቸው ሲጥሩ መታየታቸው ነው። ይህም፡ ባለፉት ጊዜያት እንደታየውና አኹንም፡ እየታየ እንዳለው ኹኔታ ማለት ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ የእግዚአብሔር በመኾኑ፡ ወደር ለማይገኝለት፥ ዘለዓለማዊና ጠቃሚ፥ መልካምና የራሳቸው ለኾነው፡ ለዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ እምነታቸው፡ የዚያን፡ ለባዕዳኑ ካበረከቱት መሥዋዕትነት፡ ከአሥር አንዱን ያህል እንኳ ሊቸሩት አለመፈለጋቸው ነው።

እየራሳችንን "ኢትዮጵያዊ" የምናሰኝ፡ ወገኖች ግን፡ በግልም ኾነ በኅብረት፡ ሊያኮራንና ሊያስመካን፥ ቅድሚያም ሰጥተን፡ ልናስተምረውና ልናሳውቀው የሚገባን፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት"ን እና ከእርሱ ጋር የተያያዘውን፡ "ተዋሕዶነት"ን እንጂ፡ የአይሁድ "እስራኤላዊነት"ን፥ ወይም፡ የግብፅ "ኦርቶዶክሳዊነት"ን አይደለም። ሊኾንም አይገባም። የዚህ እውነታ፡ ምክንያቱ፡ ግልጽ ነው፦

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን "ኢትዮጵያዊነት"፥ ከዕብራውያንና ከአይሁዳውያን "እስራኤላዊነት"፥ ከግብፃውያንም፡ "ኦርቶዶክሳዊነት" በፊት፡ እጅግ በጣም ቀደም ብሎ የነበረ፥ ከኹሉም የላቀና የከበረ ነው።

"ኢትዮጵያዊነት"፡ በእግዚአብሔርም ዘንድ፡ በይበልጥ የተወደደ፥ ለቅድስት እናቱ ድንግል ማርያምም፡ መጠሪያዋና መታወቂያዋ፥ ዕፅመ ርስቷም የኾነ፥ የኋላ ኋላም፡ ኹለቱን ማንነቶች፡ ማለትም፡ የአይሁድ እስራኤላዊነትንና የግብፅ ኦርቶዶክሳዊነትን፥ ሌሎቹንም፡ ከእግዚአብሔር የኾኑትን ኹሉ፡ በአንድነት አዋሕዶ፡ በዘለዓለማዊ ህልውናው የቀጠለ በመኾኑ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ከላይ በተጠቀሰው በነቢዩ አሞጽ፡ በተነገረ የመንፈስ ቅዱስ ቃል መሠረት፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ጥንቱ፡ ከመሠረቱ፡ ከፍጥረት ልደት ጋር፡ ከእግዚአብሔር የተገኘ፥ በእግዚአብሔር የተሠራ፥ የሚመራና የሚጠበቅ፥ የእግዚአብሔር ኾኖ፡ በቅዱሱ ኪዳን ማኅተምነት፡ ለሰብአዊው ፍጡሩ መልካም ህልውናና የዘለዓለም ሕይወት፡ በመለኮታዊ ጸጋ፡ ለሰው ልጆች ኹሉ፡ ያለልዩነት፡ የተሰጠ ሀብት ነው። እናንተ እና እኛም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "ኢትዮጵያዊነት"ን፡ የተቀበልነው፡ በዚህ ኹለንተናውና በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ ኹሉም ሊያውቀው ይገባል።

በመጨረሻም፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፡ ላለፉት ሰባት ሺ አምስት መቶ አንድ ዓመታት፡ በነጻነት እንዲኖሩ ባስቻላቸው፡ በዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ይህችኑ አገርና ሕዝቧን፡ ዓለም፡ ዛሬ፡ ከደረሰበት የሥጋዊ ሥልጣኔ ደረጃ ለማብቃትና ከዚያም አልፋ፡ በምድራዊው የሀብት ልማትና ዕድገት እንድትገሠግሥ ለማድረግ የሚያዳግት መስሎ ለሚታያቸው፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" ለሚሉ ዓለማውያን ወገኖች፡ የሚሰጣቸው መልስ፡ እንደሚከተለው፡ አጭርና ግልጽ ነው፦

"በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት መታመን፡ ለሥጋዊው ሥልጣኔ እርምጃ እንቅፋት ነው!" የሚለው አስተሳሰብ፡ ችግር ኾኖ፡ እንኳንስ፡ በእግዚአብሔር የምታምነውን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ይቅርና፤ በተለያየ የባዕድ፥ የጣዖትና የአጋንንትን አምልኮ የሚከተሉትን የዓለም ሕዝቦች እንኳ፡ ያ እምነታቸውና አምልኳቸው፡ ችግር ኾኖ፡ ከሥጋዊው ሥልጣኔ ዕድገት አልከለከላቸውም።

በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማመን ደግሞ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ተጠናቅቆ፥ ተሟልቶና ተከናውኖ የተሠራውን፡ ሰብአዊዉን ፍጡር ጨምሮ፡ ፍጥረተ ዓለምን በፈጠረው፡ በአንዱ አምላክ፡ በእግዚአብሔር ማመን ነው። እግዚአብሔርም፡ የሰው ሥጋዊው፥ ነፍሳዊውና መንፈሳዊው ህልውና ተጠብቆ ያድግ ዘንድ፡ እውቀቱንና ጥበቡን፥ መሥሪያውንና ኃይሉን ፈጥሮ የሰጠው፥ ኹሉ የእርሱ፥ በእርሱና ለእርሱ የኾነው ፈጣሪ ነው።

ይህን እውነታ፡ በበለጠ ማብራራት ይቻላል፤ ይኸውም፡ ሃይማኖት፥ ወይም፡ በእግዚአብሔር ማመን፥ ወይም፡ በመንፈሳዊ እምነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት፡ ለሥጋዊ ሥልጣኔ ዕድገት፡ ዕንቅፋት፥ ወይም፡ ጋሬጣ ሊኾን እንደማይችል፡ አረጋግጦ በማስረዳት ነው። እንዲያውም፡ በተቃራኒው፡ ለማናቸውም ዓይነት የሥልጣኔ እርምጃ፡ ጽኑ መሠረትና ድልድይ ኾኖ፡ ዕድገቱን፡ እንደሚያጠናክረውና እንደሚያፋጥነው፡ በበቂ ማስረጃ ማሳመን አያዳግትም። ለዚህም፡ በዓለም ውስጥ ከሚኖሩት፡ ከአረማውያንና ከአሕዛብ፥ ከአይሁድና ከእስላሞች፥ ከክርስቲያንም ወገኖች መካከል፡ የብዙዎች አገሮችንና ሕዝቦችን ስም፡ መዘርዘር ይቻላል።

ይኹን እንጂ፡ ለዓይነት ያህል፡ ቻይናንና ጃፓንን፥ ሕንድንና ፓኪስታንን፥ እስራኤልንና ኢራንን፥ እንግሊዝንና ፈረንሳይን፥ መስኮብንና አሜሪካንን፡ በምሳሌነት መጥቀሱ ይበቃል። ሥልጣኔው የሌላቸውና በምድረ በዳ የሚኖሩት ዘላኖቹ ዓረቦች እንኳ፡ ከነዳጅ የማዕድን ሀብታቸው የተነሣ፡ በሌሎቹ የሥልጣኔ ፍሬ በልጽገው ለመኖር፡ ሃይማኖታቸው፡ ዕንቅፋት፥ ወይም፡ ጋሬጣ ኾኖ እንዳልከለከላቸው፡ እነሆ፡ በገሃድ የሚታይ እውነታ ነው።

እነዚህ ኹሉ አገሮችና ሕዝቦች፡ በሥጋዊው ሥልጣኔያቸው ሊዳብሩ የቻሉት፡ ምንም ምን ይኹን፡ በያዙት ሃይማኖታቸው ጸንተው ስለተገኙ ብቻ መኾኑን አበክሮ መገንዘብ ይገባል።

ታዲያ! ይህ ኹነታ፡ የአኵስምን ሓውልቶችና የላሊበላን ሕንፃዎች የመሰሉት፡ የነዚያ ኹሉ፡ ጥንታውያንና ብርቅ፥ ቋሚና ግዙፍ የሥልጣኔ ፍሬዎች ባለቤቶች በኾኑት፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ስለምን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በገቢር ተፈጽሞና በተጨባጭ ደርሶ አይታይም? ምክንያቱ፡ ሌላ ኹለተኛ የሌለበት፡ አንድ እና አንድ ብቻ ነው፡፡ እርሱም፡ እንዲህ በምትል፡ በአንዲት ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል፦

"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፡ ያለፉትም ኾኑ የዛሬው፡ በዚህ መልእክት ውስጥ የተገለጸውን፥ የጠራውንና የነጻውን፥ የቀናውንና የሠመረውን፥ በልዩ ልዩ የመከራ እሳት ተፈትኖ የወጣለትንና የሰባት ሽህ አምስት መቶ አንድ ዓመታት የነጻነት ዕድሜን በማጎናጸፍ፡ ፍሬያማ የኾነውን፥ ከፈጣሪ ጋር በቃል ኪዳን አገናኝቶ ያስተሣሠረውን፡ የቅዱስ ኪዳን ሃይማኖቱን፡ እነዚያ፡ ከላይ የተጠቀሱት አገሮችና ሕዝቦች፡ የየራሳቸውን ሃይማኖት፡ አጽንተው በመጠበቅ ሊሠሩበት እንደቻሉ ኹሉ፡ እርሱም፡ እንደነርሱ፡ በዚሁ ሃይማኖቱ ጸንቶ በመገኘት፡ በምግባር ሊፈጽመው ባለመፈለጉ ብቻ ነው፡፡

ይኸው ትውልድ፡ ራሱን፡ ለዚያ ቊም ነገር በማብቃት ፈንታ፥ እንዲያውም፡ ፈጣሪውን ብቻ ሳይኾን፡ ፍጥረተ ዓለሙን ጭምር ይግረማቸው ብሎ፡ የቀደሙት አባቶቹና እናቶቹ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥተው፡ ከእግዚአብሔር ጋር የተጋቡትንና ጠብቀው የኖሩትን፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ በይፋና በድፍረት በመተላለፍ፡ በየዘመናቱ፥ ዛሬም፡ በፈጣሪው ላይ፡ የክህደትን ከባድ ኃጢኣት፥ የዓመፅን ጽኑ በደልና የአምልኮን ገሃድ አመንዝራነት ፈጸመ፡፡ ለዚህ ድርጊቱም፡ አንዳችም ጸጸትን ባለማሳየት፡ እነሆ፡ በተባባሰ ይዞታ ቀጥሎበት ይታያል፡፡

ከዚህ ግብሩ የተነሣ፡ ይኸው ትውልድ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘውን የልጅነት ጸጋ ተገፍፎ፥ በፍላጎቱና በፈቃዱም፡ ራሱን፡ ለዲያብሎስ የአገዛዝ ባርነት ዳርጎ፥ እርስ በርሱ በመናጨትና ደም በመፋሰስም እየተላለቀ፥ በድርቅና በስደት፥ በችጋርና በቸነፈር እየተቆራመደ፡ እነሆ፡ የባዕዳኑ ጌቶቹ፡ ተመጽዋች ኾኖ ሲሽመደመድና ሲማቅቅ ይታያል፡፡ በዓለሙ ኅብረተሰብ ዘንድም፡ እንኳንስ፡ የዘመናዊው ሥልጣኔ ተቋዳሽ ሊኾን ይቅርና፡ ከሥጋዊዉም፥ ከነፍሳዊዉም፥ ከመንፈሳዊዉም ሥልጣኔ፡ ከአንዱም ሳይኾን፡ ይኸው፡ ከኹሉም የዓለም አገሮችና ሕዝቦች በታች፡ ወደኋላ የቀረ ኾኖ፡ አገሩን፡ ኢትዮጵያንና ወገኑን፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ፡ በሰብአዊው ዓለም ዘንድ፡ በውርደትና በድህነት የመጨረሻ መዝገብ አስመዝግቦ፡ ይህን የመሰለውን ኑሮ፡ (መኖር ከኾነ)፡ እየኖረው ይገኛል፡፡

የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በእግዚአብሔርና በቅድስት እናቱ ፊት ቀርቶ፡ በመላው ፍጥረተ ዓለም ዘንድ፡ ይህን በመሰለ አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ፡ ለቸሩ ፈጣሪያችንና እርሱን፡ በሰውነት ለመውለድ ለበቃችው እመቤታችን፡ ምስጋናችን ይድረሳቸውና፡ እናንተ እና እኛ፡ ይኸው፡ ለሰባት ሽህ አምስት መቶ አንድ ዓመታት በቆየው የነጻነት ህልውናችን መኖርን ቀጥለን እንገኛለን፡፡ የምንኖረውም፡ አገራችን ኢትዮጵያና ልጆቿ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በተመሠረተው ማንነታቸው፥ በዘመናዊው የሥጋ ሥልጣኔ ጭምር፡ ከማንኛውም አገርና ሕዝብ ይልቅ፡ በልጠው ሊያድጉ የሚችሉበትን፡ እውነተኛውን፡ የሃይማኖትና የምግባር፥ የኑሮና የአስተዳደር ሥርዓቶቻችንን እንደያዝንና እንደጠበቅን በመኾኑ፡ ደስ ሊለን ይገባል፡፡

ይህችው ኢትዮጵያም፡ እነዚያ፡ አረማዊውና አሕዛቡ፥ ይሁዲውና እስላሙ፥ ክርስቲያኑም ኹሉ፡ በአጠቃላይ፡ መላው ፍጥረተ ዓለም፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፥ በእግዚአብሔር አገርነቷና በእግዚአብሔር ሕዝብነቷ የሚያውቋትና ሕጋዊዉን እውቅና ሰጥተው፡ የተቀበሏት፥ የሚያከብሩዋትና የሚያሞግሷት፥ የሚያፈቅሩዋትና በትሕትና የሚያቅፏት፡ ያችው፡ የጥንቷ፥ የመሠረቷ ስትኾን፥ እርሷም፡ እኒህን ኹሉ፡ በፍቅርና በበጎ ዓይን እያየች፥ በክብር እንግድነትም እየተቀበለች ስታስተናግዳቸው የኖረችው ናት፡፡

የዛሬውም የዓለም ሕዝብ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ሕጋዊውን እውቅና ሰጥቶ፥ የቀደመውንም የማዕርግ ቦታቸውን መልሶ፡ በፍቅርና በክብር ሊቀበላቸው የሚችለው፥ የሚፈልገውም፡ በዚህ እውነተኛ ማንነታቸው ጸንተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

አዎን! በዚሁም ማንነታቸው፡ ተገልጸውና ተከናውነው ሲቀርቡለት ብቻ መኾኑን፡ ይኸው፡ “ኢትዮጵያዊ ነኝ!” የሚለው፡ የዛሬው ትውልድ፡ የሚሰማ ጆሮ ካለው፡ ሰምቶ ሊያውቀውና ሊረዳው፥ ሊያስተውለውና ሊገነዘበውም ይገባዋል፤ ይበጀዋልም።

ከዚህ በላይ፡ በዝርዝር እየተብራራ የታተተው ቊም ነገር ኹሉ፡ “የኢትዮጵያውያን፡ የሃይማኖት ጸሎት። የኢትዮጵያውያን፡ የቃል ኪዳን ጸሎት። ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የምስጋና ጸሎት። ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የሰላምታ ጸሎት።” በተባሉት የኢትዮጵያዊነት መለኮታውያን ሰነዶቻችን ውስጥ ተጨምቆና ተጠቃልሎ ይገኛል። እነዚህ ሰነዶቻችን፡ የእናንተ እና የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በምግባር የሚገለጽባቸው፥ ማንነታችን፡ በገሃድ የሚታወቅባቸውና ሕይወታችን የሚመራባቸው ስለኾኑ፡ ዘወትር፡ በየጊዜያቱ፡ በጸሎት መልክ፡ በቃላችን ጭምር ይዘን እንደግማቸዋለን። ከዚህ አድራጎታችን የተነሣም፡ ለመልካሙና ለዘለዓለማዊው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወት ያበቃን፡ የእነርሱ መለኮታዊ መልእክትነት ሳይለየን፡ እነሆ፡ ኃይል ኾኖን፡ አብሮን ይኳዛል።

እኒህ፡ የኢትዮጵያዊነት መለኮታውያን ሰነዶች የያዟቸውን የእግዚአብሔር የእውነት ቃላት፡ በሃይማኖት ተቀብሎ፡ በምግባር የሚፈጽም፡ ማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር፡ “ኢትዮጵያዊ ነኝ!” የሚለው ወገን ጭምር፡ ራሱን፡ ለ“ቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት” ማብቃቱን፥ በዚችም አፍታ፡ ይኸው ግለሰብ፡ “የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ” መኾኑን አረጋገጠ ማለት ነው። ግለሰቡ፡ ለዚህ ጸጋና ሕይወት መብቃቱን፡ እንዲህ፡ በራሱ ሕሊና፡ በእውነት ሲያረጋግጥ፡ ኹለንተናዊ ሰውነቱ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ጽላት፥ ታቦት፥ መንበር፥ መቅደስና ቤተ ክርስቲያን መኾኑን፡ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርለታል።

ከዚህ በኋላ፡ በማናቸውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ ኾኖ፡ ራሱን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ረቂቅ ዙፋን ፊት እንደቆመ አድርጎ፥ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮም ተመስጦ፥ ሦስት ጊዜ፡ ለሥላሴ፥ አንድ ጊዜ፡ ለእመቤታችንና አንድ ጊዜ፡ ለጌታችን ስቅለት ሰግዶ ይነሣል፤ እንደተነሣም፡ በእነዚያ፡ በአራቱ፡ የኢትዮጵያዊነት መለኮታውያን ሰነዶች ላይ የተመሠረተውን፡ የምስክርነት ቃሉን፡ ለብቻውም ኾነ፥ ወይም፡ ሰው ባለበት፡ ድምፁን በማሰማት፡ በይፋ ይሰጣል። ወዲያውም፡ እያንዳንዳቸው፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ቀለማት ያላቸውን ሦስት ፈትሎች (ክሮች) ያሉትን ማተብ፡ በመስቀል በማማተብ፡ እዚያው በእናትና ልጁ ፊት እንደቆመ ባርኮ፡ በአንገቱ ላይ ያሥረዋል።

ግለሰቡ፡ ይህን ሥርዓት እንደጨረሰ፡ ስመ ክርስትናው፡ በመንፈስ ቅዱስ እጅ፡ በሕይወት መጽሐፍ ይመዘገባል። (በእነዚህ በአራቱ፡ የኢትዮጵያዊነት መለኮታውያን ሰነዶች ላይ የተመሠረተው፡ የምስክርነት ቃል፡ “ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፤ አንደኛ መጽሐፍ” በሚለው፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ ባዘጋጁት ዕትም፡ ገጽ ፪፻፱ ላይ ይገኛል።)

በዚህ ጊዜ፡ መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ “እብለክሙ፥ ከመ ከመዝ ይከውን ፍሥሓ፡ በሰማያት፥ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር፥ በበይነ አሐዱ ኃጥእ ዘይኔስሕ፡ ፈድፋደ፡ እምነ ተስዓ ወተስዐቱ ጻድቃን፡ እለ ኢይፈቅዱ ይነስሑ።”

ማለትም፡ “እላችኋለሁ፥ እንዲሁ፡ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፡ ንስሓ በሚገባ፡ በአንድ ኃጢአተኛ፡ በሰማያት፥ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ደስታ ይኾናል።” ያለው፡ መለኮታዊ ቃሉ ይፈጸማል። (ሉቃ. ፲፭፥ ፯-፲።)

የእግዚአብሔር የኾነውን፡ ለመንፈስ ቅዱስ እንተወውና፡ ይህ ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ለዚህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት መብቃቱን፡ ለራሱ የሚያውቀውና የሚያረጋግጠው፥ ለሌላውም የሚያሳየውና የሚያስመሰክረው፡ በእውነተኛ አምልኮቱ፥ በእግዚአብሔራዊው እውቀቱ፥ በሕፃንነት ግልጽነቱ፥ በተነሳሒ አፍቅሮቱ፥ በትሕትና ድህነቱ፥ በትእግሥታዊ ጽናቱ እና በጤናማ ትህርምቱ (ራስን ከክፉ ነገር መጠበቅ) ምግባራት ሲገልጸው መኾኑን፡ ራሱ ይገነዘበዋል።

# መፈጸም

ይህን፡ **የምሥራች** መልእክታችንን የምናጠቃልለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አምነውበት ለተከተሉት አገልጋዮቹ ሓዋርያት፡ ከትንሣኤው በኋላና ከዕርገቱ በፊት፡ በተናገራቸው የመጨረሻ ቃላቱ ይኾናል። ይኸውም፡-

**"ተውህበ ሊተ፡ ኵሉ ኵነኔ ሰማይ ወምድር። ...ሑሩ፥ ውስተ ኵሉ ዓለም! ወስብኩ ወንጌለ ውስተ ኵሉ ፍጥረት! ...ወመሀሩ፡ ኵሎ አሕዛበ! ወእንዘ ታጠምቅዎሙ፡ በሉ! 'በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ'። ወመሀርዎሙ፡ ይዕቀቡ፡ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ። ወናሁ፡ አነ እሄሉ ምስሌክሙ፡ በኵሉ መዋዕል፥ እስከኀልቀተ ዓለም።"**

ማለትም፡ **"የሰማይና የምድር ሥልጣን ኹሉ ተሰጠኝ። ...እንግዴህ፡ ወደዓለሙ ኹሉ ኺዱ! የምሥራቹንም፡ ለፍጥረቱ ኹሉ ስበኩ! ...አሕዛብንም ኹሉ አስተምሩ! ስታጠምቋቸውም፡ 'በስመ አብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ!" በሉ! ያዘዝኋችሁንም ኹሉ እንዲጠብቁ አስተምሩዋቸው! እነሆ፡ እኔ፡ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ኹልጊዜ፡ ከእናንተ ጋር ነኝ።"** የሚለው መለኮታዊ መመሪያው ነው። (ማቴ. ፳፰፥ ፲፰-፳። ማር. ፲፮፥ ፲፭።))

ቅዱሳን ሓዋርያት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ በአዋጅ እንዲያሰሙ፡ የዛሬ ኹለት ሺህ አንድ ዓመት፡ በእርሱው፡ በዓለሙ ፈጣሪ የታዘዙትን፡ ይህን "ታላቅ፥ ቋሚና ዘለዓለማዊ የመለኮት ምሥራች!"፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እናንተ እና እኛ፡ በዚህ መልእክታችን አማካይነት፡ ከኹለት ሺህ አንድ ዓመታት በኋላ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ እንደአዲስና እንደእንግዳ ነገር፡ በጽሑፍ አቅርበነው፡ እንዲነበብና እንዲሰማ ማድረጋችን፡ አያስገርምምን? ይልቁንም፡ ይህ ምጽአታዊ ምግባር፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዛሬ ተጠብቆ ለቀየው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ባለአደራዎች ኾነው በኖሩት፡ በ"ኢትዮጵያ ልጆች" የተፈጸመ፡ ኾኖ ሲገኝ፡ አያስገርምምን? አዎን! በእርግጥ ያስገርማል፤ ያስደስታልም፤ አግባብም ነው።

ይኸው፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል" ተብሎ፡ ስለዓለሙ መጨረሻ ምልክትነቱ፡ በጌታ ቃል የተነገረለት፡ የምሥራች መልእክት፡ የስሕተት ጕዞውን፡ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ፡ እያራቀቀ በመኼድ ላይ ያለውን፡ ክርስቲያኑን ዓለም ብቻ ሳይኾን፥ ይልቁንም፡ ከክርስትና እምነት ውጪ የኾነውን፡ ሌላውን የዓለም ሕዝብ፡ እንደሚያስገርማቸው፥ ከዚያም አልፎ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ትውልድ፡ በከፍተኛ ደረጃ እንዲታዘቡት እንደሚያደርጋቸው አይጠረጠርም።

ለመኾኑ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ይህን፡ የምሥራች መልእክት፡ በዚህ መልኩ እንድናወጣው፡ እናንተንና እኛን ያስገደደን፡ ምንድር ነው? እንዳለፉት ትውልዶች ኹሉ፡ በጥንታዊው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ላይ፡ ታላቁን፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአት የፈጸመው፡ የዚሁ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ድርጊት አይደለምን? አዎን! እውነታው፡ ይኸው መኾኑን፡ ኹላችንም እናውቀዋለን።

ይኹን እንጂ፡ ይህ የምሥራች መልእክት፡ ሺሁ ዓመት አልቆ፡ ኹለተኛው ሺህ ዓመት በተጀመረበት እና ያ፡ "የቀደመው እባብ" የተባለው ዲያብሎስ፡ "ለጥቂት ጊዜ" ከእሥራቱ በተፈታበት፡ በአንደኛው ዓመት ላይ የቀረበ ስለኾነ፡ እየራሳችንን፡ ለፊተኛዪቱ የትንሣኤ ሕይወት ላበቃነው፡ ለእናንተና ለእኛ፡ ምሥራቹ፡ ላለንበት ህልውናችን፡ ማጽኛና ማጐልበቻ ሲኾን፥ እየራሳቸውን፡ ለዚህ ዕድል ላላበቁት ደግሞ፡ የምሥራቹ ማስታወሻና መቀስቀሻ ነው። ስለዚህ፡ በዚህ ወቅት፡ **ታላቁ ምሥራች!** እንደገና፡ በይፋ ታውጆ መነገሩ፡ በእርግጥ አግባብና ተገቢ ይኾናል።

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከፈጸመው የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ ምንዝርና ኃጢአቱም የተነሣ፡ አኹን እየማቀቀ ከሚገኝበት የሥቃይ ህልውናው፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሶ፡ ራሱን፡ ለምን፡ ለዚህ ቋሚና ዘለዓለማዊ የምሥራች ሕይወት አያበቃም? ይህን ታላቅ ቊም ነገር ለመፈጸም፡ ከልቡ ከፈለገና በእርግጥ ከመረጠ ደግሞ፡ ምንም የሚያዳግተው፥ አንዳችም የሚያስቸግረው ምክንያት አይኖርም።

አዎን! በእርግጥ ከፈለገና ከልቡ ከመረጠ፡ ራሱን፡ ለዚህ ቋሚና ዘለዓለማዊ የምሥራች ሕይወት ሊያበቃ ይችላል:: ለምን አይችልም? ይችላል እንጂ::

የፈለገውንና የመረጠውን ለማድረግ ከወሰነማ፡ እንኳንስ፡ ይህን፡ የራሱ የኾነውንና ከእግዚአብሔር ያገኘውን፡ የመልካም ሕይወት መገኛ ሥርዓት ይቅርና፡ የባዕዳንና ሰይጣናዊ የኾነውን ሌላውን፡ ሊሠራበት የሚችል መኾኑን፡ ባለፈው አረጋግጦ ያሳየ አይደለምን? ዛሬስ፡ ይኸው፡ አረጋግጦ በማሳየት፡ እያስመሰከረ አይደለምን?

ለማስረጃም ያህል፡ በቅርቦቹ ዘመናት እንኳ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ፡ Capitalism (ካፒታሊዝም) የሚባለውን፡ በገንዘብ ብዕል ላይ የተመሠረተውን፡ የምዕራባውያንን የአስተዳደር ፖሊሲ፥ ቀጥሎም፡ በደርግ ጊዜ፡ Communism (ኮሚዩኒዝም) የሚባለውን፡ "እግዚአብሔር አልባ" የኾነውን የምሥራቃውያኑን አረመኔያዊ አገዛዝ፡ ለአጭጭር ጊዜያትም ቢኾን፥ ይኸው፡ አኹን ደግሞ፡ Democracy (ዲሞክራሲ) የሚባለውን ዓለማዊ የክፍፍል አመራር፡ ተቀብሎ ሊሠራባቸው መቻሉን አረጋግጧል::

በዚህ ረገድ ያሉትን፡ የሩቆቹንም ዝክረ ነገሮች ማውሳት አያዳግትም:: እነዚህም፡ እንደቅርቦቹ ኹሉ፡ ለአጭጭር ጊዜያትም ቢኾን፡ በውድም ኾነ በግድ ተቀብሎ የኖረባቸው፡ የአይሁድ፡ እስራኤላዊነት፥ የጉዲት፡ ይሁድና፥ የግብፅ ኦርቶዶክሳዊነት፥ የአሕመድ ግራኝ እስልምና፥ የሮማውያን፡ ኵትልክና፥ የኢጣልያን ፋሺዝም አገዛዞች ናቸው::

ይልቁንም፡ እናንተና እኛ፡ የዓይን ምስክሮች የኾንንበትን፡ "እግዚአብሔር የለም!" የሚለውን የCommunismን፥ ወይም፡ የScientific Socialismን (ሳይንቲፊክ ሶሺያሊዝም=ሥነ እውቀታዊ ኅብረተሰብአዊነትን) ባዕድና ሰይጣናዊ የአገዛዝ ፍልስፍና፡ ይኸው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ሥጋውያን መሪዎቹ በኾኑት፡ በቤተ ምልክናው አማካይነት ብቻ ሳይኾን፡ በቤተ ሕዝቡና በቤተ ክህነቱም ግብረ አበርነት ጭምር፡ በአንድነት፡ "ሆ!" ብሎና አጨብጭቦ ተቀብሎትና ኖሮበት አይተነው የለምን?

ታዲያ፡ አልፈለገውም እንጂ፡ ከፈለገውማ፡ በዚህ የምሥራች መልእክት ተብራርታ የተገለጸችውንና ለሰባት ሺ አምስት መቶ አንድ ዓመታት በነጻነት ያኖረችውን፥ የራሱ የኾነችውንና የሚያውቃትን፡ ይህችን የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱንና በእርሷ ያገኛትን የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥርዓት ተቀብሎ፡ የክብርና የሰላም፥ የብልጽግና የዕድገት ህልውናውን፡ በሚያስተማምን ይዞታ መቀጠል፡ ምን ይከለክለው ነበር? ካለመፈለጉ በቀር፡ አዎን፡ ምንም የሚከለክለው ነገር አልነበረም፤ አኹንም፡ የለም::

በዓለም ላይ የሚኖሩት የእግዚአብሔር ፍጡሮች የኾኑት ሕዝቦች ኹሉ፥ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ ጭምር፡ በያገራቸው ላለው፡ ለየመንግሥታቸው መሪዎች የሚኾኑትን ባለሥልጣኖች በሚመርጡበትና የምርጫው ውድድር ተፈጽሞ፡ አሸናፊው በሚታወቅበት ጊዜያት፡ የሚያደርጉት የደስታ በዓል፡ የቱን ያህል የላቀና ትንግርታዊ መኾኑ፡ በማንኛውም ዘመናዊ ሰው ዘንድ ይታወቃል:: እንዳጋጣሚ፡ በዚህ በኹለት ሺህ አንደኛው ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ላይ፡ በሥጋዊው ሥልጣኔና ሀብት፡ የዓለሙ ልዕለ ኃያላን በተባለው ታላቅ አገር፥ የመላውን ዓለም ኅብረተሰብ ጨምሮ፡ በዚህ ረገድ የታየው ኹኔታ፡ ለዚህ አገላለጣችን እውነተኛነት፡ በቂ ማስረጃ ነው::

ዓለማውያን ሰዎች፡ በዚያ ሥጋዊ ፍልስፍናቸው ላቋቋሙትና ለሚመሩት፥ ለሚተዳደሩበትም ምድራዊ መንግሥታቸው፡ ያን የሚያህልና ያን የመሰለ፡ ጊዜያዊ የደስታ በዓል ካደረጉ፡ እናንተና እኛማ፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት፡ "ሥዩማነ እግዚአብሔር" በሚል ማዕርግ፡ አባሎቿና አገልጋዮቿ፥ ዜጎቿና ሕዝቧም በመኾናችን፡ ደስታችን የቱን ያህል ሊልቅ እንደሚገባ መገመት፡ ከቶ አያዳግትም:: ይልቁንም፡ የዚችው መንግሥት፡ ባለቤቶቿ፥ የእኛም መሪዎቻችን፡ ዓለም ከተፈጠረ እስከዛሬ፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም፥ ወደርና መሰል የሌላቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም በመኾናቸው፡ ከእነዚያ፡ ከዓለማውያኑ ደስታ ይልቅ፡ የእኛ ደስታ፡ እንደምን፡ በብዙ መጠን ዕጥፍ ድርብ አይኾን? አማናዊውና ፍጹሙ፥ ኹለንተናዊውና ሕያዉ ደስታስ፡ እንዴት አይሰማን!? አዎን! ይሰማናል እንጂ::

እናንተና እኛማ፡ እንዲያውም፡ አልፈን ተርፈን፡ ከዚሁ ደስታችን የተነሣ፡ ይኸው፡ እንደዛሬው፡ ኹልጊዜም፡ "የምሥራች!" ልንባባል ይገባናል፡፡

እንግዴህ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠውና ዛሬም፡ በመንፈስ ቅዱስ እየሠራ ያለው እግዚአብሔር፡ ከጥንት ከመሠረቱ አንሥቶ፡ የእርሱ "ልጆች" ለተባሉትና እውነተኞች አማኞቹ ለኾኑት፡ ቅዱሳን ኢትዮጵያውያንና ቅዱሳት ኢትዮጵያውያት፡ የወጠነውንና ያካኼደውን፥ በመጨረሻም የፈጸመውን የቸርነት ሥራውን፡ እስከዚህ በቀረበው የሓተታ ቅንብር ተመልክተናል፡፡

ፈጣሪያችን፡ ገና ከመጀመሪያው፡ እናንተን እና እኛን፡ እያንዳንዳችንን፡ በመልኩ ከመፍጠሩና "ሰው፡ ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" ካሰኘው ማዕርጉ እስካበቃን፥ በዚያም ብቅዓታችን፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የመባልን ክብር፡ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት  አጎናጽፎ ካኖረን በኋላ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ በፈጸመው ትስብእቱ ቤዛነት፡ እንደገና፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ፡ ከእግዚአብሐር ተወልደን፡ ያን የቀድሞ ልጅነታችንን፡ በዘለዓለማዊነት አድሶ አጸናው፡፡ እናንተ እና እኛም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እንደመኾናችን መጠን፡ በእግዚአብሔርዋ የእውቀት ጸጋ፡ ይህንኑ ተረድተንና ተገንዝበን፡ የበኩላችንን ድርሻ መፈጸማችንን፡ በእነዚህ፡ ከላይ በተጠቀሱት እውነታዎች፡ በሚበቃ እንደተረዳን እናምናለን፡፡

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ ሥነ ፍጥረትን አስቀድሞ አዘጋጅቶ፥ በመልኩና በእውቀቱም፡ ራሱን አስመስሎ፡ በወንድና በሴት ጾታዎች፡ በክብር ለፈጠረው ለሰብአዊው ወገን፡ በሥጋው፥ በነፍሱና በመንፈሱ፡ መልካም ሕይወት ይኾንለት ዘንድ የሠራለት፥ በመለኮታዊው የትስብእት ደሙም ቤዛነት፡ ከዲያብሎስና ከክፋት ኃይላት፥ ከኃጢኣትና ከሞት ነጻ ያደረጋት መንግሥቱ፡ እንዲህ፡ የእኛ ከኾነች፥

እርሷም፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በመላዉቱ ምድርና ፍጥረተ ዓለም ላይ የሰፈነች ከኾነች፥

ለእርሷ መንጻትና በዘለዓለማዊ ህልውናዋ መጽናት፡ የደከሙላትና የመጨረሻውን ታላቅ መሥዋዕትነት የከፈሉላት፡ ፈጣሪዋና ባለቤቷ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ የኹለንተና መሪዎቻችን ከኾኑ፥

ይህችው፡ <u>"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡</u> ላለፉት ፯ሺ፭፻፩ ዓመታት፡ ቀድሞ፡ በገነት የተድላ ሕይወት፥ ኋላም፡ በዘመነ ምሕረት፡ በፊተኛው ትንሣኤ፡ የኖርንባትና የምንኖርባት ከኾነች፥

እናንተም፥ እኛም፥ ኹላችንም፡ ለዚህ ጸጋ በመብቃታችን፡ እጅግ  ደስ ብሎን፡ ይህን የምሰለውን ቸርነት ላደረጉልን መሪዎቻችን፡ ፍጹም ምስጋናችንን የምናቀርብላቸው ከኾነ፥

እነርሱም፡ ፈጣሪ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ ለዚህ ማዕርግ በመብቃታችን፡ በእኛ፡ ደስ የሚላቸው ከኾነ፡ ታዲያ! ከዚህ የበለጠ ምን የምሥራች አለ? የለም፡፡ ስለሌለማ፡ ይኸው፡ "በያለንበት እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!" ለመባባል፥ ይህንም፡ የምሥራች መልእክት፡ በዚህ ቋሚ መልኩና ዘለዓለማዊ ይዘቱ ለማስተላለፍ፡ እነሆ፡ በቃን፡፡

ከዚህ ጋር፡ ይህ የምሥራች መልእክት፡ በቀናውና በታማኙ ሕሊናችሁ ውስጥ፡ ምናልባት፡ እስካኹን የሚጉላሉና ያልተመለሱ ጥያቄዎች ቢኖሩ፡ ለእነዚያ ፍለጋዎቻችሁ፡ መልስና ማብራሪያ ኾኖ እንደምታገኙት፥ ደግሞም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ላይ ተመሥርቶ የጸናው፡ ሥጋዊውና ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊውም ህልውናችሁ፡ በዘወትሩ ንስሓችሁ፡ ፍጹም ጤናማ፥ ከጥርጥርና ከውልውል፥ ከማመንታትና ከፍርኀት፥ ከጭንቀትና ከሥጋት የነጻ፡ መልካም ሕይወት ኾኖላችሁ እንደምትቀጥሉ እናምናለን፡፡

እንግዲህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን ምክንያት፡ ስማችን፡ በእግዚአብሔር የሕይወት መጽሓፍ ውስጥ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተመዘገበው፡ እናንተ እና እኛ፡ በመላው ዓለም በተዘረጋችውና በሰፈነችው በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የአባልነት ምዝገባና የወር ክፍያ፥ መታወቂያ ደብተርም ሳያስፈልገን፡ በያለንበት እንዳለን ኾነን፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችን አማካይነት፡ ዘወትር፡ በየግላችን እንገናኛለን። በማኅበር እንሰባሰባለን። መንፈሳዊ ግንኙነታችንን፡ በዚህ መልክ በማካኼድ፡ ኢትዮጵያዊቷን የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወታችንንና አገልግሎታችንን፡ በያለንበትና በየሙያችን እንቀጥላለን።

በዚህ ቃል፡ መለኮታዊዉን የምሥራች መልእክታችንን በማጠቃለል፡ እንደገና፡ በያለንበት፡ "እጅግ ደስ ይበለን! ታላቅ ሓሤትም እናድርግ!" እያልን፡ ለጊዜው እንሰናበታችኋለን።

\+ \+ \+